#DEFYHATENOW

# የመስክ ስራ መመሪያ

## የማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግር መከላከያ

### ኢትዮጵያ

**ሞጁል 1**

ሁለተኛ እትም 2017

https://defyhatenow.org
ethiopia@defyhatenow.org

©2025 r0g_agency for open culture and critical transformation gGmbH Berlin
Concept: r0g_agency gGmbH Berlin, Stephen Kovats & Susanne Bellinghausen

**የመስክ መመሪያው አርክቴክቶች፡-** ኬንዲ ጂኩንዳ
**የመስክ መመሪያው ጸሀፊዎች እና አርታዮች፡-** ካሮላይን ፓትሪክ፣ ኬንዲ ጂኩንዳ እና ሳራ ቡዳርዝ
**የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ፡-** ብሩክ መዝገቡ
**የመስክ መመሪያው  አጠቃላይ ይዘት ኤዲቶሪያል አማካሪዎች፡-** ኤደን በሪሁን፣ አቤሴሎም ሳምሶን፣ ርሆቦት አያሌው፣ ማቲያስ አሰፋ እና የምስራች የትነበርክ
**የመስክ መመሪያው ጨዋታ ጽንሰ-ሀሳብ፡-** ጆዲ ሮዝ እና የምስራች የትነበርክ
**የመስክ መመሪያው ንድፍ እና አቀማመጥ፡-** የምስራች የትነበርክ
**የኢትዮጵያ የመስክ መመሪያ ማሳያዎች፣ A2-ፖስተሮች እና የጨዋታ ንድፎች፡-** የምስራች የትነበርክ
**የመስክ መመሪያው የአቻ ግምገማ አስተባባሪ፡-** ይበልጣል አሰፋ
**የመስክ መመሪያው ነባረዊ ሁኔታ አቻ ገምጋሚዎች፡-** መሀመድ አሊ፣ ህይወት አሸናፊ፣ አቤል ዮናስ፣ ተስፋዬ ይመር፣ አንተነህ ሰይፉ፣ አብዱራዛቅ ነስሮ፣ ቆንጂት ዘውዴ፣ ኤደን ወርቃለማሁ፣ ተመስገን ቢረዳ፣ አሰፋሽ ከተማ፣ ሳራ ገዛኸኝ (MD)፣ ሰላም ገብረመድህን፣ እልልታ ሞላ እና ሃና አድማሱ
**የመስክ መመሪያው ነባረዊ ትርጉም ገምጋሚዎች፡-** ባልቻ ቢርቢሳ ጂማ_አፋን ኦሮሞ፣ ኃይለመለኮት ታደሰ_ትግርኛ፣ ቴዎድሮስ አለማየሁ _አማርኛ
**ትርጉም፡-** ሰላም ነጋሽ የትርጉም እና ሴክሬታሪያል አገልግሎት በፍቅረስላሴ የማነ፣ ተሰማ በቀለ እና ጥላሁን ሸዋዬ መሪነት

የ#defyhatenow የማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግር የመስክ ስራ መመሪያ በሼር አላይክ 4.0 አለም አቀፍ ፍቃድ ያለው የጋራ የፈጠራ ውጤት ነው።

የ#defyhatenow የማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግርን የመከላከል እንቅስቃሴ የr0g_ኤጀንሲ ፎር ኦፕን ከልቸር ኤንድ ክሪቲካል ትራንስፎርሜሽን gGmbH በርሊን ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ተባባሪዎች ጋር የሚተገበርና በአውሮፓ ህብረት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ነው።

Print ISBN: 978-3-949253-12-6
EBook ISBN: 978-3-949253-13-3

ኢትዮጵያ፣ ሁለተኛ እትም፣ 2017

#defyhatenow
https://defyhatenow.org/ethiopia/
https://www.facebook.com/defyhatenowethiopia/
https://www.instagram.com/defyhatenow_ethiopia/

Funded by
the European Union



# መቅድም



*ዲጂታል ማካተት እና የሲቪክ ተሳትፎ ታሪክ ሰሪ እና ሻምፒዮን እንደመሆኔ በአፍሪካ ውስጥ የዲጂታል መብቶች ማንነት ምርጫዎቻችንን፣ ታማኝነቶቻችንን እና ማህበረሰቦቻችንን እንዴት እንደሚቀርጽ ከልብ አደንቃለሁ። ከሲቪል ማህበረሰብ ተዋናዮች እና ከወጣቶች ጋር በመስራት ማንነት እንዴት ኩራትን፣ ባለቤትነትን ዓላማን ሊያቀርብ እንደሚችል መገናኛ ብዙሃን ገልጧል። በተሳሳተ መንገድ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት ማንነት ጥቅም ላይ ሲውል መለያየት፣ ማግለል እና መነሳሳት ሊያስከትል ይችላል። በሰላም ጊዜ ማንነት ማህበራዊ ድርን ያጠናክራል፣ በግጭት ጊዜ ደግሞ ሕዝብን ለመበተን እንደ መሣሪያ ሊጠቅም ይችላል።*

ኢትዮጵያ በድንገት በይነመረብን ማዕከል ባደረገ አለም ውስጥ አብሮ ለመኖር ስትታገል የ#defyhatenow ማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግር ቅነሳ የመስክ መመሪያ እየሆነ መጥቷል። በግጭት ትስስር እና ከመስመር ውጭ ያሉ ጥያቄዎችን በአየር ላይ በሚዲያ መረጃነት ማንበብና መጻፍ ጥልቅ ግላዊ እና ፖለቲካዊ የማንነት ፅንሰ- ሀሳብ ያስከትላሉ።

ይህ የመስክ መመሪያ ውስብስብነት ከሚያመጣው ልዩነት ወደ ኋላ አይልም። ማንነት ከተወለደ ጀምሮ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ እና በትምህርት እንዴት እንደሚፈጠር ይዳስሳል - ሁሉም በዚህ ዘመን በማህበራዊ ሚዲያ እና በይነመረብ የማይካድ ተፅእኖ የተቀረጹ ናቸው። በኪነ-ጥበባት እና በሰላም ግንባታ መካከል ግንኙነቶችን በመፍጠር ጾታዊ ጥቃትን ለመቀነስ ተስፋ ሰጭ መንገድን በመክፈት የአዕምሮ ጤናን የሚመለከት ጥያቄ ይፈታል።  የዚህ አቀራረብ ቁልፍ አካል የተለያዩ ተዋናዮች እውቅና መስጠት እና ሰላምን ለማስፍን ስለሚያስፈልጉ




ሀብቶች ነው። መመሪያው የማህበረሰብ መሪዎችን (ሽማግሌዎችን፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የወጣት መሪዎችን) እና የሚዲያ እና የመረጃ እውቀትን የጥላቻ ንግግርን፣ የተሳሳቱ መረጃዎችን እና ማነሳሳትን ለመለየት እንደ መድኃኒት አፅንዖት ይሰጣል፣ በተለይም በዛሬው ዲጂታል ዓለም፣ የአየር ላይ ጉዳቶች የእውነተኛ ህይወት መዘዝ ይሆናሉ።

ወጣቶች በበይነመረቡ ላይ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ኃይል ስለተሰጣቸው ለበጎእንዲጠቀሙት ማድረግ። ይገባል። በመመሪያው መጽሐፍ መሠረት፣ ወጣቶች ውይይትን ለማሽከርከር እና አካታች የወደፊት ሁኔታዎችን እንደገና ለመገመት ልዩ አቅም ያላቸው ንቁ የለውጥ ወኪሎች ናቸው። ሥነ-ጥበብ በተለምዶ ለጭንቀት ፈውስ፣ ራስን ለመግለጽ እና ከግጭት በኋላ ርኅራኄን የማሳያ መንገድ ሆኖ ቆይቷል። ቲያትር፣ ተረት ተረት፣ ሙዚቃ እና ምስላዊ ሥነ-ጥበባት ከንግድ ባሻገር የፈጠራ ልምዶች እና ቦታዎች ናቸው። ለተበታተኑ ማህበረሰቦች ዕርቅ እና መልሶ ግንባታ አስፈላጊ መሣሪያዎች ናቸው።

ጥላቻን እና የተሳሳተ መረጃን ለመከላከል የአካባቢው እውቀት፣ የዲጂታል ተጠያቂነት፣ እና የማህበረሰብ የመቋቋም አቅም #defyhatenow ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ናቸው። ይህ መመሪያ አውድ እና ተስማሚ የባለድርሻ አካላት መፍትሄዎችን በመስጠት ይህንን ጥረት ያሻሽላል።

ይህን መመሪያ ሰላም ሰባኪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ጋዜጠኞች፣ ተዋናኝ፣ የማህበረሰብ አስተባባሪዎች እና ማንኛውም ይመለከተኛል የሚል ማህበራሰብ እንድ ግብዣ ሀሳብ ሊሰጥበት፣ ሊወያይበት እና ትርጉም ያለው ለውጥ ሊያደርግበት የተዘጋጀ እንጂ ማንዋል አይደለም። ■



*ዶክተር ንጋላ ዴዝሞንድ ንጋላ ,*
*የሲቪክ ዋች ካሜሩን ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣*
*የካሜሮን ስነዜጋ ጠባቂ እና የ**#defyhatenow***
*ካሜሩን ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ*

# ማውጫ


**8 01 ማንነት**

10 ማንነትን ከሰላምና ግጭት አንፃር መረዳት

**11 1. መግቢያና ፍቺዎች**

**11 2. ማንነትና የማንነት አመሰራረት**

14 2.1 ማንነት እና ይዘቱ

15 2.2 ተጨማሪ ግብዓቶች

**15 3. ማንነት እና ግጭት**

16 3.1 የማንነት ብሄርተኝነት

17 3.2 ብሄርን መሰረት ያደረገ የፌደራሊዝም ስርዓት እና ግጭት

18 3.3 ማንነት ለግጭት

18 3.4 ጭፍን ጥላቻ

19 3.5 የጥላቻ ፒራሚድ

21 3.6 ከማንነት ምክንያቶች ጋር የተያያዙ - በኢትዮጵያ የሚቀሰቀሱ ግጭቶች

**23 4. ማንነት፣ የሰላም ግንባታ እና እርቅ**

23 4.1 ትርጉም ያለው የቡድን ውይይት ሚና

25 4.2 የማህበረሰብ መሪዎች ሚና

27 4.3 የፖሊሲ ሀሳቦች/አስተያየቶች

**28 02 ሚዲያ እና የመረጃዎች መዛባት**

30 በግጭት ውስጥ የመገናኛ ብዙሃን አስተዋፅኦ መረዳት

**31 1. መግቢያ**

31 1.1 ሚዲያ ምንድን ነው?

31 1.2 መደበኛ ወይም ነባር እና አዳዲስ ሚዲያ ተቃርኖ

33 1.3 ኢንተርኔት እና ማህበራዊ ሚዲያ

**36 2. ሚዲያ እና የመረጃ እውቀት**

37 2.1 የሚዲያ ይዘቶች እና የመረጃ እውቀት

**40 3. የጥላቻ ንግግርና የጥላቻ ንግግርን መቃወም**

40 3.1 የጥላችን ንግግርና አደገኛ ንግግሮች

42 3.2 የጥላቻ ንግግር ማዕቀፎች

42 3.3 የጥላቻ ንግግር አመላካቾች እና ምልክቶች

44 3.4 የጥላቻ ንግግሮችን ማየት/ቼክሊስት

45 3.5 የጥላቻ/አደገኛ ንግግሮች መቃወም

**45 4. የተሳሳተ መረጃ እና የማረጋገጫ እውነታዎች**

47 4.1 የተሳሳተ መረጃ

49 4.2 የተሳሳተ መረጃ ገጽታዎች

52 4.3 እውነታን የማጣራት እና የመቃወሚያ ስልቶች

54 4.4 የተሳሳቱ መረጃዎች ዝርዝር በወቅቱ መለየት

**56 03 ጥበብ ለሰላም ግንባታ**

58 አርቲቪዚም ከኢትዮጵያ አውድ አንፃር

**59 1. መግቢያ እና ትርጓሜዎች**

**61 2. ጥበብ እና ታሪካዊ ዳራው**

62 2.1 ሃይማኖት እና ጥበብ በኢትዮጵያ

63 2.2 ንጉሳዊ የመኖሪያ ስፍራዎች እና የጥበባት ማበብ

63 2.3 ጥበብ እና የማህበረሰብ ግርግር

**65 3. ጥበብ ለአንድነትና ለብዝሃነት አከባበር**

66 3.1 የጥበብ ቅጾች

**70 4. ጥበብ እንደ የማህበራዊ ለውጥ ቀስቃሽነት**

**73 5. ጥበብ ለድህረ-ግጭት ፈውስ**

73 5.1 ጥበብ ጠባሳን ይፈውሳል - በዚህ መልኩ

**78 ለአመቻቾች የተዘጋጁ ማስታወሻዎች**

**78 1. ስልጠና ማመቻቸት**

**78 2. የክፍለ ጊዜዎን እቅድ ማውጣት**

**82 3. መሰረታዊ ስልጠናዎች**

**83 4. ክፍለ-ጊዜውን ማመቻቸት**

**86 5. በራስ ከስልጠናው ያገኙትን ማብራራት**


**89 ምስጋና**

# 01

# ማንነት



# ማንነትን ከሰላምና ግጭት አንፃር መረዳት



## የምዕራፉ ዓላማ

*በዚህ ምእራፍ መጨረሻ ማንነት ከብሔር፣ ከሃይማኖት፣ ከቋንቋ እና ከክልል ጋር እንዴት እንደተሳሰረ፣ ሰዎች ራሳቸውን እና ሌሎችን እንዴት እንደሚገነዘቡ እና እነዚህ ማንነቶች በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት እንደሚለዋወጡ መረዳት ትችላላችሁ።*

በተጨማሪም ይህ ማንነት ከሰላምና ግጭት ጋር ተለዋዋጭነት ባለው መልኩ ምን አይነት ተጽእኖ እንዳለው ትማራላችሁ። እንደ ማህበራዊ ማንነት ያሉ ማዕቀፎች እንዴት ማንነቶቻችን በተለያዩ ሁኔታዎች እንደሚደራረቡ የሚያሳዩ ይሆናሉ። በተመሳሳይ ሁኔታም የጥላቻ ፒራሚድ ከትንሽ የማዳላት ስራዎች በተለይ እንደ ማንነት መገለጫዎች ወይም እንደ ቀልድ ጀምሮ በቀላሉ ካልተቀረፈ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንደሚደርስ ወይም እንደሚያድግ በግልጽ የሚያሳያችሁ ይሆናሉ። የሰላም ግንባታ ማለት ያለፉትን ኢ-ፍትሃዊ ድርጊቶች እውቅና መስጠት፣ ሁሉን ያካተተ ትርክቶችን ማበረታታት እና ለውይይት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ማለት ነው። በመሆኑም የማንነት ሀይልና አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት አድሎአዊ ድርጊቶችን ቀደም ብለን በመፍታት ወደ እርቅ እና የበለጠ ሰላማዊ የወደፊት ሁኔታን መፍጠር እንችላለን።

# ዩዘት


8 የምዕራፉ ዓላማ
9 መግቢያና ፍቺዎች
9 ማንነትና የማንነት አመሰራረት
13 ማንነት እና ግጭት
21 ማንነት፣ የሰላም ግንባታ እና እርቅ




## 1. መግቢያና ፍቺዎች



*ማንነት የሚያመለክተው አንድን ሰው ወይም ቡድንን ነው። እነዚህም ግላዊ እና ማህበራዊ ገጽታዎችን ያጥቃልላሉ። ግለሰቦች እራሳቸውን እና ሌሎችን እንዴት እንደሚገነዘቡ የሚቀርጹ ልዩ የእምነት እና የባህሪዎች ስብስብ ነው።*

በመሆኑም ማንነት （እራሳችን የምናይበት እይታ） መሰረት የሚገለጽ እና የተለያዩ ተጨባጭ ነገሮች ላይ የተመሰረተ （በስነ ህይወት ወይም በማህበራዊ ጉዳዮች ለራስዎ የሚሰጡትን አመለካከትና እይታ） ላይ የተመሰረተ ነው። ማንነት  የባህል፣ የብሔር፣ የብሔራዊነት፣ የሀይማኖት፣ የጾታ እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ገጽታዎችን ያጠቃልላል። ማንነት በባህሪያት ላይ፣ በእርስ በእርስ ግንኙነቶች እና ማህበራዊ መዋቅሮች ላይ የራሱ ተጽእኖ ይኖረዋል። በኢትዮጵያ ሁኔታ ስናይ ማንነት የአንድነትና የመከፋፈል ምንጭ ሆኖ በታሪካዊና በቅርብ ግጭቶች ላይ ትልቅ ሚና ተጫውቷል።

ይህ ምዕራፍ በዋናነት በማንነት ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን አላማውም ማንነት በሰላም ግንባታና ማስፋፋት ሂደት ውስጥ ያለውን ሚና እንዲሁም በአጠቃላይ የማንነት መገለጫ እና በግጭት ውስጥ ያለውን ሚና መለየት ላይ ትኩረት ያደርጋል።

## 2. ማንነትና የማንነት አመሰራረት

*ማንነት ተለዋዋጭ እና ዘርፈ ብዙ ነው። ግለሰብ ወይም ቡድን በተመሳሳይ ጊዜ ብዙ ማንነቶችን ማካተት ይችላል። ማንነትን ወደ ነጠላ ምክንያት ማቅለል የሰውን ልጅ ልምዶች ውስብስብነት ይመለከታል።*

በልጅነታችን ሰዎችን በፍጥነት በተወሰኑ ቡድኖች እንመድባቸዋለን። በዚህ መሰረት የኛ ቡድን የሆነው እና ያልሆነውን እንለያለን። የሚከተሉት ነባራዊ ማሳያዎች ሆን ብለን ወይም በተለያዩ ሁኔታዎች “እኛ እና እነሱ” የሚለው መካከል የመለየት ልማድ አብዛኛው ጊዜ አመለካከቶቻችን የሚቀርጽ እና ከሌሎች ጋር የምንጋራቸው ቅርጾች ይኖሩናል።

- የቤተሰቦቻችን አካል የሆኑ እና ያልሆኑ ይኖራሉ።
- አብረን የምንጫወት ልጆችና አብረን የማንጫወት ልጆች ይኖራሉ።
- ከሰፈራችን የሆኑ ሰዎችና ያልሆኑ ሰዎች ይኖራሉ።
- አንዳንድ ሰዎች ከእኛ እምነት ወይም ሀይማኖት ጋር አንድ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ከሌላ ናቸው።
- አንዳንድ ሰዎች ጎበዝ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ አይደሉም።

*ዝርዝሮቹ ይቀጥላሉ፡-*

አብዛኛውን ጊዜ እነዚህን ቡድኖች በጭንቅላታችን ውስጥ ያለማቋረጥ እንቀርጻቸዋለን፡ - እኛ እና እነሱ እና ሌሎች ሰዎች ሀይማኖቶች፣ ብሔሮች፣ ጎሳዎች እና ቋንቋዎች በዚህ መልኩ በአለማችን ላይ የምንቀርጻቸው ወይም ለመቅረጽ የሚያግዙን ናቸው። ይህ አይነቱ አስተሳሰብ በቀላል መንገድ ይመጣል። የአንዱን ቡድን ማንነት ፍቅር መስጠት ትክክል ነው፤ ሌሎችን ደግሞ በማንነታቸው ምክንያት የምናሳየው ማግለል ውጥረትን ከማንገሱም በላይ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል ግጭቶችን ይቀሰቅሳል። ለምን? ምክንያቱም ከእኛ ወይም ከቡድናችን በጣም የተለዩ ናቸው ብለን ካሰብን ሰዎችን ማጎሳቆል ቀላል ነው።

ነገር ግን መልካም ዜናዎች አሉ። በራሳችን እና በሌሎች ማንነቶች ላይ የበለጠ ትኩረት ካደረግን ከልዩነቶቻችን ይልቅ በጋራ ጉዳዮቻችን የበለጠ ትኩረት እናደርጋለን። በመሆኑም እኛ ከእነርሱ የሚለው አስተሳሰብ መቀበል የለብንም ይልቁንም በጋራ ባሉን የጋራ ጉዳዮቻችን ላይ ትኩረት በማድረግ ብዝኃነታችንን ማዕቀፋችን ውስጥ ማድረግ ይኖርብናል።

**ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይም፡-** ከምንም በላይ ተመሳሳይነቶቻችንን እና እንደ ሰውኛ የምንጋራቸው ነገሮች የበለጠ ትኩረት ሰጥተን ማየት ከቻልን ያሉንን ልዩነቶቻንን እና ብዝሃነቶቻችንን እያደነቅን እና ከምንም በላይ እየተደሰትንበት እያጣጣምን በሰላም አብረን መኖር እንችላለን።



*የሚከተሉትን ግለሰቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት በተከታታይ የውይይት ጥያቄዎች ጋር በማያያዝ ይወያዩበት፡-*

- ግለሰብ ሀ፡- የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ሴት ልጅ የሶፍትዌር ምህንድስና ተማሪ የሆነችው በሰላማዊ ኦንላይን ተግባሯ የምትታወቅ ስትሆን በአፋርና ትግራይ ድንበር አካባቢ ትኖራለች።
- ግለሰብ ለ፡- ወንድ አማርኛ መምህር፣ አፋን ኦሮሞ እና ትግረኛን ጨምሮ በስድስት ቋንቋዎች ከፍተኛ ችሎታ ያለው ነው።
- ግለሰብ ሐ፡- የፓን አፍሪካ ወይም አፍሪካዊያን አንድነት የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች የደሴ ነዋሪ ነው።
- ግለሰብ መ፡- የዩንቨርሲቲ ፕሮፌሰር ከጋምቤላ የመጡ፣ ለ15 ዓመታት በሀረር ኖረዋል።
- ግለሰብ ሠ፡- በአዲስ አበባ ጨርቆስ አካባቢ ተወልዶ ያደገ አማርኛ ቋንቋ ብቻ ይናገራል።
- ግለሰብ ረ፡- ከአዲስ አበባ ቦሌ ሲሆን፣ ግለሰቡ አማርኛ እና ጉራጌኛ ይናገራል።
- ግለሰብ ሰ፡- ከአዲስ አበባ የካ የሆነው አፋን ኦሮሞና አማርኛ አቀላጥፎ ይናገራል።
- ግለሰብ ሸ፡- የጅቡቲ ዲፕሎማት የሆኑት በድሬደዋና ጅቡቲ ከተማ መካከል ይኖራሉ።
- ግለሰብ ቀ፡- በቦሌ መድኃኒያለም ለ20 ዓመታት የኖረ የሶማሌ ስደተኛ ሲሆን አማርኛ መናገር የሚችል።
- ግለሰብ በ፡- በወለጋ ተወልዶ ያደገ ሲሆን በነቀምት ከተማ ይኖራል።
- ግለሰብ ተ፡- በዩኬ ለ35 ዓመታት ሲኖር ቆይቶ ወደ ሀገሩ የተመለሰ ኢትዮጵያዊ ነው።

## የውይይት ነጥቦች

- ከላይ የተዘረዘሩ ግለሰቦች የሚጋሩት እሴቶች ምንድን ናቸው?
- የጋራ መገለጫ ባህሪያት ምንድን ናቸው?
- የበለጠ በተሻለ ራሳቸውን መግለጽ የሚችሉት እንዴት ነው?


**ጉርሻ፡-** *አምስት ደቂቃ ወስደው ስለማንነቶ ያስቡበት እና እንዴት ራስዎን በአንድ አረፍተ ነገር መግለጽ እንደሚችሉ ያስቡ፤ ቅድሚያ የሚያደርጉት የትኞቹን ነው?*

- የማንነት መገለጫዎች ቋሚ ወይስ ተለዋዋጭ ናቸው?
- የአይምሮ ማነቃቂያ ጥያቄዎች፡- ብሔር በተፈጥሮ የተጎናጸፍን ወይም በህይወት ተሞክሮ ያገኘነው የማንነት መገለጫ ነው? ጾታስ?

## 2.1 ማንነት እና ፀዘቱ

ማንነት በርካታ እርስ በርስ የሚገናኙ አካላትን እንደያዘ እንድትረዱ የማህበራዊ ማንነት መገለጫ መሳሪያው  ያግዝዎታል። የምንጋራቸውን የማንነት መገለጫዎች መገንዘብ የበለጠ ግንዛቤ እንድናዳብር እና ከዚህ የሚመነጩ ግጭቶችን ለመቀነስ ይረዳናል።

የማንነት መገለጫ እንደ አንድ ነጠላ ነገር ሳይሆን የተለያዩ በውስጡ የያዛቸው ነገሮች እንዳሉ ካሰብን በብዛት ከሌሎች ጋር ያሉንን ተመሳሳይ ነገሮች በተሻለ መልኩ በቀላሉ ለመለየት እንድንችል የሚረዳ ሲሆን እንዲሁም ከቡድናችን ውጪ ነኝ ብሎ ለሚያስበውም ጨምሮ ተመሳሳይነት ወይም የምንጋራው  ተመሳሳይ ነገሮች እንደሚኖሩን እንድናውቅ ይረዳናል።




*ስዕሉ በክፍሎች የተከፈለ ክብ ያሳያል፣ እያንዳንዱም የማንነታችንን እምቅ ገጽታ ይወክላል። በእርግጥ በርካታ ነገሮች የማንነታችን መገለጫዎች ሲሆኑ ነገር ግን የጋራ መገለጫዎች የሆኑ አንዳንዶች ይኖራሉ።*

*የማህበራዊ ማንነት ሽክርክሪት*

### መልመጃ

- **የግለሰብ አስተያየት፡-** ተሳታፊዎቹ ብሄራቸውን፣ ሃይማኖታቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ ማህበራዊ ሁኔታቸውን፣ እድሜያቸውን እና ፆታቸውን በመጥቀስ የማህበራዊ ማንነት ሽክርክሪቶቻቸውን ያጠናቅቃሉ።
- **የቡድን ውይይት፡-** በትናንሽ ቡድኖች ውስጥ ተሳታፊዎች የትኞቹ አካላት ለማንነታቸው አስፈላጊ እንደሆኑ ያካፍላሉ። እንዲሁም መገለጫዎቻቸውን በብዛት የሚዛመዱትን ወይም የሚመሳሰሉትን ይለያሉ።
- **የማጠናከሪያ ውይይት፡-** በጋራ መለያ ማንነት መገለጫዎች ላይ ትኩረት ማድረግ እንዴት ግለኝነትን እንደሚቀንስ እና ሰላም እንደሚያስፋፋ ይወያዩበት።
- **አእምሮ መፍታታት፡-** የማንነት መገለጫዎች በምንገልጽበት ጊዜ ከግምት መግባት ያለባቸው ምንድን ናቸው?

## 2.2 ተጨማሪ ግብዓቶች

የማንነት መገለጫዎች፣ የግል ማንነት መገለጫ፣ የማህበረሰብ ማንነት መገለጫ፣ ባህል፣ ብሄር፣ ግጭት፣ በተለያዩ ትውልዶች መካከል የሚስተዋሉ ግጭቶች፣ ማህበራዊ ግጭቶች፣ የማንነት ከብሄርተኝነት ጋር መቆራኘት

*Ethnic Identity and Conflict* | *Elements of Identity in Conflict* | *Culture and Conflict*

# 3. ማንነት እና ግጭት

## ታሪክ እና አግባብነት ያለው ትርጓሜ

***ከደርግ መንግስት ውድቀት በኋላ በ1983ዓ.ም የተመሰረተው የኢትዮጵያ የፌደራሊዝም ስርዓት ነው። ምንም እንኳን አግባብነት ያለው መንግስታዊ መዋቅሮች መፍትሄ ለማምጣት እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ወይም ብዙሃን ቋንቋ የሚነገርባት ሃገር በመሆኗ እነዚህን ውስብስብ ሁኔታ ለመቅረፍ እና ግጭቶችን ለመቀነስ ተብሎ የተመሰረተ ነበር።***

ይህ የአስተዳደር ሥርዓት የተፈጠረው ራስን በራስ የመወሰንና ውክልና የሚፈልጉ በብሔር የተደራጁ ቡድኖች ለአስርት ዓመታት የዘለቀውን የፖለቲካ ትግል ተከትሎ ነው። የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የሽግግር ቻርተር (1983) መግቢያ እንደሚለው፣ "የሁሉም ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሕይወት የአስተዳደር መርሆች አንዱ ይሆናል" ይላል።

በመሆኑም አላማው በዚህ መልኩ በሃገሪቷ በስፋት ይስተዋል የነበረውን ጠላትነት ለማክተም እና የብሄሮችን የፖለቲካ ቁስሎችን ለማዳን ወይም ለመጠገን እንዲሁም ሰላምና የተረጋጋ አኗኗር ለማረጋገጥ ነበር።

በኢትዮጵያ ማህበረ-ፖለቲካዊ ገጽታ ላይ የብሄር ፌደራሊዝምን ውጤታማነት እና ተፅእኖ በተመለከተ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ። አንዱ የመከራከሪያ ነጥብ የብሔር ፌደራሊዝም የተለያዩ ብሔረሰቦችን የተወሰኑ አንገብጋቢ ፍላጎቶቻቸውን ማለትም ራስን በራስ የማስተዳደር መብት፣ የባህል፣ የፖለቲካ ውክልና እና ሥልጣንን ያልተማከለ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መንገድ አድርጎ መመልከቱ ነው። ሌሎቹ ደግሞ ብሄርን መሰረት ያደረገ የፌደራሊዝም ስርዓት ከብዙ ነገሮች በተለይ በማንነት መገለጫዎች መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን ሊያስፋፋ እንደሚችል እና በሃገሪቱ ከሚጋሩት በርካታ ተመሳሳይ የማንነት መገለጫዎች ይልቅ በልዩነት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ያነሳሳል በማለት ይከራከራሉ።

አሁን በተጨባጭ በኢትዮጵያ ከሚስተዋለው ግልጽ ነገር በተለያዩ ደረጃዎች በሃገሪቷ ግጭቶች ተስፋፍተው የሚገኙ ከመሆናቸውም አንጻር ግጭቶቹ በግለሰቦች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች፣ በቡድኖች ውስጥ እና በተለያዩ ቡድኖች እንዲሁም በብሄራዊ ደረጃ የሚስተዋሉ ግጭቶች ተንሰራፍተዋል። ለእነዚህ ግጭቶች መነሻ የሆኑ ምክንያቶች በተለይ ለሃብት ውድድር ወይም መቀራመት፣ የአመለካከት ልዩነቶች፣ ታሪካዊ ቅራኔዎች፣ የስልጣን ኢ-ፍትሃዊ ክፍፍል እና ከማንነት ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ስጋቶች ናቸው።

**የበለጠ ለመማር፡-** ፌደራሊዝም ስልጣን በማዕከላዊ ባለስልጣን እና በትናንሽ የክልል መንግስታት መካከል የሚጋሩበት የመንግስት ስርዓት ነው። በመሆኑም የፌደራሊዝም መዋቅራዊ ስርዓት ክልሎች አንዳንድ የራሳቸውን ጉዳዮች በተለይ እንደ የትምህርት ውሳኔዎች ወይም የስራ ቋንቋዎች አስመልክቶ የራሳቸውን አስተዳደራዊ ሃላፊነቶች ወይም ስልጣን እንዲኖራቸው እና የመማሪያ እና የስራ ቋንቋ የራሳቸውን ተጠቅመው የሃገሪቱ አካል ሆነው የሚቀጥሉበት ስርዓት ነው። የፌደራሊዝም ስርዓት የሚከተሉት ሃገራት፡ እንደ አርጀንቲና፤ ካናዳ፣ ጀርመን እና ደቡብ አፍሪካን ያካትታል።

## 3.1 የማንነት ብሄርተኝነት

በርካቶችየብሔር ፌደራሊዝምን መቀበል የብሔር ማንነት ላይ የብሔር ማንነት ላይ የበለጠ ትኩረት እንዲሰጥ አድርጓል ይላሉ፣ ይህ አመለካከት የማንነት ብሔርተኝነት ተብሎ ይጠራል። .

***ይህ በኢትዮጵያ የሚታይባቸው አንዳንድ መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፡-***

- አብዛኛው ወጣቱ ትውልድ በአሁኑ ዘመን ከብሄራዊ ማንነታቸው ይልቅ ለብሄራቸው ማንነት የበለጠ ያደላሉ።
- ብሄር ለብዙ ፖለቲካዊ እና አንዳንድ ማህበራዊ ቡድኖች ዋነኛው መቀስቀሻ እና ማህበር ሆኗል።



## 3.2 ብሄርን መሰረት ያደረገ የፌደራሊዝም ስርዓት እና ግጭት

ምንም እንኳን ብሄር መሰረት አድርጎ የተቋቋመ የፌደራሊዝም ስርዓት የተገለሉ ማህበረሰቦችን አቅም ለማጎልበት እና ግጭቶችን ለመቀነስ ቢሆንም በብዙ መንገዶች ደግሞ በቡድኖች/በብሄሮች መካከል ግጭቶችን የማስፋፋት አስተዋጽኦ አበርክቷል። ***ብሄር መሰረት ያደረገው የፌደራሊዝም ስርዓት ቀጥሎ በተመለከተው ነባራዊ ሁኔታዎች ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለግጭቶች አስተዋጽኦ አድርጓል።***

- ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ጽንፎቹ ጋር የሚያይዝ ሲሆን በሃገራችን ደረጃ ይህ አይነቱ ግጭትም ላለፉት አስርት አመታት በስፋት የተስተዋለ እና በሂደትም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ላይ ጉዳት ያደረሰ እና ለስደት የዳረገ ክስተት ነው፡ ፡ በኢትዮጵያ ከተፈናቀሉት 4.4 ሚሊዮን ሰዎች ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በግጭት ምክንያት ቤታቸውን ለቀው የተሰደዱ ናቸው።
- በመሆኑም ብሄርን መሰረት ያደረገ ፖለቲካ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መጥቷል። በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ዋና ዋና የፖለቲካ ፓርቲዎች በብሄር የተደራጁ ናቸው። ይህ መከፋፈል ደግሞ ህዝቡ እንዳይተማመን እና እርስ በእርሱ እንዲጠራጠር በማድረግ ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ የብሄር ተለዋዋጭ ሁኔታዎች እንዲንሰራፋ አድርጓል።
- በብሄር ትርክት  መሰረት "እኛ እና እነሱ" እየተባለ የሰፋ ልዩነቶች በሂደትም ወደ ከፍተኛ ጽንፈኝነት፣ አድሎ እና አንዳንድ ጊዜ በእርስ በርሳቸው መካከል ወይም በሰፋሪዎቹ መካከል በተለያዩ በርካታ አካባቢዎች የግጭቶች  መስፋፋት እና የፖለቲካ መብቶቻቸውን መንፈግ ታይታል።

**ጠይቅ፡-** በሌላ መንገድ ብሄርን መሰረት ያደረገው የፌደራሊዝም ስርዓት በኢትዮጵያ ለሰላም ወይም ለግጭት አስተዋጾ አድርጓል? ከግል አመለካከቶች በመነሳት በቤት ወይም በትምህርት ቤት ወይም በስራ ቦታ ይህንን ከሌሎች ጋር ይጋሩ።

## 3.3 ማንነት ለግጭት

*የብሔር ማንነት እንደ ባህላዊ ቅርስ፣ ታሪካዊ ልምዶች፣ ዜግነት፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ ወይም ቦታን ያካትታል። በእነዚህ የጋራ ባህሪያት ላይ በመመስረት የአንድን ግለሰብ የአንድ የተወሰነ ጎሳ አባልነት ስሜት ያመላክታል። በኢትዮጵያ ሁኔታ የብሄር ማንነት የህብተ ተደራሽነት፣ የፖለቲካ ውክልና እና ማህበራዊ ደረጃ የሚታይበት ቀዳሚ አመለካከት ሆኗል።* በብሄር ላይ የሚደረገው ከፍተኛ ትኩረት በቡድኖች መካከል የሚደረገውን ውድድር ከፍ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ያላካተተ ግለሰቦችን እንደ "ውስጣዊ ወይም ውጫዊ" ተብለው የሚፈረጁበት አግላይ ተግባራትም አሉት። አንዳንዶቹ የብሄር ግጭት በዚህ ጉዳይ ሊኮነን አይገባም ብለው ይከራከራሉ። ይልቁንም በፖለቲከኞቹ የብሄር ማንነት ከለላ እና ጥላ ስር ያጋነኑት የብሄር ልዩነት ውጤት እንደሆነ ያስረዳሉ። ይህ መዋቅራዊ ማዕቀፍ ለአካባቢያዊ ግጭቶች፣ የድንበር አለመግባባቶች እና በአናሳ ቡድኖች መካከል እየጨመረ ለመጣው መገለል አስተዋፅዖ አድርጓል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ ከማንነት ጋር በተያያዙ ቅሬታዎች የተቀሰቀሱ ጉልህ ግጭቶች ታይተዋል። የታሪክ ትርክቶች፣ የህብት እጥረት ፉክክር እና ብሄር ተኮር የፖለቲካ ቅስቀሳ ውጥረቱን አባብሷል። የማህበራዊ ሚዲያ መስፋፋት እነዚህን ክፍፍሎች የበለጠ አባብሶታል፣ የጥላቻ ንግግሮች እና ግጭቶችን የሚያባብሱ አነቃቂ ንግግሮች በመድረክ ቀርበዋል።

## 3.4 ጭፍን ጥላቻ

*ማህበረሰቦች ብዙውን ጊዜ ከተለያዩ ብሄሮች፣ ሃይማኖቶች እና ባህላዊ ቡድኖች የተዋቀሩ ናቸው።* አንዳንድ ጊዜ፣ እነዚህ ቡድኖች አንድ ላይ የማይጣጣሙ እንደሆኑ ይሰማቸዋል። ለዚህ የሚዳርጉ አብዛኛዎቹ ሁኔታዎች፣ እነዚህ በታሪካዊ ምክንያቶች፣ በቅኝ ግዛት ውርስ ወይም የቅርብ ጊዜ ክስተቶች እንደ ምክንያት ናቸው። በዚህ የተነሳ ውጥረቶች ወደ ግጭቶች ሊያመሩ ይችላሉ።

ብዙውን ጊዜ በማህበረሰቡ ውስጥ በሌላ ቡድን ትኩረት የሚደረግበት የማንነታችን መገለጫዎች አስመልክቶ ግንዛቤ ይኖረናል። ማንነታችን ከሌሎች ጋር በምንኖርበት ጊዜ ከፍተኛ ተግዳሮቶች ወይም ማስፈራሪያዎች ሊያጋልጡን ይችላሉ። እንዲሁም በክልል እና ሃገር አቀፍ ደረጃ ሊያድግ ወይም ሊስፋፋ ይችላል። እኛ የተጣመርነው እና በማህበራዊ የተቆራኘነው በቡድናችን ውስጥ



ባሉት ሰዎች መሰረት እንጂ በሌላ ቡድን እንዳሉ ሰዎች አይደለም። ይህ ባህሪ ለአንድ ሰው ወይም ቡድን አድልዎ፣ ጭፍን ጥላቻ ይባላል።

ጎርደን ኦልፖርት፣ እውቅ የስነ ልቦና ባለሙያ የሆነው፣ ጭፍን ጥላቻን በተከታታይ ከተፈጸመ እጅግ ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል አሳይቷል። እነዚህ እርምጃዎች ደግሞ ከተራ ቀላል እርምጃዎች አንድን ሰው ለማስወገድ፣ ለማግለል፣ አካላዊ ጥቃት እና እንዲሁም ወደ ዘር ማጥፋት ወንጀል ሊያድግ ይችላል።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ወስደን ያየን እንደሆነ በጥቂት አመታት ውስጥ ተራ አድሎ እንዴት ወደ ዘር ማጥፋት ደረጃ እንዳደገ ማየት ይቻላል። በመሆኑም የሚፈጸመውን አድሎ መዘንጋት ወደ ምን ደረጃ ሊያድግ እንደሚችል የሚያስረዳን በመሆኑ እንደ አጋጣሚ የተፈጠሩ ወይም የተከሰቱ አድሎዎችን ወዲያው ጉዳት በማያደርስ መልኩ እንዲፈታ ተገቢ ምላሽ መስጠት ይኖርብናል።


*ጭፍን ጥላቻን በምናስብበት ጊዜ በአእምሯችን የሚመጡ አንዳንድ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፦*

- ጭፍን ጥላቻ በዘልማድ የምንቀበለው ወይም የምንለምደው እንጂ በትምህርት የምንወስደው አይደለም።
- ጭፍን ጥላቻን ለመግታት ተግባራዊ ዘዴ ከቡድኖች ይልቅ በግለሰቦች ላይ ማተኮር እና የጋራ ጉዳዮችን መፈለግ ነው።
- ለራሳቸው ጥሩ ግምት ያላቸው ሰዎች ሌሎች ላይ ጥቃት ማድረስ አይፈልጉም። ስለዚህ ለራሳችን መልካም ቦታ የሰጠን እንደሆነ እና የተሻለ አመለካከት ካለን ለሌሎችም በተመሳሳይ መልኩ የተሻለ እንዲኖራቸው ማሳየት እንችላለን።

## 3.5 የጥላቻ ፒራሚድ

*የጥላቻ ፒራሚድ የሚያሳየው አሉታዊ ባህሪያት ከታች ከመሰረቱ ጀምሮ እስከ ጫፉ ድረስ በተወሳሰበ መልኩ እንዴት እንደሚያድግ የሚያሳይ ነው።* ምንም እንኳን እንደዚህ አይነት አሉታዊ ባህሪያት በእያንዳንዱ ደረጃ በግለሰቦችም ሆነ በቡድኖች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትል ቢሆንም ከጥላቻው ፒራሚድ ወደ ላይ አንድ በሄደ ቁጥር ውጤቱ በከፍተኛ ደረጃ ለህይወት ስጋት ይሆናል።

የፒራሚዱ የላይኛው ደረጃዎች ከስር በሚገኙ ደረጃዎች ይደገፋሉ። ሰዎች ወይም ተቋማት ገና በታችኛው ደረጃ ላይ እያሉ ተገቢ አያያዝ ቢያገኙ ተቀባይነታቸው ወይም እንደመደበኛ ባህሪያት በመውሰድ በሚቀጥሉት ደረጃዎች የበለጠ ተቀባይነታቸው የሚጨመር ይሆናል።




*የጥላቻው ፒራሚድ በተቀበልነው አሉታዊ ባህሪያት ምክንያት ጥፋት እና የዘር ማጥፋት ድርጊቶች እንዴት እንደሚፈጠሩ እና ወደዚያ ደረጃ እንዴት እንደሚያድጉ የሚያሳይ ሲሆን ወደዚያ ደረጃ እንዲያድጉ የሚያደርጋቸው እንደ አድሎ እና መድሎ እንዲሁም ዛቻ እና ማስፈራሪያ በተለይ በታችኛው የፒራሚዱ ደረጃዎች ላይ የተመለከቱትን ጨምሮ የሚያሳይ ነው።*

*የጥላቻ ፒራሚድ*

## ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ጥያቄዎች

ሁላችንም በተወሰነ መልኩ በተለያየ መንገድ እና ሁኔታ በዚህ የጥላቻ ፒራሚድ ተሳታፊመሆናችንን ማወቅ ይገባል። *የበለጠ ታማኝ ማንነታችን በተለይ በቀድሞ ተግባሮቻችን የምናሳየው የበለጠ ታማኝነት ከጥላቻ ይልቅ መልካምነት እና ሰላም ለማስፈን ጥረት ማድረግ። ቀጣይ ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት፡-*

- በተለያዩ ደረጃዎች ምን አይነት ድርጊቶችን እንደፈፀሙ መቀበል ይችላሉ?
- እነሱን ለማካካስ ምን ማድረግ ትችላለህ?
    - *በእነሱ ላይ እንደገና ምንም ላለመፈጸም ቃል ትገባለህ?*
    - *ከዚህ በፊት ጉዳት ያደረስክበትን ሰው ይቅርታ ትጠይቃለህ?*
    - *ሰላም ለመስበክ ወይም ለማስፋፋት ሌላ አማራጭ ምን ማድረግ ይቻላል ብለህ ታስባለህ?*
    - *ያደክበት ባህል እና ሃይማኖት ለአድሎአዊ ባህሪ እንዴት ያለ ተጽእኖ አሳድሯል ብለህ ታስባለህ?*



## 3.6 ከማንነት ምክንያቶች ጋር የተያያዙ - በኢትዮጵያ የሚቀሰቀሱ ግጭቶች

- የሃገር ወይም የመንግስት ሃብቶችን በብሄር የበላይነት የመቆጣጠር ውድድር ብዙውን ግዜ በመሬት፣ በውሃ እና በምጣኔ ሃብት እድሎች ላይ የሚከሰቱ ግጭቶች፤
- ብሄርን ለፖለቲካ ቅስቀሳዎች፣ ዘመቻ አገልግሎት ማዋል - መሪዎች በብሄር ማንነት ተጠቅመው ድጋፍ ማግኘት እና ስልጣናቸውን ማጠናከር፤
- በግዛት ወሰኖች ላይ የሚቀሰቀሱ ግጭቶች አንዳንድ ክልሎች/ማህበረሰቦች በታሪክ ወይም በባህል ትስስር እና ተቃውሞዎች የሚስተዋልባቸው አካባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶች፤
- ከብሄር ጋር የተያያዘ የዜግነት መብቶች በተለይ የማይገቡ መደቦችን ለመፍጠር እና በክልሉ ውስጥ የሚጠቀሙባቸውን እና የማይጠቀሙባቸውን በመፍጠር አብዛኛውን ጊዜ አነሳዎቹን የማግለል ተግባራት፤
- በታሪክ የጥላቻ ቁርሾ ምክንያት ጽንፈኝነት ወደ ግጭቶች ማምራት መሸፈን እና የጎሳዎችን ታሪክ የአተረጓጎም እና አገላለጽ በፖለቲካ ውስጥ ያላቸውን አስፈላጊነት እንደገና መቀረጽ ተጋባራት ናቸው።

**ማስታወሻ፡-** ጥናቶች እንደሚያሳዩት በብሄሮች ጽንፈኝነት የተንሰራፋበት ሃገር ውስጥ፣ የብሄር ታማኝነት እና  ለብሄራቸው ድምጽ እንዲሰጡ፣ ይህም የእምነት ጥላቻ እና የብሄር ጥላቻን በመቀስቀስ ወደ እርስ በእርስ ጦርነት ሊያመራ እንደሚችል አረጋግጠዋል።

### *በጉዳዩ ላይ የተካሄድ ጥናት፡- ማንነትን መሰረት ያደረገ ግጭት*

ኬ፣ ከዩኬ ወደ ሃገሩ ኢትዮጵያ፣ የቀድሞ ጓደኛውን ኤችን ለመጎብኘት ወደ ድሬደዋ ከተማ ተጓዘ። በኤች መኖሪያ አካባቢ በአንድ ቡና መሸጫ ሱቅ ወይም መደብር ቁጭ ብሎ በመጠበቅ ላይ እያለ የፓን አፍሪካ አክቲቪስቱ ኬ ከሲ ጋር ተገናኘ። በያዙት ጨዋታ በወቅቱ የዩኬ መንግስት ህገወጥ ስደተኞችን ወደ ሩዋንዳ ለመመለስ የወጠነውን ፖሊስ ላይ እየተነጋገሩ ጨዋታቸው እየጋለ ሄደ፤ ኬ እና ሲ ሲያወሩ የነበረውን ተቃራኒ ጉዳይ በመያዝ ሲሆን ክርክራቸውም እየጋመ መጣ።

ዶክተር ዲ፣ የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር ወደ ድሬደዋ ለአጭር ጊዜ የስራ ጉዞ ያደረገ በመሆኑ እሱም በቡናው መሸጫ መደብር ውስጥ ነበር። ዶክተሩ ክርክሩን በመስማት ተቀላቀለ፤ በዚህ ጊዜ የተከራከረው የዩኬ መንግስትን በመደገፍ ነበር፤ ኬ ደግሞ የበለጠ ክርክሩን እያከረረ ዶክተር ዲ ላይ አፈጠጠ፣ አሸሟጠጠ፣ አንተ ባሪያ ብሎ (በማይገባ ቃል) ጠራው። በቃል ብቻ የነበረው ግጭታቸው ወዲያው ወደ አካላዊ ድብድብ ተሸጋገረ፤

ኤች በአካባቢው ደርሶ በጉዳዩ ጣልቃ ለመግባት ሙከራ አደረገ፤ ነገር ግን በተፈጠረው ብጥብጥ በዶክተር ዲ በድንገት ተመታ፤ በኤች ላይ የደረሰው ጉዳት ከባድ በመሆኑ ከዚያ ቀን በኋላ ህይወቱ በሆስፒታል አልፏል።

## የውይይት ጥያቄዎች

- *መነሻ ምክንያቶች፦* ለዚህ ግጭት ማባባስ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
- *ጉዳዩዮቹ፦* ማንነት፣ የታሪክ ቁርሾዎች እና የማንነት ልዩነቶች እንዴት ሚና ሊጫወቱ ቻሉ?
- *ተጽእኖ፦* የዚህ ክስተት ቀጥተኛ እና የረዥም ጊዜ ውጤቶች ምንድን ናቸው?
- *የግጭት አያያዝ፦* እርስዎ ኬ፣ ሲ ወይም ዶክተር ዲ ቢሆኑ ጉዳዩን እንዴት ያረግባሉ?
- *የወሰድነው ትምህርት፦* እንደዚህ አይነት ጉዳቶቶች ለወደፊት እንዳይከሰቱ ማህበረሰቡን ለመከላከል ምን አይነት እስትራቴጂዎች መጠቀም ይቻላል?

**የበለጠ ይማሩ፡-** ግጭት ትንተና ማለት የግጭት መገለጫ፣ መንስኤዎች፣ ተዋናዮች እና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ያካተተ ስልታዊ ጥናት ነው። በማንኛውም ጊዜ ማንኛውንም አይነት ግጭት ሲያጋጥመን የግጭቱን አመጣጥ እና ባህሪ መነሻ ምክንያት፣ ተዋናይዎቹም ወዘተ . . . በአግባቡ ሳንረዳ የጣልቃ አገባብ ሁኔታ በፍጥነት መወሰን የለብን።



# 4. ማንነት፣ የሰላም ግንባታ እና እርቅ

## 4.1 ትርጉም ያለው የቡድን ውይይት ሚና

*በተለያዩ ቡድኖች መካከል ስለ ጋራ ጉዳዮች በጋራ መወያየት እና መከላከል በተለይ ደግሞ የተለያየ ሃይማኖት፣ እምነት ወይም የባህል ዳራ ያላቸው ማህበረሰብ መካከል የሚደረገውን ውይይት እና ክርክር የነበሩትን ውጥረቶች ለማርገብ እና ጥርጣሬዎችን ለመቀነስ ይረዳል።*

ትርጉም ያለው በቡድኖች መካከል የሚደረገው ምክክር እና ውይይት ያለመኖር መነጣጠል ወይም መራራቅ በቡድኖች መካከል ውጥረቶች የበለጠ እንዲነግሱ አስተዋጽኦ ያበረክታል። በእነዚህ ሁኔታዎችም ጠላትነትን፣ አድሎዎችን እና የጥላቻ ንግግሮችን እንዲሁም ወደ ጥፋት እና ጥቃቶች ሊሸጋገሩ የሚችሉ በተለይ ደግሞ በእውነተኛው ቡድኖች መካከል ውጥረቶች የሚያስነሱ ታሪካዊ እውነታዎች ካሉ የበለጠ እንዲከር ያደርጋሉ።

### መሳምታዊ ታሪክ

የሚከተለውን ታሪክ ያንብቡ እና ግድፈቶቹን የሚያስገኘው የውይይት ውጤት ላይ ይወያዩ፤

ከግጭት በኋላ በተወሰነ ማህበራዊ አውድ ውስጥ፣ የወጣቶች ቡድን በሰላም ክለባቸው በኩል የማህበረሰብ ውይይት አዘጋጅቷል። ክበቡ ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ግጭት በመካከላቸው የተፈጸመ ያህል በመቁጠር ከእያንዳንቸው ተወካዮች እንዲሳተፉ ጋብዟል። የተጋበዙ ተሳታፊዎች በሙሉ ከመጠን በላይ ከመናደዳቸው የተነሳ ወደ ውይይቱ የገቡት የጉዳዩ ሰለባ ስለመሆናቸው እና የተፈጸመባቸው ኢ-ፍትሃዊ ተግባራት አስቀድሞ ስሜታቸውን ለመግለጽ እና እንዲሁም በውይይቱ ክፍል ውስጥ በነበረው ሌላ ቡድን ላይ ክስ ለማቅረብ ነበር።በቡድኑ ተግባር እና ተሳትፎ ምክንያት የደረሰውን ያስተዋሉትን የጥቃት ተግባራት መሆኑን አስምረውበታል። አንዳቸውም የአቻቸውን ልምድ ለማዳመጥም ሆነ ለመስማት ዝግጁ አልነበሩም። ተሳታፊዎቹ ለሙሉ ቀን ሳይደማመጡ ሲጯጩ ውለዋል። መድረኩ በሌሎች ተሳታፊዎች ባህሪ እና የቃል እና የቃል ያልሆኑ ግንኙነቶችን በመጠቀም ተሳታፊዎችን ቀስቅሷል። የመጀመሪያው ቀን የውይይቱ ክፍለ ጊዜ በዚህ አይነት መልኩ ተጠናቀቀ።

**ጥያቄ፡-** እውነተኛ ውይይት ወይም ምክክር የተደረገ ይመስላችኋል? ካልሆነ ችግሩ ምን ነበር? በጥንድ ተወያዩ እና ሀሳብዎን ያካፍሉ።

**ምክክር ወይም ውይይት ውጥረትን ለማርገብ ይረዳል።**

ምክክር ወይም ውይይት ውጤታማ ለመሆን ከምሳሌያዊ ይልቅ ለእውነተኛ አመለካከት ቦታ ቦታ መስጠት አለበት። እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ በልዩነቶች ላይም ሆነ ያልተስማሙባቸው ነጥቦች ላይ መወያየት እንዲችሉ እድል ሊፈጠር ይገባል። ምክክር ከባህላዊ መሪዎች ተጨማሪ የማህበረሰብ ውክልና እንዲኖር የሚያስችል አካታች መሆን አለበት። የሴቶችን፣ የልጃገረዶችን፣ የወጣቶችን እና የተፈናቀሉ/አናሳ ማህበረሰቦችን ድምጽ ወደ ግንባር ማምጣት አስፈላጊ ነው።

**ምክክር እና የእርቅ ድርድር**

አስተማማኝ የሆነ አካታች የምክክር መድረክ ፣ የእርቅ ሂደትን እንዲመቻች የሚያስችል ሲሆን ይህም ዳግም ግንኙነት እንዲገነባ፣ የጋራ መግባባት እንዲፈጠር፣ ፣ ቀደም ብሎ የተፈጸመ ኢ-ፍትሃዊ ተግባር እና የነበረ ጉዳት እንዲፈታ እና የሚጋሩት ራዕይ እንዲፈጠር ያደርጋል።

### ከግምት ውስጥ መግባት የሚገባቸው ጥያቄዎች

- ከዚህ በፊት በቡድኖች መካከል በተካሄዱ ምክክሮች ላይ ተሳትፈው ያውቃሉ?
- የተለያዩ ቡድኖች ትርጉም ባለው ውይይት ላይ እንዲሳተፉ እና ለሰላም ግንባታ እንዴት ድጋፍ ማድረግ እንደሚችሉ አስመልክቶ ለመስራት አስበህ ታውቃለህ?
- በቡድኖች መካከል በሚካሄደው ምክክር አስመልክቶ አነስተኛ መውሰድ ያለብህ ትንሹ እርምጃ ምንድነው?
    - *ከቡድኑ ውጭ ያለው ግለሰብ በግል ደረጃ መነጋገር ለመጀመር አንድም ሰው አናግረህ ታውቃለህ?*
    - *ሰዎች በብዛት የሚሰበሰቡበት ትምህርት ቤት ወይም ቤተክርስቲያን ህዝቡን በጋራ ለማወያየት ፕሮግራም መጀመር ትችላለህ?*
    - *ግልጽ ምክክር መድረክ ለማስፋፋት ሊረዱ ይችላሉ ብለህ የምታስባቸው ሌሎች ሃሳቦች ምንድን ናቸው?*
- ሰዎች ደህንነቱ አስተማማኝ፣ በአክብሮት እና በነጻነት የሚናገሩበት ቦታ ማዘጋጀት ለምን አስፈላገ?



**ማን በምክክር ውስጥ መሳተፍ ይኖርበታል?**

ለምክክር ቀስቃሽ ወይም አዘጋጅ ከሚያስፈልጉት መሰረታዊ መመሪያዎች አንዱ አካታችነቱ ነው። ስኬታማ ለመሆን በግጭት (ለምሳሌ፣ የታጠቁ ቡድኖች፣ ተቋማት እና ግለሰቦች) ፍላጎታቸውን፣ ግባቸውን፣ አቅማቸውን እና ግንኙነታቸውን ጨምሮ ሁሉም በግጭት የተሳተፉ እና የተጎዱት ወደ ውይይት ጠረጴዛው መጋበዝ አለባቸው። በምክክር ሂደት ውስጥ ተዋናይዎች የማህበረሰብ መሪዎች፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ሴቶች፣ የክልል መንግስት መዋቅሮች፣ የታጠቁ ቡድኖች እና ወጣቶችን ያካተተ ሊሆን ይገባል።

## 4.2 የማህበረሰብ መሪዎች ሚና

የማህበረሰብ እና የሃይማኖት መሪዎች በሌሎች ህይወት እና ስብእና ላይ ተጽእኖ የማድረግ አቅም አላቸው። ሲናገሩም መልእክቶቻቸው ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ለዚህም ነው መሪዎች የጥላቻ ንግግርን እና ሁከትን በመቃወም ወሳኝ ሚና የሚጫወቱት።

***የስኬት ታሪክ፦ የብሄር ጥቃትን ለመከላከል የሽማግሌዎች ሚና***



በቅርቡ በኢትዮጵያ የተፈጸመው የተሳካ የጋሞ አባቶች የእርቅ መንገድ አንድ ምሳሌ ነው። በአርባ ምንጭ በተንሰራፋው ብሄርተኮር ውጥረት ጋር ተያይዞ የኦሮሞ ሱቆች እና ንብረቶች ላይ ጥቃት ሊሰነዘር ነበር። ይህም የተከሰተው በቡራዩ በመስከረም 7/2011 በጋሞ ተወላጆች ላይ እንዲሁም በኦሮሞ እና ሌሎች ብሄሮች ላይ በተፈጸመው ግድያ ለመበቀል በማሰብ ነው።

የጋሞ ጎፋ አባቶች በተሳካ መልኩ ለበቀል የመጡትን ወጣቶች ማስቆም ችለዋል። ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት በኦሮሚያ ክልል ስር የምትገኘው ቡራዩ ከተማ በእንደዚህ ዓይነት ግጭቶች የተነሳ በርካቶች ቀያቸውን ለቀው እንዲወጡ ተገደዋል። ከዚህም የተነሳ በምዕራብ ኢትዮጵያ በሚገኘው ጋሞ ዞን የአርባ ምንጭ ከተማ ወጣቶች በቡራዩ በብሄራቸው የተፈጸመውን ጥቃት ለመቀበል ተደራጅተው በአርባ ምንጭ ውስጥ በሚኖሩ የኦሮሞ ተወላጆች በተያዙ ንብረቶችን ለማጥቃት በተነሱበት ጊዜ የጋሞ አባቶች እርጥብ የታጨደ ሳር በእጃቸው ይዘው ከተቃዋሚዎቹ ወጣቶች ፊት ተንበርክከው ወጣቶቹ የኦሮሞ ንብረቶችን እንዳያጠቁ የለመኗቸው ሲሆን ከዚህም የተናሳ የጋሞ አባቶች በኦሮሞ ብሄር ንብረት ላይ ሊደርስ የነበረውን ውድመት አስቀርተዋል። በርካታ ኢትዮጵያዊያን በጋሞ አባቶች ጥበብ ተደንቀዋል እንዲሁም እንደ ከፍተኛ ስኬት ተጠቅሰዋል። (ዩኔስኮ 2020)

- የሰላም፣ የመቻቻል፣ የመከባበር፣ የጋራ መከባበር እና ተቀባይነት ያላቸው መልክቶችን ማስተላለፍ ወይም ማሰራጨት፣
- በማህበረሰብ መካከል የሰፈኑ ውጥረቶችን ለማርገብ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ለመውሰድ በተለይ ደግሞ የምክክር መድረኮችን በማስፋፋት የተለያዩ የሰላም እና በሰላም አብሮ መኖር የሚያበረታቱ እና የሚያስፋፉ ተግባራት ማከናወን፣
- አዎንታዊ ይዘት ያላቸው መልክቶችን በኦንላይንም ሆነ በተለያዩ መንገዶች ማስተላለፍ ወይም ማሰራጨት፤ በሚቻልበት ጊዜ ደግሞ እነዚህን የሰላማዊ እና አዎንታዊ መልዕክቶችን ያዘሉ በአከባቢው ቋንቋ እንዲሁም የየአከባቢውን ዘዬ በመጠቀም ማሰራጨት፣
- ሀይማኖታዊ፣ ማህበረሰብ እና የብሔር መግለጫዎችን ሪፖርቶች አዘጋጅቶ በተለያዩ የማህበረሰብ መሪዎችና ስልጣን ባላቸው አካላት ማስተዋወቅ እና/ወይም አማራጭ መልዕክቶችን ማሰራጨት፣
- ወጣቶችን ማሳተፍ እና አግባብነት ባለው መልካም ተግባር እንዲጠቀሙ እንዲሁም ኢ-ፍትሃዊ የሆነ ተግባር በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ማድረግ፣
- የወጣቶችን ቅሬታ ትኩረት ሰጥቶ መስማትና ተገቢ ምላሽ መስጠት እንዲሁም ስሜታዊ ሆኖ ወይም እጅግ በጣም አስደንጋጭ የሆኑ ቃላትን በመጠቀም ሲናገሩም ትኩረት ሰጥቶ በመስማት አዎንታዊ ምላሽ መስጠት፣
- አክራሪነትን እና ኃይለኛ ጽንፈኝነትን ለመከላከል "የወጣቶች አምባሳደሮችን መለየት እና ማሰልጠን።



## 4.3 የፖሊሲ ሀሳቦች/አስተያየቶች

- **ትምህርት፡-** የኢትዮጵያ ብዝኃ እና ህብረ ብሔር ቱባ ባህሎችን እና በጋራ የምንጋራቸው ታሪካዊ ማንነቶችን  በመልካም ገጽታ በማስተዋወቅ ግንዛቤን ማዳበር።
- **ምክክር መድረኮች/ዝግጅቶች፡-** የተለያዩ ቡድኖች አስፈላጊ የሆኑትን ምክክሮች እንዲያደርጉና መልካም ግንዛቤ እንዲኖራቸው የጋራ ምክክር ቦታ ወይም እድል መፍጠር።
- **የጥላቻ ንግግር ህጎች፡-** የጥላቻ ንግግርን እና መድሎዎችን በተመለከተ ተገቢ እርምጃ መውሰድ የሚያስችሉ ተፈጻሚነት ያላቸው ህጎችን ማጠናከር።
- **የቴክኖሎጂ ቅንጅት፡-** የግጭት የግጭቶችን መንስኤዎችን ለይቶ በማወቅ ለመቅረፍ እና ተገቢ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችሉ የተለያዩ ዲጂታል መሳሪያዎችን አገልግሎት ማስፋት።
- **ባህላዊ ዘዴዎች/ስልቶችን መደገፍ፡-** በተለምዶ ግጭቶችን ለመቅረፍና ተገቢ መፍትሄዎችን ለማጎናጸፍ የሚያስችሉ ባህላዊ ስርዓቶችን ማጠናከርና ማዘመን ናቸው።

# 02

# ሚዲያ እና የመረጃዎች መዘባት



# በግጭት ውስጥ የመገናኛ ብዙሃን አስተዋፅኦ መረዳት



ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቅን በኋላ ሚዲያ የሰውን አመለካከትና አስተሳሰብ አስመልክቶ በተለይ ከሰላም ግንባታና ግጭት ማስፋፋት ጋር ተያይዞ በሀገራችን ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳድርብን የምንረዳ ይሆናል። እንዲሁም በልማዳዊ እና አዳዲስ ሚዲያዎች መካከል ያለውን ልዩነት የምንማር ሲሆን በዚህ ክፍል ስለ ሚዲያ እና የመረጃ እውቀት በተለይ ከሚዲያ ይዘት ኃላፊነት አንጻር ተገቢ ተደራሽነት፣ ትንተና እንዲሁም አስፈላጊ ክህሎቶችን መፍጠር መቻል ተገቢ ክህሎቶችን ማንጸባረቅ እንድንችል ይረዳናል። ምዕራፉ በይበልጥ የጥላቻ ንግግር ተጽእኖዎች እና አደገኛ ንግግሮችን በመመርመር የጥላቻ ንግግር ማዕቀፎች እና የኢትዮጵያ የህግ ምላሽ በተመለከተ ተገቢ ግንዛቤን ይሰጠናል። የተለያዩ የመረጃዎች መዛባት፣ የመረጃዎች ግድፈት፣ መረጃዎችን ያለአግባብ መረዳት እንዲሁም የመረጃዎችን እጥረት በትክክለኛ ተጫባጭ መረጃዎች መለየት በመቻል ማወቅ እና አልፎም ደግሞ እነዚህ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በአግባቡ መቃወም፣ በጥልቅ አስተሳሰብ እና በአከባቢው የሚገኙ መሳሪያዎችን ተጠቅመህ መከላከል የምትችልበት አጋጣሚዎች ይኖሩሃል። በአጠቃላይ በዚህ እውቀት ጎጂ የሆኑ ትርክቶችን፣ መረጃዎችን ለመቃወም እና ለመከላከል የሚረዳ ሲሆን ከዚህ ጎን ለጎን ሁሉንም አካታች የሆነ የምክክር መድረኮች በመፍጠር የበለጠ ተገቢ መረጃ እንዲኖርህ እና ሰላማዊ ማህበረሰብ ለመገንባት አስተዋጽኦ ያበረክትልሀል።

## ፀዘት


34 ሚዲያ እና የመረጃ እውቀት
38 የጥላቻ ንግግር እና የጥላቻ ንግግርን መቃወም
45 የተሳሳተ መረጃ እና የማረጋገጫ እውነታዎች



*ቀደም ብሎ በቀረበው ምዕራፍ ስለ ማንነት ጽንሰ ሀሳብ መርምረን እና አጥንተን ነበር። በዚህ ጊዜም ማንነት እንዴት እንደሚቀረጽ እና እንዴት እንደሚገነባ እንዲሁም ልምዳችን እና አመለካከታችን በውስጣዊም ሆነ በውጫዊ ማንነት ጉዳይ ላይ እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ አይተናል።*



# 1. መግቢያ

## 1.1 ሚዳየ ምንድን ነው?

*በአጠቃላይ ሚዲያ ማለት የመረጃ ማስተላለፊያ፣ የግንኙነት መረብ ወይም መሳሪያ ሲሆን መረጃዎችን ወይም ዳታዎችን ለማከማቸት እና ለማሰራጨት የሚረዳ ነው።*



ሚዲያ ማለት የመጀመሪያ ደረጃ ህዝባዊ መገናኛ ዘዴ ነው። የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እንደ ኢንተርኔት፣ ህትመቶች እና ሚዲያዎች የህዝብ መረጃ የማሰራጫ ዘዴዎች ናቸው። እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቭዥን፣ ጋጤቶች፣ መጽሄቶች፣ ኢንተርኔት የመገናኛ ዘዴዎች በቀላሉ የመረጃ መለዋወጫሚዲያ ሲሆኑ ሰፊውን ህዝብ የሚያዳርሱ ወይም ተጽእኖ የሚያሳድሩ ናቸው።

## 1.2 መደበኛ ወፀም ነባር እና አዳዲስ ሚዳየ ተቃርኖ

**መደበኛ/ነባር ሚዲያ** የምንለ ሰዎችን ወይም ህዝብን እንደ መገናኛ መሳሪያ ሆነው ለበርካታ አመታት አገልግሎት ላይ የነበሩትን እንደ የህትመት ጋዜጦችን፣ ቴሌቭዥን፣ ሬዲዮ እና መጻፍትን የሚያካትት የመገናኛ ብዙሀን ማለት ነው። ለዘመናት እነዚህ የመገናኛ ዘዴዎች ብቸኛ የብዙሀን መረጃ ምንጩችና መዝናኛዎች ሆነው ሲያገለግሉ ነበር። በኢትዮጵያ የእነዚህ የተለመዱ ሚዲያዎች እንደምሳሌ ሸገር ኤፍ ሬዲዮ፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን፣ ኢቲቪን ጨምሮ) እና የሪፖርተር ጋዜጣ መጥቀስ ይቻላል።

**አዳዲስ ሚዲያ** የሚባሉት ደግሞ ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎች እና ቴክኖሎጂዎች ሲሆኑ እነዚህም ኢንተርኔት፣ ማህበራዊ ሚዲያ፣ የሞባይል ስልኮች፣ ቨርቹዋል ሪያሊቲ፣ እና ሌሎች ዲጂታል ዘዴዎችን ያካትታል። ይህ አዲስ ሚዲያ ስልት የሚዲያውን ገጽታ በከፍተኛ ሁኔታ ለውጦታል፣ እንዴት እንደምንጠቀም እና ከይዘት ጋር መስተጋብር መፍጠር ችሏል።አንዳንድ የአዲስ ሚዲያ ማሰራጫ ዘዴዎች ለምሳሌ በኢትዮጵያ እንደ ቲክቫህ- ኢትዮጵያ (ቴሌግራም መሰረት ያደረገ አዲስ የሚዲያ ዘዴ)፣ ድሬ ቲዩብ (ፌስቡክ መሰረት ያደረገ አዲስ የሚዲያ ዘዴ) እና የኢትዮጵያ ኢንሳይደር (አዲስ ዌብሳይቶች) መጥቀስ ይቻላል።

| **የተለመዱ ሚዲያዎች ገጽታ** | **የአዲስ ሚዲያዎች ገጽታ** |
|---|---|
| - የአንድ አቅጣጫ ብዙሀን ግንኙነት<br>- ውስን ግንኙነት<br>- አካላዊ ገጽታ<br>- በመርህ ግብር ማሳራጫ ላይ የተመሰረተ<br>- የተወሰነ አካባቢ ብቻ የሚወስን<br>- የዝግጅት ወጪዎች<br>- ሙያዊ- መግቢያ ጠባቂ<br>- ዘላቂነት እና ቋሚነት<br>- ውስን ትንተና<br>- አፍላይን ግብዓት | - ብዙሀንን በአንዴ የሚያገናኝ<br>- ተደራሽነት<br>- ግሎባል ተደራሽነት<br>- የበርካታ ሚዲያዎች ቅንጅት<br>- በጊዜ እና ሰአት ተደራሽነት<br>- ተጠቃሚው በኩሉን ግብረ መልስ የሚሰጥበት<br>- ግላዊነት<br>- በማንኛውም ጊዜ ማንኛውም መገራት የሚችል<br>- ወጥ ለውጦች<br>- ምናባዊ እና እውነተኛ ዓለምን ማቀናጀት |

ለማጠቃለል ያህል መደበኛ ወይም ነባር የሚዲያ ዘዴዎች በጣቢያዎቻቸው ላይ ስልጣን ባለው ዘገባ የህዝብን አመለካከት እና ፖሊሲ ይመራሉ። በአንጻሩ፣ አዲስ የሚዲያ ዘዴዎች ደግሞ በርካታ ድምጾችን በአንድ ጊዜ ለብዙሀን ማዳረስ የሚችሉ እና በትክክለኛ ሰአት ትክክለኛ መረጃ በፍጥነት የሚያዳርሱ የህዝቡን አስተያየት እና ውሳኔ ላይ በፍጥነት ተጽእኖ የሚያስከትሉ ናቸው። አጠቃላይ የማህበረሰቡን አስተያየት እና ማጠቃለያ ላይ አንድ ላይ ተደጋግፈው አስፈላጊውን ሚና የሚጋሩ ሲሆን የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

## የውይይት ጥያቄዎች

- ከላይ ከተዘረዘሩት የሚዲያ ዘዴዎች ውጪ ሌላ የምታውቀው የሚዲያ አይነት ምንድን ነው?
- መረጃዎችን ለማግኘት አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙት ምን አይነት ሚዲያ ነው? እና ሚዲያውን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያምኑ ወይም እንዲጠቀሙ አስተዋጽኦ ያሳደሩብህ ነገሮች ምንድን ናቸው?
    - *ጠይቅ፡- ማስታወሻ ለመያዝ 5 ደቂቃ ወስደው ካሰቡበት በኋላ ሚዲያውን እንዲያምኑት/እንዲጠቀሙት ያነሳሱትን ነገሮች ይዘርዝሩ*
    - *ተአማኒነት እና ትክክለኛነት፣ ግልጸኝነት እና አላማ ተኮር መሆኑ፣ እውቅናው ተደራሽነት፣ ፖለቲካዊ ወይም ጽንሰ ሀሳባዊ፣ አሳታፊነት እና ይዘት፣ የአቻ ተጽእኖ*
- አንዳንድ የተለመዱ ሚዲያዎች ምሳሌዎች ምንድን ናቸው?
    - *የተለመዱ ሚዲያዎች የምንላቸው ጋዜጦችን፣ መጽሄቶችን፣ ራዲዮ፣ ቴሌቭዥን የሚያካትቱ ናቸው፤*
- የአዲስ ሚዲያ ምንድን ነው? ከተለመደ ሚዲያ የሚለይበት እንዴት ነው?
    - *ጉርሻ፡- ሰዎች በዜና እና መረጃዎች እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው አዳዲስ ሚዲያዎች እንዴት ለውጥ አደረጉባቸው?*

## 1.3 ኢንተርኔት እና ማህበራዊ ሚዳያ

**ኢንተርኔት ምንድን ነው?**

ኢንተርኔት የግሎባል መረጃ መረብ ሲሆን ቲሲፒ/አይፒ (ትራንስሚሽን ኮንትሮል ፕሮቶኮል/ኢንተርኔት ፕሮቶኮል) የተባለውን የተለመደ ቋንቋ በመጠቀም ኮምፒውተሮችን የሚገናኝ ግሎባል ኔትዎርክ ነው። ይህ ግንኙነት ደግሞ መረጃዎች/ዳታዎች በፖኬቶች፣ በተዘጋጀው የመረጃ መስመሮች በቀላሉ እንዲተላለፍ እና በተጠቃሚዎች ዘንድ እንዲደርስ የሚያስችል ነው። የተለያዩ አገልግሎቶች እንደ ኢሜይል፣ ሶሻል ሚዲያ እና ወርልድ ዋይድ ዌብ/መረጃ መረብ የሚደግፉ ናቸው። ኢንተርኔት የሰፊው መረጃ መረቦች መረጃ መረብ ሲሆን ወርልድ ዋይድ ዌብ/መረጃ መረብ (ወይም በቀላሉ ዌብ) ተብሎ ሚጠራው ደግሞ ገጾችን እና ሰነዶችን በኢንርኔት ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የሚያገናኝ መስመር ወይም ስርዓት ነው።

**WWW**/ወርልድ ዋይድ ዌብ/ ደግሞ የኢንተርኔት ሰርቨር መስመር ሲሆን በሰነዶች መካከል ግንኙነት በቀላሉ በማሰስ እንዲፈጠር የሚረዳ ነው። ኢንተርኔት ሰፋ ያለ ኔትዎርክ/መረጃ መረብ ሲሆን ወርልድ ዋይድ ዌብ ደግሞ መረጃ ተደራሽ ለማድረግ የሚረዳ የመረጃ የግንኙነት ዘዴ ነው።

**የኢንተርኔት ባለቤት ማነው?**

**ማጋለጥ፡-** "ኢንተርኔት በአንድ የተደራጀ ማዕከል ንብረትነት የተያዘ ነው" የሚለው መግለጫ እውነት ወይም ውሸት መሆኑን ተሳታፊዎችን ጠይቅ

በአጠቃላይ በግል ኢንተርኔትን የያዘ የለም። ማንንም ያላማከለ የመረጃ መረብ/ኔትዎርክ ነው። የተለያዩ ድርጅቶችና የንግድ ተቋማት የራሳቸውን ኢንተርኔት የያዙ ሲሆን ሁሉም ግን አንድ ላይ ተያይዘው ኢንተርኔትን ይፈጥራሉ። በመሆኑም በአንድ ተጨባጭ ድርጅት የተያዘ መሰረተ ልማት ሳይሆን አጠቃላይ የኢንፍራስትራክቸር ወይም የመሰረተ ልማት ጽንሰ ሀሳብ የያዘ ነው።

**ማህበራዊ ሚዲያ ምንድን ነው?**

ሶሻል ሚዲያ ማለት በኢንተርኔት አማካኝነት በተጠቃሚዎች እና በሰፊው ማህበረሰብ መካከል የኦንላየን ግንኙነት የሚያቀላጥፍ የብዙሀን መገናኛ መሳሪያ ነው። ከ1990ዎቹ ጀምሮ የማህበራዊ ሚዲያ ዘዴዎች በከፍተኛ ደረጃ የሰዎችን የእርስ በእርስ ግንኙነት እና መገናኛዎችን አዳብረዋል። የማህበራዊ ሚዲያ ዘዴዎች ተሳትፎዎችንና ግንኙነቶችን መፍቀድ ይኖርበታል። ዋና ዋናዎቹ የማህበራዊ ሚዲያ ዘዴዎች በ2025 አገልግሎት ላይ የሚገኙት የማህበራዊ ሚዲያ ዘዴዎች፡- ***ፌስቡክ፣ ዩቱብ፣ ኢንስታግራም፣ ዋትሳፕ፣ ቲክቶክ፣ ዊቻት፣ ቴሌግራም*** እና ***ስናፕቻት*** ናቸው።

**የማህበራዊ ሚዲያ ተግባራት፡-**

ሶሻል ሚዲያ መተግበሪያዎች የተጠቃሚዎችን ይዘት መፍጠርና መረጃ መለዋወጥ ያስችላሉ። እንዲሁም እንደ እርሶና እንደ እኔ ያለን ተጠቃሚዎች አዘጋጅተን እንድንጠቀምበት እንዲሁም እንድንመካከርበት የምክክር መድረኮችን በማመቻቸት በተገቢው ጊዜ ያለ ቦታ ልዩነትና ተጽእኖ ተገናኝተን አስፈላጊውን መረጃ እንድንለዋወጥ ያስችለናል።

የማህበራዊ አውታረ መረብ ጣቢያዎች ለግለሰቦች ያላቸው አገልግሎት፡-

- የተለያዩ ግለሰቦች ወይም ህዝብ ተገቢውን ህዝባዊ ወይም በከፊል ህዝባዊ መገለጫ መገንባት እንዲችሉ፤
- የመገናኛ ዝርዝርን ማስተካከል እንዲችሉ፤
- ግንኙነቶቻቸውን ማየትና አስተያየት መስጠት ማቋረጥ እንዲችሉ ይረዳቸዋል፤

በብዙ ሀገራት የማህበራዊ ዘዴዎች እንደ ፌስቡክ አይነት ያሉ ከተለመዱ ሚዲያዎች የበለጠ የመረጃ ምንጮች እያገለገሉ ነው። የተለያዩ የሚዲያ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን በማጣመር የተዋሃዱ መድረኮች ናቸው፣ ይህም ከዋና ሚዲያዎች ተመራጭ ያደርጋቸዋል።



**የበለጠ ለመረዳት፡-** "የዜግነት ጋዜጠኛ" የሚለው ቃል የመደበኛ ሰዎችን ሪፖርት እና ዜና በመስመር የመረጃ መረብ እና ማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት ያሰራጫል። እንዲሁም ስለ ወቅታዊነት እና ተአማኒነታቸው ዘርፈ ብዙ አመለካከቶች እና አፋጣኝ ቀጥተኛ ሽፋን አገልግሎት በማቅረብ ያረጋግጣል። ለምሳሌ የቲክቶክ ተጽእኖ ፈጣሪ ከመሬት ላይ ለበርካታ ጉዳዮች ሽፋን ይሰጣል።

**በማህበረሰቡ ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ፡-**

ማህበራዊ ሚዲያ በማህበረሰብ ላይ አሉታዊና አዎንታዊ ተጽእኖ ሊያስከትል ይችላል። ዋና ዋና ተጽእኖዎቹም፡-

- ግንኙነት መጨመር፡- ማህበራዊ ሚዲያ ሰዎች ምንም ርቀት ይሁን ምን ከጓደኛ እና ቤተሰብ ጋር እንዲገናኙ ይረዳል።
- መረጃዎችን መጋራት፡- ዜናዎችን እና መረጃዎችን በከፍተኛ ፍጥነት ያሰራጫሉ።
- ማህበረሰብ ግንባታ፡- ተጠቃሚዎች ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር አስፈላጊ የሆኑትን የጋራ ፍላጎቶች ወይም ምክንያቶች መፍጠር እንዲችሉ እና በኦላይን እንዲገናኙ ይረዳቸዋል።
- ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች፡- ከፍተኛ ንቃተ ህሊና እና እንቅስቃሴዎችን በማበረታታት ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን ያጎላሉ።
- የምጣኔ ሃብት እድሎችን ፡- ለአዳዲስ አድማጮች እና ተመልካቾች አዳዲስ የምጣኔ ሃብት፣ የስራ፣ የስራ ፈጠራ ና ገበያ ይፈጥራል።
- የአእምሮ ጤንነት ውጤቶች፡- በአእምሮ ጤና ላይ የራሱ የሆነ ተጽእና ሊያስከትል የሚችል ሲሆን ወደ ድብርት፣ ሱስ፣ መደበት እና በራስ መተማመን ማጣት ሊያመራ የሚችል ሲሆን በተለያዩ እንደ ራስን ማነጻጸር እና በሳይበር ማስፈራሪያዎች አሉታዊ ተጽእኖ ሊያስከትል ይችላል።
- የግል ጉዳዮች፡- ስለ መረጃ ደህንነት እና የግል ጉዳዮች በተመለከተ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል።
- የተሳሳቱ መረጃዎች ማሰራጨት፡- የተሳሳቱ መረጃዎች በፍጥነት በህዝቡ ዘንድ እንዲደርሱ ሊያድረግ ይችላል።
- የባህል ልውውጥ፡- በግሎባል ደረጃ ባህላዊ ሃሳቦችን እና ልማዶችን መለዋወጥ ያስችላል።

### የውይይት ጥያቄዎች

- ኢንተርኔት ለምን ዓላማ ትጠቀማለህ?
  - *ኢንተርኔት ዜና ለማንበብ እና የወቅቱን ሁኔታዎች፣ ትኩስ መረጃዎች እንዲኖረኝ እጠቀማለሁ።*
  - *ለትምህርት ዓላማ  ሲሆን ኦላይን የሚሰጡ ትምህርቶችን ለመከታተል፣ ለምርምር ወይም ለአጋዥ ትምህርቶች እጠቀማለሁ።*
  - *ከቤተሰብ እና ከጓደኛ ጋር በኢሜል፣ በመልእክት መላላኪያ መተግበሪያዎች እና በቪዲዮ ጥሪዎች ለመገናኘት እጠቀማለሁ።*
  - *ለመዝናኛ፤ ሙዚቃ ለመስማት፣ ቪዲዮ ለማየት ወይም ኦላይን ጌሞችን ለመጫወት እጠቀማለሁ።*
  - *ለስራ፣ ለንግድ አገልግሎቶች እና ግብይቶች እንዲሁም ለርቀትና ለትርፍ ጊዜ ስራዎች እጠቀማለሁ።*
  - *ጉርሻ፡- ተሳታፊዎቹን በተለያዩ ቡድኖች ይከፋፍሉ ለእያንዳቸው የተለያዩ አላማዎች (ለምሳሌ፡- ትምህርት፣ ንግድ ስራ፣ መዝናኛ) በመስጠት ይመድቡ። በእነዚህ ዙሪያ ኢንተርኔት መጠቀም ያለው ጥቅሞች እና ስጋቶች ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ።*
- የማህበራዊ ሚዲያ የግል አድራሻዎ ምን አይነት የሶሻል ሚዲያ ነው?
  - *መጠየቅ፡- ተሳታፊዎች የሚጠቀሙትን የማህበራዊ ሚዲያ ዜዴዎች እንዲዘረዝሩ ጠይቋቸው። እንደ አገልግሎታቸውም በቡድን በቡድን  (ለምሳሌ፡- ለኔትወርኪንግ፣ ለዜና፣ ለመዝናኛ፣ ለአክቲቪዝም) አከፋፍላቸው።*

# 2. ሚዲያ እና የመረጃ እውቀት

***ላለፉቱ ጥቂት አስርት አመታት የእውቀት ግንዛቤ ስልት ዘገምተኛ ለውጥ አሳይቷል።***

እውቀት ወይም ማንበብ እና መፃፍ በቀላሉ ማንበብ መፃፍ፣ መቁጠር እና ቋንቋዎችን በአግባቡ መጠቀም ብቻ እንዳልሆነ አስረድቷል።

ሚዲያ እና የመረጃ እውቀት ማለት እውቀትን፣ አስተሳሰብን፣ ክህሎቶችን እና የተለያዩ ልምዶችን አቀናጅቶ የያዘ እና በተለይ የምናስተላልፋቸው መረጃዎች ወይም ለሌሎች ብዙሃን መገናኛዎች የምንሰጣቸው መረጃዎች ተደራሽነት በአግባቡ ማጣራት መገምገም፣ መጠቀም ማዘጋጀት የሚያስፈልጉትን እውቀቶች የያዘ እና በፈጠራ አግባብነት ባለው ህጋዊነት እና ስነምግባር የሰው መብቶች በማክበር የምናስተላልፋቸው መረጃዎች ማጣራት የምንችልባቸው እነዚህን አንድ ላይ አቀናጅቶ የያዘ ነው።



**ማስታወሻ፡-** **የሚዲያ እና መረጃ እውቀት ጥልቅ የአስተሳሰብ ክህሎቶችን በማጎልበት ግለሰቦች ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ በጥልቀት ማሰብ እና የሚዲያ መረጃዎችን አጣርተው መቀበል የሚያስችላቸው ይሆናል።**

## 2.1 የሚዲያ ይዘቶች እና የመረጃ እውቀት

የመረጃ ምንጭ፣ እና መረጃ የማግኘት ተደራሽነት ሂደቶች ጋር የተያያዘ እና የተለያዩ የመረጃ ምንጮች ይዘቶች እና ዘዴዎችን ያመለክታል። በመረጃ አሰባሰብ እና በመረጃ ስርጭት ወቅት መጠቀም የሚገባንን ዘርፈ ብዙ ቴክኖሎጂዎች እንደ ኮፒዩተሮች፣ ስማርት ስልኮች እና ቤተ መጽሃፍቶች በተለይ ደግሞ ተዛማጅ መረጃዎችን በአግባቡ ለማግኘት በምናደርገው ሂደት የምንጠቀምባቸውን ያጠቃልላል፡ ፡ እንዲሁም መረጃዎችን ለማግኘት እንቅፋት የሚሆኑብንን እንደ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሃብት ጉዳዮች ወይም የቴክኖሎጂ ግድፈቶች ወይም ውስንነት መገምገም እንድንችል የሚደረጉ ሂደቶችን ያካትታል።

በዚህ ትርጓሜ የሚዲያ ተደራሽነት በቀላሉ ማግኘት ከምንችላቸው ቴክኖሎጂዎች፣ ከተለያዩ ቁሳቁሶች እና ኢንተርኔት በላይ ነው። በአጠቃላይ ጥልቅ የሚዲያ ግንዛቤ የሚፈልግ መሰረታዊ የሚዲያ ተደራሽነት መሳሪያ ሲሆን እንዴት እንደሚሰራ እና ውጤታማ እንዴት መሆን እንደሚችል ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

**ትንተና፡-** የሚዲያ ትንተና በሚዲያ የሚተላለፉ መረጃዎችን በጥልቀት መመርመርን፣ የመረጃ ምንጮቹን ከአላማዎቻቸው አንጻር መረዳትን፣ ከተለያዩ አመለካከቾች አንፃር ማየትን እና ከአድሎ የጸዳ መሆኑን ለማወቅ የሚደረገውን ምርመራ ያካትታል። እንዲሁም ውስብስብ የሆኑ የሚዲያ ይዘቶችን በመተንተን ተጨባጭ ማዕከላዊ መልእክቱ ምን እንደሆነ መለየትን እና ጥልቅ በሆኑ ስትራቴጂዎች በተለይ ደግሞ የይዘቱ አዘጋጆች ለመጠቀም የፈለጉትን መርምሮ መረዳትን ያካትታል። የመረጃ ትንተና ከዚህ በተጨማሪም የመረጃ ምንጩቹ ታማኝነትን እና ተጨባጭነትን መገምገም ይጨምራል። በተጨባጭ እውነታዎች እና አስተያየቶች መካከል በአግባቡ መለየትን እና በባህል፣ ማህበራዊ እና ጽንስ ሃሳባዊ ሁኔታዎች ላይ ተጽእኖ የሚያስከትሉትን የሚዲያ ይዘቶች መገንዘብን ያካትታል።

**የሚዲያ ይዘቶችን ለመተንተን አምስቱ ቁልፍ ጥያቄዎች**

- ይህንን መልዕክት ያዘጋጀው ወይም የፈጠረው ማነው? (የፃፊው ባለቤትነት)
- ትኩረትን ለመሳብ የተጠቀሙት ወይም አገልግሎት ላይ የዋሉ የፈጠራ ቴክኒኮች ምንድን ናቸው? (ፎርማት)
- ይህን መልእክት ከእኔ በተለየ መልኩ የተለያዩ ሰዎች እንዴት ሊረዱት ይችላሉ? (አድማጮች)

- በዚህ መልእክት የተካተቱት እሴቶች እና ነጥቦች ወይም ያልተካተቱት እሴቶች እና ነጥቦች ምንድን ናቸው? (ይዘት)
- ይህ መልእክት ለምን ተላከ? (አላማው)

**የይዘት ዝግጅት፡-** የይዘት ዝግጅት የሚዲያ መረጃዎችን ይዘት በተሳካ እና ሃላፊነት በተሞላበት አዘጋጅቶ ማጋራትን ያካትታል። ይህ ሂደት የተለያዩ የሚዲያ ዝግጅቶችን ያካተተ ሲሆን እነዚህም መጻፍ፣ ፎቶግራፍ ማንሳት፣ ቪዲዮ ማረም፣ ግራፊክ ዲዛይን እና የመልቲሚዲያ ታሪኮችን ጨምሮ የተለያዩ የሚዲያ ፕሮዳክሽን ዓይነቶችን ያጠቃልላል። የፈጠራ ስራ ከዚህ በተጨማሪም የቅጂ መብት ህጎችን፣ የስነምግባር ጉዳዮችን እና የሚዲያ ይዘት በተመልካቾች እና በህብረተሰብ ላይ ያለውን ተጽእኖ መረዳትን ያካትታል።

**ትርጉም ያለው ይዘት ለመፍጠር ቁልፍ ጥያቄዎች**

- ይህ እውነት ነው፣ የእኔ ሃሳብ ነው፣ ወይም የሌላ ነው?
- የመረጃ ምንጮቹ ምንድናቸው?
- ሌሎች ሰዎች የእኔን መልእክት በተለየ መልኩ እንዴት ሊረዱ ይችላሉ?
- በዚህ ጥያቄ ተጠቃሚ ወይም ተጎጂ ሊሆኑ የሚችሉ ወገኖች እነማን ናቸው?
- ለዚህ መልእክት ምላሽ ህዝቡ መውሰድ የሚገባው እርምጃ እንዲወስድ የፈለግሃቸው ምንድናቸው?
- ምን አይነት ሃሳቦች፣ እሴቶች ወይም መረጃዎች የአመለካከት ነጥቦች ያንጸባርቃሉ?
- ለማወቅ አስፈላጊ የሆነ ያልተካተተ ምን ሊሆን ይችላል?

**ነጸብራቅ፡-** ስለ ሚዲያ በተመለከተ ሚዲያ የሚያንጸበርቃቸው ቁልፍ ይዘቶች የሚዲያ እውቀት ሲሆን እያንዳንዱ ግለሰብ የተላለፈውን መልእክት በጥልቀት እንዲመረምር እና አድሎ ያልተፈጸመበት መሆኑን  ይረዳል። ሚዲያ አመለካከታችንን እና እምነታችንን የሚቀርጽ በመሆኑ ሚዲያ የሚያንጸባርቃቸውን እና ተጽእኖ የሚያሳድርብንን መረዳት እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በተለይ በአጀንዳው ላይ መጠየቅ ይገባናል። እንዲሁም ይዘቱ በስሜታዊነት ወይም በሌላ በማንኛውም መልኩ እንዴት እንደነካን እንድንገነዘብ ይረዳናል።

በሚዲያ አቋም ከመያዝ በፊት ቅድመ ትንተና በመስራት ጠለቅ ብለን ለማየት የሚያስፈልጉን መሰረታዊ ነገሮች በመለየት የመረጃውን አቋም በቀላሉ መረዳት እንድንችል ያግዘናል።



**እርምጃ፡-** የሚዲያ እውቀት እያንዳንዱ ግለሰብ የሰማውን የሚዲያ መረጃ ነጸብራቅ ተቀብሎ በጥንቃቄ ከመረመረ በኋላ ተገቢ ውሳኔ ላይ እንዲደርስ ይረዳል። ሃላፊነት የተሞላበት እርምጃ ጠቃሚ በሆነ መንገድ ለመምረጥ ያስችላል። እርምጃ መውሰድ ለሌሎች  ተጨባጭ እና ትክክለኛ መረጃ ማጋራት እንዲሁም ደግሞ ትርጉም ያለው ክርክር ላይ በመሳተፍ ወይም ተገቢ እና ተጨባጭ እርምጃዎች በመውሰድ በተነሱ እርምጃዎች ላይ ተገቢ ምላሽ መስጠትን ያካትታል።

## ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያለው ጥናታዊ ጽሁፍ ፣፡-


የከንቴዎች ድምጽ
August 3

ዛሬ ሐምሌ 27 የከንቴ ከተማ ነዋሪ በኑሮ ውድነት ምክንያት እየደረሰበት ያለውን ጫና ለመንግስት ለማሰማት ሰልፍ የወጣ ቢሆንም ሰላማዊ ሰልፍ በወጡ ወጣቶች ላይ የከንቴ ፖሊስ አስለቃሽ ጭስ በሙተኮስ እና ድብደባ በማድርግ ሰላማዊ ህዝብ ላይ ጥቃት ፈጽሟል። በጥቃቱም 3 የአከባቢው ወጣቶች ህይወታቸውን ያጡ ሲሆን በሙቶዎች የሚቆጠሩ ቀላል እና ከባድ ጉዳት ደርሰባቸው ህክምና እየተደረገላቸው መሆኑን በከንቴ ሆስፒታል ተግኝቼ ከጤና ባለሞያዎቹ ያገኘውት መረጃ ያሳያል። ከዚያም በተጨማሪ 23 የሚሆኑ ወጣቶች መታሰራቸውንም አንዳንድ የወጣቶቹ ቤተሰቦች ደውለው አስታውቀውኛል።
የአከባቢው ፖሊስን ፅ/ቤትን ስለጉዳዩ ለመጠየቅ ያደረኩት ሙከራም አልተሳካም።
በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ መረጃ ሳግኝ የማሳውቃችሁ ይሆናል። እስከዛው ሁላችሁም እራሳችሁን ጠብቁ። ያላችሁን መረጃ እና ጥቆማ በውስጥ መስመር ላኩልኝ።

ላሜ የከንቴ ልጅ and 5.2K Others 1K Comments


ከንቴ ሚዲያ ኔትዎርክ (KMN)
August 3

የከንቴ ነዋሪ ወጣቶች የድጋፍ ሰልፍ አደረጉ

ሐምሌ 27፤ 2008

የከንቴ ነዋሪዎች መንግስት እያከናወናቸው ባሉ የልማት ስራዎች ደስታቸውን ለመግለፅ የድጋፍ ሰልፍ አደረጉ። አንዳንድ የአከባቢው ነዋሪዎች ለከንቴ ሚዲያ ኔትወርክ እንደገለፁት መንግስት እያደረገ ያለው ልማት ለአከባቢው እድገት አስተዋፅኦ ያለው በመሆኑ እንዲቅጥልበት እና ማህበረሰቡም ድጋፉን እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

በድጋፉ ወቅት አንዳንድ የልማት አደናቃፊዎች እና ፀረ ሰላም ሃይሎች ለድጋፍ የወጡ ሰወችን ለማወክ እና በህብረተሰቡ ላይ ጥቃት ለመፈፀም የሞከሩ ቢሆንም በፀጥታ አካላት እና በአከባቢው ነዋሪዎች ርብርብ ሁከቱን በፍጥነት ለመቆጣጠር ተችሏል።

መንግስትም የተጀመሩ የልማት ስራውን በአፋጣኝ እንደሚጨርስ አስታውቆ ህብረተሰቡም ትብብሩን እንዲቀጥል እና ፀረ ሰላም ሃይሎችን ለመከላከል ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ አስታውቋል።

5.2K 1.2K Comments

**ነባረዊ ሁኔታ፡-** አንድ የተማሪዎች የቡድን ስብስብ በየጊዜው መረጃዎችን ወይም ዜናዎችን ከሁለቱም ከተለመዱ እና ከአዳዲስ የሚዲያ ዘዴዎች ያገኛሉ። በአንድ የፖለቲካ ክስተት ላይ ሁለት የተለያዩ የሚዲያ ዘዴዎች እርስ በእርስ የሚጋጩ ሪፖርት መልቀቃቸውን ተገንዝበዋል።

**ጥያቄዎችን ስሩ፦**

- የእነዚህን ዜና ሪፖርቶች በጥልቀት መርምሩ
- በሁለቱም ሪፖርቶች ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉ ማዕቀፎች፣ አጀንዳዎች እና ቴክኒኮችን አነጻጽሩ
- እያንዳንዱ የዜና አውታር ይዞ በወጣው የየራሱ ዘገባ እንዴት እንዴት አጀንዳው ላይ ተጽእኖ አሳረፉ፤
- ሚዛናዊ የሆነ አመለካከት ለመያዝ የተለያዩ የመረጃ ምንጮች ማግኘት አስፈላጊነቱ ምንድን ነው?
- ከላይ በቀረቡት ይዘቶች መሰረት የራስህ የሆነ ሚዛናዊ የማህበራዊ ሚዲያ ሪፖርት አዘጋጅ፤
- በአምስቱም የሚዲያ እውቀት ይዘቶችን አንጸባርቅ

# ૩. የጥላቻ ንግግርና የጥላቻ ንግግርን መቃወም

## ૩.1 የጥላችን ንግግርና አደገኛ ንግግሮች

*የጥላቻ ንግግር፦ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት "ማንኛውንም አይነት በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ወይም በሌላ አይነት መገናኛ ብዙሃን ሌላውን ለማጥቃት ወይም ለመጉዳት፣ የአድሎ እና መድሎ ተግባራት የሚያባብስ በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ መጠቀም፣ በተለይ በማንነት ዙሪያ የሚንጸባረቁ ንግግሮች ወይም ዘገባዎች ማለት ሲሆን በሌላ አገላለጽ በሃይማኖት፣ ብሄር፣ ብሄርተኝነት፣ ዘር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ ወይም በሌሎች የማንነት መገለጫ መሰረት አድርጎ ሌላው ላይ ጥቃት ለማድረስ ወይም ለማግለል አገልግሎት ላይ የዋለ ንግግር" ነው ተብሎ ትርጓሜ ተሰጥቶታል።*



አደገኛ ንግግር፦ ማንኛውንም አይነት በአድማጮች ላይ ጉዳት የሚያደርስ አገላለጽ (ንግግር፣ ጽሁፍ ወይም ምስል) እና አድማጮችን በሌላው ወገን ወይም ቡድን ላይ ለጥቃት ወይም ለማጥፋት የሚያነሳሳ አገላለጽ ወይም ንግግር ነው።

**የኢትዮጵያ የጥላቻ ንግግር አዋጅ**

**ጥያቄ፦** ስለ የኢትዮጵያ የጥላቻ ንግግር ህጎች ምን ታውቃላችሁ?




የኢትዮጵያ "የጥላቻ ንግግር እና የመረጃ እጥረት መከላከያ እና ማስወገጃ አዋጅ ቁጥር 1185/2020" የጥላቻ ንግግር ትርጓሜ ከዚህ አንጻር ሲታይ ሆነ ተብለው ጥላቻን ለማስፋፋት እና አድሎ እና መድሎን በዜጎች መካከል ለማስፋፋት ወይም ሌሎች ግለሰቦች ላይ ጥቃት ለማድረስ ወይም በማንነታቸው ምክንያት ማለትም በብሄር፣ በሃይማኖት፣ በዘር፣ በጾታ፣ ወይም በአካል ጉዳተኝታቸው ምክንያት እንዲጠቁ ጥላቻን ማስፋፋት ወይም አድሎ እና መድሎ የሚያስፋፋ ንግግር እንደሆነ ተተርጉሟል።

**በህጉ መሰረት የጥላቻ ንግግር የሚከሰትበት ጊዜ፦**

- ሆነ ተብለው ጥላቻን፣ አድሎ እና መድሎን፣ ጥቃትን ለማስፋፋት እና ለማስፈጽም በሚደረግበት ጊዜ፤
- በብሄራቸው፣ በሃይማኖታቸው፣ በዘራቸው፣ በጾታቸው ወይም ባለባቸው አካል ጉዳተኝነት ምክንያት ትኩረት በሚደረግበት ጊዜ የጥላቻ ንግግር ይከሰታል።

የጥላቻ ንግግር ጥቃት ወይም ጥፋት በማስከተል ወይም ሁከት በመቀስቀሱ ብቻ የሚገለጽ አይደለም። "ጥላቻ" እና "ማግለል" የሚሉ ቃላት ከመነሻቸው ግልጽና ወጥ ያልሆነ አተገባበር የሚያስከትሉ፣ በነጻ ሃሳብን የመግለጽ እድል የሚያቀጭጩ እንደሆኑ አንዳንዶቹ ይከራከራሉ። በህጉ መግቢያ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው በነጻ ሃሳብን የመግለጽ እድልን የሚያቀጭጩ እና የሚገድቡ መሆናቸውን እና የጥላቻ ንግግር የማስወገድ ከለላ ስር እንደሚተገበሩ ተገልጻል።

**በጥላቻ ንግግር ምክንያት የሚጣሉ ቅጣቶች፦**



| | |
|---|---|
| ፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፬ መሰረት የተከለከለውን የጥላቻ ንግግር ያደረገ እንደሆነ እስከ ሁለት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር ፻ሺ ያልበለጠ መቀጮ ይቀጣል፡፡ | 1/ Any person who commits acts proscribed under Article 4 shall be punished with simple imprisonment not exceeding two years or a fine not exceeding 100,000 birr. |
| ፪/ በጥላቻ ንግግሩ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት የሚደርስ ቀላል እስራት ይሆናል። | 2/ If an attack against a person or a group has been committed as a result of a hate speech, the punishment shall be simple imprisonment not exceeding from one year up to five years. |
| ፫/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፭ መሰረት ክልክላ የተደረገበትን ተግባር የፈጸመ እንደሆነ እስከ አንድ አመት በሚደርስ በቀላል እስራት ወይም ከብር ፶ሺ ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል፡፡ | 3/ Any person who commits acts proscribed under Article 5 shall be punished with simple imprisonment not exceeding one year or a fine not exceeding 50,000 birr. |
| ፬/ የጥላቻ ንግግር ወይም የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ወንጀሉ የተፈጸመው ከአምስት ሺ በላይ ተከታይ ባለው የማህበራዊ ሚዲያ ገጽ ከሆነ ወይም በብሮድካስት አገልግሎት ወይም በየጊዜው በሚወጣ የህትመት ውጤት ከሆነ ቅጣቱ እስከ ሶስት አመት የሚደርስ ቀላል እስራት እና ከብር ፻ሺ ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል፡፡ | 4/ If the offense of hate speech or disinformation offense has been committed through a social media account having more than 5,000 followers or through a broadcast service or print media, the person responsible for the act shall be punished with simple imprisonment not exceeding three years or a fine not exceeding 100,000 birr. |
| ፭/ ሐሰተኛ መረጃ በመሰራጨቱ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ ከሆነ፣ ሁከት ወይም ግጭት የተከሰተ እንደሆነ ከሁለት እስከ አምስት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ይሆናል። | 5/ If violence or public disturbance occurs due to the dissemination of disinformation, the punishment shall be rigorous imprisonment from two year up to five years. |

*ከ2 አመት የእስር ቅጣት ጀምሮ እስከ ብር 100,000 ብር ያስቀጣል። ወደ ጥቃት ያመራ ከሆነ ደግሞ ከ1-5 እስር ቅጣት ያስቀጣል። የጥላቻ ንግግር ወይም የተዛባ ወይም የተሳሳተ መረጃ በማህበራዊ ሚዲያ መልቀቅ ከ3 አመት የስር ቅጣት ጀምሮ እስከ ብር 100,000 ያስቀጣል።*

*በጥላቻ ንግግር አዋጅ መሰረት ህግ ጥሶ የተገኘ ላይ የሚጣል ቅጣት ነው።*

## 3.2 የጥላቻ ንግግር ማዕቀፎች

- **መልእክት፡-** በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በንግግር የሚደረግ ቅስቀሳ ይዘት ነው?
- **ተናጋሪ፡-** ተናጋሪው በማህበረሰቡ ውስጥ (ያለው ተጽእኖ የማሳደር ደረጃ) የት ቦታ ላይ ይገኛል?
- **አድማጭ፡-** ንግግሩ የተላለፈው ለየትኛው ማህበረሰብ ክፍል ነው?
- **የተላለፈበት መሳሪያ፡-** የተነገረው ወይም የተጋሩት በየትኛው ነው? እንዴት ተደራሽ ሊሆን ይችላል?
- **ከአውዱ አንጻር፡-** ያለው ማህበራዊ እና ታሪካዊ አውድ ምንድን ነው? በተላለፈው መልእክት ውስጥ የተካተተው አውድ ማግለልን ወይም ጥቃትን አስቦ ነው? ንግግሩ ጉዳት እንዲያስከትል የሚረዱ አስቻይ ሁኔታዎች አሉ?

## 3.3 የጥላቻ ንግግር አመላካቾች እና ምልክቶች

**የስድብ ቃላት/ሃረጎች፡-** አብዛኛውን ጊዜ በጥላቻ ንግግር ውስጥ አገልግሎት ላይ የሚውሉ የስድብ ቃላቶች/ሀረጎች አናሳ ወይም የተገለሉ ማህበረሰብን ለማግለል እና አድሎ እና መድሎ ፍትሃዊ ለማስመሰል ወይም ጥቃት ህጋዊ ለማስመሰል በጥላቻ ንግግር ውስጥ አገልግሎት ላይ ይውላሉ። ዘርን መሰረት ያደረገ፣ ሃይማኖትን እንዲሁም ጾታዊ ሁኔታዎችን እና የአካል ጉዳተኝነትን እና ተያያዥ የስድብ ቃላት በመጠቀም ከስነ አእምሮ ጋር የማይላቀቅ ጥላቻ ወይም ዘረኝነት ቋንቋ በመጠቀም የጥላቻ መፈክሮች ወይም ሌሎች በመጠቀም የጥላቻ ቃላት/ሀረጋት ይሰራጫሉ።


**ኢ-ሰባዊ፡-** ግለሰቦችም ወይም ቡድንን በኢ-ሰባዊ ንግግሮች ማጥቃት ወይም መስደብ ማለትም ከሰው በታች ወይም ከሰዎች የማያንሱ መሆናቸውን በመግለጽ የስድብ ቃላት መጠቀም እና አብዛኛውን ጊዜ እነዚህን ቃላት በዘር በመጥፎ ድርጊት እንደመጣ እና አደገኛ ወይም ንዑስ ሰብአዊ ስሜት የሚያንጸባርቁ ናቸው። ኢ-ሰብአዊ ንግግሮች በተመሳሳይ ሁኔታ ሆነ ተብሎ ትኩረት የተደረገባቸው ወገኖችን ለማግለል እና በእነዚህ ወገኖች ላይ ጥቃት ለማድረስ የሚጠቀሙ ሲሆን እነሱን ለማግለል ወይም በእነሱ ላይ ጥቃት ለማድረስም ከማንኛውም አንግል አንጻር ሲታይ ወይም ከሞራል አንጻር ሲታይ ፍትሃዊ ለማስመሰል ይጥራሉ። ለምሳሌ ሰዎችን እባብ ወይም ጅብ ብሎ መጥራት።

**አሻሚ ቃላቶች ወይም ሃረጋት** ላይ ላያቸው ትክክለኛ መስሎ የሚታዩ ነገር ግን ጠለቅ ብሎ ሲታዩ ትርጓሜያቸው ወይም የሚያስተላልፉት መልእክት በግለሰብ ወይም በቡድኖች ደረጃ በተለይ በማንነታቸው ወይም በባህሪያቸው ወይም በመሰል ማንነታቸው ላይ ትኩረት ያደረጉ ቃላት/ሃረጋት ሲሆኑ ለምሳሌ፡- ጁንታ የሚለውን ቃል ማየት ይቻላል።



**ጥቃት-ጥልቅ ንግግሮች** እንደ ዋነኛ ማመላከቻ ማሳያ የሚያገለግሉ ወይም የጥላቻ ንግግር ሲሆን በቀጥታ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች ላይ በማንነታቸው ወይም በባህሪያቸው ጥቃት ወይም ጉዳት የሚያደርሱ ንግግሮች ናቸው። እነዚህ  አይነት ንግግሮች እጅግ በጣም አደገኛ በመሆናቸው ጥላቻን በማቀጣጠል መቻቻልን በማዳከም አድሎ እና መድሎን በማባባስ በቀጥታ እና በተጨባጭ ለጥቃት ወይም ለሰብአባዊ መብቶች ጥሰት ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። አብዛኛውን ጊዜ እንደዚህ አይነት ንግግሮች ሆነ ተብሎ በቀጥተኛ አንዱን ለማጥቃት ወይም ለማስፈራራት አገልግሎት ላይ ይውላሉ። ለምሳሌ፡- ግደል፣ አጥቃ የሚሉ ቃላቶች አይነት።

**የጥላቻ ንግግር ኢላማዎች፡-** ከዚህ በታች ያለው የፓይ ሰንጠረዥ የጥላቻ ንግግር በተመረጡ የማንነት ቡድኖች የተከፋፈለ መሆኑን ያሳያል። በጣም ዒላማ የተደረጉ ቡድኖች ሴቶች እና ልጃገረዶች (21%) ሲሆኑ፣ ኦሮሞዎች (19.1%) እና አማራዎች (16.7%) በጥብቅ ይከተላሉ። ሌሎች የጥላቻ ንግግር ኢላማዎች ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች (8.7%)፣ ወንድ (5.9%) እና የትግራይ ተወላጆች (5.5%) ናቸው። የ"ተጨማሪ የጥላቻ ኢላማዎች" ምድብ በፓይ ሰንጠረዥ 5ቱ በጣም ከተለመዱ ኢላማዎች ውጭ ያሉ ሌሎች ቡድኖችን ያቀፈ ነው፤ ይህ ፕሮቴስታንቶችን፣ ነጭ ሰዎችን፣ አምላክ የለሾችን፣ ብዙ ዘር ያላቸውን ሰዎች እና አይሁዶችን ያጠቃልላል። የ "ሌላ ዒላማ" ምድብ የተመረጠው የተጠበቀ ባህሪን ዒላማ ያደረገ የጥላቻ ንግግር በተገኘባቸው ጉዳዮች ላይ ነው፣ ግን በማንኛውም ምድቦች ውስጥ አይወድቅም።




ምንጭ፡- በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ በሚውሉ ማህበራዊ ሚዲያ መድረኰች ላይ የጥላቻ ንግግርን ለመግለጽ የሚያስችሉ ምንጮች፡- አዲስ የቃላት መዝገበ-ቃላት እና የመለያ አሠራር፣ ኑሁ ኢብራሂም፣ ፌሊሲቲ ሙልፎርድ፣ ማት ሎውረንስ እና ሪዛ ባቲስታ-ናቫሮ።

## 3.4 የጥላቻ ንግግሮችን ማየት/ቼክሊስት

- [ ] ከእነዚህ በአንዱ ላይ (በዘር፣ በብሄር፣ በሃይማኖት፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በጾታ) ላይ ያነጣጠር ነው።
- [ ] ከእነዚህ ባህሪያት (የስድብ፣ የጥቃት ቀስቃሽ፣ ለአንድ ወገን ጥቃት ጥሪ ማቅረብ ወይም ሃሰት መረጃዎች የያዘ አገላለጽ) አንዱን ይዟል።
- [ ] አድማጮችን ለስድብ/የሚያሳፍር፣ አድሎ እና መድሎ፣ ማዕቀብ ወይም ሌላውን እንዲጠሉ ይገፋፋቸዋል?
- [ ] አድማጮች ሌሎች ላይ እንዲያምጹ፣ እንዲገሉ፣ እንዲዘርፉ፣ እንዲያጠቁ፣ እንዲያፈናቅሏቸው ወይም ለአካላዊ ጥቃት ያነሳሳቸዋል?
- [ ] አድማጮች እርምጃ እንዲወስዱ ስሜታቸውን ያነሳሳቸዋል?

### የውይይት ጥያቄዎች

- በአንተ ወይም በሌሎች ላይ ያነጣጠረ የጥላቻ ንግግር አጋጥሞህ ያውቃል?
  - *የመከባበር ልምዶች እንደተጠበቁ ሆነው ማህበረሰቡ ተገናኝቶ እንዲወያዩ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ተሳታፊዎችን ማበረታታት።*
  - *ለምሳሌ፡- "በፖለቲካ ውይይት ወቅት ስለተወሰነ ማህበረሰብ የተነገረ አሳፋሪ አስተያየቶች ሰምቻለሁ"*
- የጥላቻ ንግግር ማሳያዎች ምንድናቸው?
  - *የስድብ ቃላት፣ የዘረኝነት ወይም የአሳፋሪ ቃላት ወይም ሃረጎች በተለይ በተወሰነ ቡድን ላይ ያነጣጠረ መጠቀም፤*
  - *በተወሰነ ብሄር፣ ሃይማኖት፣ ጾታ ወይም ሌሎች የማንነት መገለጫዎች መሰረት ያደረገ የጥቃት ወይም የማግለያ ጥሪዎች*
  - *ጉርሻ፡- የተለያዩ ንግሮች ናሙናዎችን ማቅረብ (ከተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ፣ ፖለቲካ ማጣቀሻዎች ውጪ) እና ተሳታፊዎቹ እንደ የጥላቻ ንግግር መሆኑን እና አለመሆኑን እንዲወስኑ ጠይቃቸው፤*

- ንግግሮችን ወይም አደገኛ የጥላቻ ንግግሮች የሚያሰኙ ምንድን ናቸው?
  - *ሁሉም ንግግሮች ወደ ጥቃት እንደማያመሩ እና ለጥቃት እንደማይጋብዙ አብራራላቸው ነገር ግን አደገኛ ንግግሮች ለእነዚህ ከፍተኛ ስጋት ይጨምራሉ።*
  - *መጠየቅ፡- 5 ደቂቃ ወስደው በትኩረት በኢትዮጵያ የነበሩ ታሪካዊ ግጭቶች ወይም በአሁኑ ወቅት የሚስተዋሉ ግጭቶችን ያስቡ። አደገኛ ንግግር ለጥቃት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረከተበት አጋጣሚ መለየት ትችላለህ?*
- አደገኛ ንግግሮችን ለመለየት መጠየቅ የሚገባቸው ቁልፍ ጥያቄዎች ምንድን ናቸው?
  - *መልእክቱን ያሰራጨው ማን ነው፤ መልእክቱ በህዝቡ ላይ ተጽእኖ አስከትሏል?*
  - *ታሪካዊ እና ማህበራዊ አውዶች ምንድን ናቸው፤ አሁን የሚስተዋል ግጭት ወይም ውጥረት አለ?*
  - *ለዚህ ንግግር ህዝቡ የሚሰጠው ትርጓሜ እንዴት ሊሆን ይችላል? ጥቃትን ያበረታታል?*
- የጥላቻ/አደገኛ ንግግሮችን ለመቃወም እጅግ ምርጥ ስልት ምንድን ነው?
  - *ጉርሻ፡- የጥላቻ ንግግሮች በኦላይን በሚሰራጩበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ሁኔታዎች በዋናነት፤ ተሳታፊዎቹ ለጥላቻ ንግግር መቃወሚያ ቴክኒኮች ምላሽ በመስጠት ልምድ አላቸው፤*
- በማህበረሰብዎ ውስጥ የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል ሌላ ዘዴ አጋጥሞዎታል?

## 3.5 የጥላቻ/አደገኛ ንግግሮች መቃወም

**መቃወም እና አማራጭ ዘገባዎች**

የመቃወሚያ ዘገባዎች በቀጥታ በጥላቻ ንግግር ግብረ መልስ እና ለማስወገድ አስፈላጊውን ጫና የሚፈጥር ሲሆን ይህም የጥላቻ ንግግር መልእክቶችን በማጣጣል እና ዋጋ እንዳይኖራቸው በማድረግ በተገቢው መቃወሚያ ክርክሮች እና እውነታዎች በመደገፍ ነው። በተቃራኒው ግን አማራጭ ዘገባዎች አዎንታዊ እና አካታች የአእምሮ አስተሳሰብ በማጎልበት ጠቃሚ ሃሳቦችን በመገንባት ረገድ ህብረተሰቡን በማበረታታት የጥላቻ ንግግሮችን ስርጭት ጨምሮ በመልካም ጎን በአዲስ እይታ እንዲተካ ማድረግ ነው። ሁለቱም ስትራቴጂዎች አዎንታዊ ውይይቶችን በማጎልበት እና ጎጂ ዘገባዎችን በማምከን ላይ ያነጣጠሩ ናቸው።

**የሚከተሉት አራቱ ዋና ዋና የተለመዱ አማራጭ ዘገባዎች ናቸው፦**

**በእውነት ላይ የተመሰረተ አማራጭ ዘገባ፦** ይህ አማራጭ ዘገባ ወይም ትረካ ተጨባጭ እና በማስረጃ የተደገፋ መረጃዎች ላይ መሰረት በማድረግ የጥላቻ ንግግር ለመቃወም አገልግሎት ላይ ይውላል። እንዲሁም በሃሰት የቀረቡ ጥያቄዎች ወይም መረጃዎችን በተጨባጭ ማስረጃ፣ የመረጃ ቋቶች፣ እስታቲክስ እና አስተማማኝ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም አድማጮችን ለማስተማር ይጠቅማል። **ለምሳሌ፦** ብሄር ተኮር የወንጀል ድርጊቶች ጋር በተያያዘ የቀረቡ የሃሰት መረጃዎችን በተጨባጭ እና ትክክለኛ የወንጀሉ ስታቲስክ መረጃዎች በማቅረብ ሃሰት መሆኑን ለአድማጮች ማረጋገጥ።

**የሞራል አማራጭ ዘገባ/ትረካ፦** ይህ አይነቱ ዘገባ ወይም ትረካ በትክክለኛ አእምሮ እና የሞራል እሴቶች የሚቀርብ በተለይ ደግሞ በጋራ የሚጋሩ ሰብአዊ እሴቶች እና ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ዘገባ ወይም ትረካ ነው። በግለሰቦች እና በማህበረሰብ ላይ የጥላቻ ንግግር የሚያስከትለውን ጉዳት እንደ ማሳያ ይጠቀማል። **ለምሳሌ፦** የቀረበው የጥላቻ ንግግር ትኩረት ያደረገበት ሃይማኖት እና የጥላቻ ንግግሩን ለመቃወም በሰብአዊ እሴቶች እና መተሳሰብ ላይ ትኩረት በማድረግ ከልዩነት ይልቅ በጋራ የምንጋራቸው ሰብአዊ እሴቶች ላይ ትኩረት በማድረግ የጥላቻ ንግግር መቃወም ይቻላል።


**የቀልድ እና መሳለቂያ ንግግሮች፦** የጥላቻ ንግግሮችን ለማጣጣል እና ለማውገዝ ጥቅም ላይ የሚውሉ የማስመሰያ እና የተጋነኑ ቃላት መጠቀምን ያካትታል። አድማጮችን በቀልድ መልክ በማበረታታት በጥላቻ ንግግር ላይ ያላቸውን ስሜት ወደ አዎንታዊ መንገድ ማዞርን ያካትታል። ለምሳሌ፦ የተለያዩ የጥላቻ ንግግሮች ለማስወገድ የሚያስችሉ የቀልድ ወይም ይህንኑ ማፋለስ የሚችሉ ቪዲዮችን ማሰራጨት።

**አዎንታዊ አማራጭ ዘገባዎች/ትረካዎች፦** በዚህ መልኩ ይህ አይነት ዘገባ ወይም ትረካ በተለይ በማህበረሰቡ ዘንድ የተሰራጨውን የጥላቻ ንግግር ለመቃወም እና በዚህ ተቃውሞ ላይ ደግሞ የሰፊውን ህዝብ አመለካከት የበለጠ አካታች በማድረግ በመቃወም ተግባር ላይ የሚውሉ አዎንታዊ ትርካዎች እና ምሳሌዎችን ያካትታል። ትኩረት የተደረገባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ወይም ቡድኖች ከዚህ የጥላቻ ንግግር እንዲወጡ ያሚያስችል ስኬታማ ትረካዎችን እና አዎንታዊ አስተዋጽኦችን ማጋራትን ያበረታታል።

እነዚህን የመቃወሚያ እርምጃዎች በመተግበር ግለሰቦች እና ማህበረሰቡ የጥላቻ ንግግሮችን ለመገዳደር እና ተጽእኖውን ለመቀነስ ብሎም አብዛኛውን ህዝብ አካታች የሆኑ ውይይቶችን በማበረታታት የጥላቻ ንግግር ተጽእኖን ውጤታማ በሆነ መልኩ መቀነስ ይቻላል።



*ስለ ጉዳዩ የተካሄደ የትንተና ጽሁፍ2፦*




**አውድ፦** በኢትዮጵያ ታዋቂ የማህበራዊ ሚዲያ የተለጠፈው የሃሰት መረጃ በተወሰነ አናሳ ማህበረሰብ ክፍል የአእምሮ የጤና እክል ያለባቸው መሆኑን በሃሰት ያቀረበባቸው መረጃ እና የሌላውን ማህበረሰብ ክፍል ወይም ብሄር መሬት ለመቀማት የሞከረው፣ አጋጣሚ ወደ ኦላይን ጥላቻ ንግግር በማምራት ጥቃት አስከትሏል። ይዘቱም በአንድ ታዋቂ የማህበራዊ ሚዲያ ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰብ ፌስቡክ ገጽ ላይ ለማህበረሰቡ ተላልፏል።

ስራ፦

- የጥላቻ ንግግሮችን ከተለጠፋበት ቦታ መለየት ማሳያዎቹን መዘርዘር
- በጥላቻ ንግግር ማዕቀፍ መገምገሞ
- ንግግሩ እንዴት ወደ አደገኛ ሁኔታ ሊሸጋገር እንደሚችል እና ወደ ጥቃት እንደሚያመራ ተወያዩበት።
- የመቃወሚያ/አማራጭ ዘገባ/ትረካ አዘጋጁ

# 4. የተሳሳተ መረጃ እና የማረጋገጫ እውነታዎች

## 4.1 የተሳሳተ መረጃ

*የተሳሳተ መረጃ ማለት ጤናማ ባልሆነ አካሄድ እና ፍሰት መዘጋጀት ወይም መተሳለፍ ማለት ነው። በመሆኑም በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ከሁኔታዎች ጋር ይያያዛል፦*

**የተሳሳተ መረጃ** ማለት ሆነ ተብሎ ለመጥፎ ነገር ለመጠቀም ወይም ጉዳት ለማድረስ በሃሰት ተቀነባብሮ በተሳሳተ መንገድ የሚሰራጭ መረጃ ማለት ነው። ሆነ ተብሎ በሃሰት የተቀነባበረ ወይም ሆነ ተብሎ በሃሰት በምስል እና በድምጽ መረጃ የተለያዩ ሴራዎችን እና የሴራዎችን ጽንሰ ሃሳብ ተከትሎ የተቀነባበረ ወይም በሃሰት በመንሾካሾክ ሌላውን በመጉዳት የሚሰራጭ ያለመተማመን የሚያስከትል መረጃ ሊሆን ይችላል። **ለምሳሌ፡-** አንድ ግለሰብ የግል ጥቅም ለማስከበር ወይም የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት ሆነ ተብሎ ሌላውን ለመጉዳት በሃሰት ተቀነባብሮ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የተሳሳተ መረጃ ነው።

**የመረጃ ግድፈት/የተሳሳተ መረጃ፡-** ሳያስቡበት ሌሎችን ሰዎች ለማሳሳት ወይም ወደራሱ ለማምጣት በሃሰት የተቀነባበረ መረጃ ማጋራት፤ ለምሳሌ፡- በሃሰት የተቀነባበረ መረጃ ወይም ሹክሹክታ ተጋርተው እንደ እውነት ተቀብሎ ማመን፣ እንዲሁም ሆነ ተብሎ ሳይታሰብበት የተፈጠረ ስህተትን በመረጃ ግድፈት/በተሳሳተ መረጃ ስር መመደብ እንችላለን፤ እነዚህም እንደ ትክክለኛ ያልሆነ የፎቶ መረጃ፣ ቀን፣ ቁጥሮች እና ትርጉሞች ወይም እነዚህ የሚፈጠሩትን እንደ የመረጃ ግድፈት/እንደተሳሳተ መረጃ መመደብ እንችላለን።

**መረጃን በተሳሳተ መንገድ ማቅረብ፡-** ሆነ ብለው የግል መረጃዎችን ተጠቅመው ህትመቶችን ማዘጋጀት፣ ለህዝብ ፍላጎት ሳይሆን ለግል ወይም ለፖለቲካ ጥቅም ሲባል ማቀናጀት ወይም  አሳትሞ መጠቀም ነው። **ለምሳሌ፡-** ሆነ ብሎ ለበቀል የሌላውን ምስል በአሳፋሪ እና በማይገባ መልኩ አዘጋጅቶ በአደባባይ ማቅረብ፣ ሆነ ብሎ ለፖለቲካ ፍጆታ ወይም ለግል ጥቅም ሲባል የሌላውን መረጃ ኢሜል ወይም ሰነድ እንዲሰበር እና ሌሎች እንዲያዩ ማድረግ ናቸው። መረጃን ማሳሳት አብዛኛውን ጊዜ የሚያካትተው አሳሳች ሃሳቦችን ወይም መስመር ለማስያዝ ወይም ጉዳት የሚያስከትል ዘገባ/ትረካ ከእውነት በራቀ መንገድ አዘጋጅቶ ማቅረብን ያካትታል። በዚህ ጊዜ የመንግስት አካል ላይ ትኩረት በሚደረግበት ጊዜ የተሳሳተ መረጃ ወይም በሌላ መንገድ መረጃን በማሳሳት ሌላ ማንኛውንም መጉዳት በሚችል መልኩ፣ በተለይ ደግሞ አወዛጋቢ በሆኑ ጉዳዮች ያካተቱ ወይም ሆነ ብለው ሌላው የጥቃት ዘመቻ ለመክፈት የሚያደረጉትን ያካትታል።

**ማስታወሻ፡-** ነገሮችን ለማቅለል አብዛኛዎቹ “የተሳሳተ መረጃ” በማለት የሚጠቀሙ ሲሆን ይህንን ቃልም ከላይ ለተገለጹት ለሶስቱም አፈራርቆ ይጠቀሙበታል።



## 4.2 የተሰሰተ መረጃ ገጽታዎች


የተሳሳተ መረጃ የተለያዩ በርካታ ገጽታዎች ሊኖረው ይችላል። አብዛኛዎቹ የታወቁት፡-




**የአሽሙር ንግግሮች**

ጉዳት የማድረስ አላማ የለውም፣ ነገር ግን የማታለል አቅም አለው። ይህ የመረጃ መታወክ በቀላሉ እንደገና ሊጋራ ወይም ሊዛባ ይችላል፣ ከዋናው አስቂኝ አውድ ውጭ ይሰራል።

*በእስክሪንሻት ገጽ እይታ ላይ እንደሚታየው በተሳሳተ መንገድ በኢትዮጵያ የሚገኝ የኑክሌር ኃይል ማመንጫን እንዳለ የሚያሳይ አስቂኝ ምስል ይታያል። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ምስሉ  የኢትዮጵያ የአከባቢ የአልኮል መጠጥ የሆነውን "አሬቄ" የማጣራት ሂደት ነው። ሩሲያ በዩክሬን ውስጥ ትልቁን የኑክሌር ኃይል ማመንጫ ተከላ በመቆጣጠሯ ምክንያት የተሰራጨው ሜም በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ መነጋገሪያ ሆኗል። (ለተጨማሪ መረጃ የፔሳ ቼክ እውነታን የማረጋገጫ ጽሑፍ ይመልከቱ)*





**የሃሰት ግንኙነት**

ዋናው ርእሰ ጉዳይ፣ እይታ ወይም የጽሁፍ መግለጫ ይዘት የማይደግፍ ሆኖ ሊገኙ ይችላሉ።

የሃሰት ግንኙነታቸው በመጀመሪያ ደረጃ ሊኖር ይችላል ብለን ብናስብ እንኳን ርእሰ ጉዳዮቹ የሌላውን ስሜት በመኮትኮት፣ በሰፊው ምልከታ ሊወጣ የሚችል ሲሆን ይህ አይነቱ አሰራር የሚዲያውን ታማኝነት የሚጎዳ እና ጽንፈኝነትን የሚያዳብር ሊሆን ይችላል።

*የእስክሪንሻት ምስሉ የተማሪዎች የመውጫ ፈተና ውጤቶችን ለመመልከት የሚያገናኝ ሊንክ እንደሚሰጥ የሚናገር የፌስቡክ ጽሑፍን ያሳያል። ሊንኩ ተጠቃሚዎችን በተሳሳተ ይዘት እና በተጋነኑ የይገባኛል ጥያቄዎች ጠቅ እንዲያደርጉ ለማታለል የተቀነባበረ ነው። ነገር ግን ሊንኩ ወደ መውጫ ፈተና ውጤቶች የሚያመራ ሳይሆን ይልቁንስ ምንም ተዛማጅ መረጃ ወደሌለው የቴሌግራም ሰርጥ ነው የሚያመራው ( ለተጨማሪ መረጃ የፔሳቼክ እውነታን የማረጋገጫ ጽሑፍ ይመልከቱ) ።*









**አሳሳች ይዘቶች**

አንድ ጉዳይ አግባብነት ባለው የመረጃ ማዕቀፍ ውስጥ ለማካተት ወይም በተለይ በግለሰቦች ዙሪያ የተሳሳተ መረጃ ጥቅም ላይ ማዋል ማለት ነው። በመሆኑም ፎቶዎችን መርጠን በመጠቀም ወይም ርእስ ጉዳዮችን ወይም ማጣቀሻዎችን መርጠን በመጠቀም ክርክሩን በሚደግፍ መልኩ ማቅረብ ነው።

*የእስክሪንሻት እይታዎች በዎልታ ሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የዜና ዘገባ ያሳያሉ። ”በፎቶዎቹ ላይ የሚታዩት ሴቶች የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቢቤ፣ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዲ፣ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስትር ኤርጎጊ ተስፋዬ ( ከግራ ወደ ቀኝ) እና ሌሎች ናቸው። የዋልታ የዜና ርዕስ" በከተማ አስተዳደሩ የተገነባው የሴቶች የመልሶ ማቋቋም እና የልህቀት ማዕከል ሥራ ሊጀምር ነው" ይላል።*

*ይሁን እንጂ በምስሎቹ ውስጥ ያሉት መግለጫዎች የተለየ ታሪክን ይናገራሉ። የመጀመሪያው እስክሪንሻት (በግራ በኩል ያለው ምስል) አንድ ግለሰብ “ገላ በመሸጥ የሚተዳደሩ ሴቶች” በሚለው መግለጫ ስር "ዋልታ ምን እያለ ነው?" የሚል ሃሳብ አጋርታል። ሆኖም ሁለተኛው ምስል በራሱ በዋልታ ሚዲያና ኮሚኒኬሽን የተሰራጭው የሴት ሠራተኞችን ሕይወት ለመለወጥ የተዘጋጀው ማዕከል ሥራውን ሊጀምር ነው ይላል። የመጀመሪያው ልኡክ ጽሑፍ አሳሳች ነው ምክንያቱም ጥቅሱ የተለየ ትርጉም እንዲኖረው ለማድረግ ስለተሞከረ።*








**የተሳሳተ የፖስተር ይዘት**

ከዋናው እውነተኛ እና የመረጃ ምንጭ ወይም ሰውኛ ገጽታ ማላበስ ማለት ነው። ይህ አይነቱ የተሳሳተ መረጃ ደግሞ በአንድ ተጨባጭ ድርጅት ላይ ወይም ግለሰብ ወይም ብራንድ ወይም ሌላ ተቋም ያለንን እምነት ይሸረሽራል።






**ሃሰት አውድ**

በሃሰት የሚቀርብ ሀሳብ ወይም አውድ እውነተኛ ይዘት ያለው መረጃ ከተሳሳተ አውድ ወይም መረጃ ጋር ተደባልቆ መቅረብ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ አውድ ወይም መረጃ በሚቀርበበት ወቅት ነው።

*የመጀመሪያው ልኡክ ጽሑፍ (ከላይ ያለው የእስክሪንሻት ገጽ እይታ በ2023 የተጋራ ሲሆን" ይህም (የጦር መሣሪያዎችን የሚያመለክት) በሻሸመኔ በሚገኝ ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ተገኝቷል" የሚል መግለጫ ተሰጥቶታል። ይሁን እንጂ ምስሉ ከአውድ ውጭ ነው የቀረበው። ሁለተኛው ልኡክ ጽሑፍ (በቀኝ በኩል ያለው የእስክሪንሻት እይታ) ምስሉ በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን እንደዘገበው በ2021 መሆኑን እና በሲዳማ ክልል በአንድ ግለሰብ ቤት ውስጥ የተገኙ የጦር መሣሪያዎችን እንደሚያሳይ ያብራራል።*



**የተቀናባበረ ይዘት**

እውነተኛ የመረጃ ምንጮች ወይም ምስሎች ሆነ ተብሎ ሌላውን ለመሸወድ በሚቀነባበሩበት ጊዜ ፎቶዎች መለወጥ፣ ቪዲዮችን ከትክክለኛ ገጽታቸው የመቀየር ስራን ያካትታል። እስከ አሁን እውነተኛ ይዘቶች በአጠቃላይ ትርጓሜያቸው ከታሰበ ይለያሉ።

*የመጀመሪያው ስዕል (በግራ በኩል) የኢትዮጵያ እንደሆነ የሚነገርለት መርከብን ያሳያል። ይሁን እንጂ ባንዲራው ምንም ባንዲራ በሌለው የመጀመሪያው ስዕል (በቀኝ በኩል) ባለው ላይ በፎቶሾፕ የተጨመረ ነው።*





*በኤ አይ የተቀነባበረው ምስል ዶናልድ ትራፕ ከፖሊስ ኦፊሰሩ ለማምለጥ ሲሮጡ እና ተይዘው ሲታሰሩ ያሳያል። ሆኖም ምስሉ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንት የተቀነባበረ እና በውነታው አለም ያልተከወነ ነው።*

**በሃሰት የተቀናበባረ ይዘት**

ይህ አይነቱ የመረጃ ይዘት 100% በሃሰት እንደ አዲስ የተቀነባበረ ይዘት ያለው ሆነ ተብሎ ሌላውን ለመሸወድ ወይም በሌላው ላይ ጉዳት ለማድረስ የሚቀነባበር ነው። ሙሉ በሙሉ የመረጃ ይዘት በሃሰት በሚቀነባበርበት ጊዜ የሚኖረው ግድፈት ወይም ውስንነት የአክተሮቹ ወይም የተዋናይወቹ አስተሳሰብ ብቻ ይሆናል። በእውነት የቀረበ እና በሃሰት የተቀነባበረ መረጃ ልዩነት በአይን ለማየትም ሆነ ለመገመት እጅግ በጣም ከባድ ነው። "በጥልቀት የተቀነባበረ ሃሰት መረጃ" ያየን እንደሆነ በሃሰት የተቀነባበረ መረጃ አካል ሲሆን ነገር ግን ሙሉ በሙሉ እምነታችንን ወደ መቀየር የሚያደርስ ጥልቅ ተጽእኖ እንዴት ሊያሳድርብን እንደሚችል ማየት እንችላለን።

## 4.3 እውነታን የማጣራት እና የመቃወሚያ ስልቶች

**እውነታን ማጣራት** ማለት የተሰበሰበውን ወይም የተገኘውን መረጃ ግብዓት እና ተጨባጭ ምንጮች ከየት እንደሆኑ እና ትክክለኛነታቸውን እንዲሁም ታማኝነታቸውን ለማረጋገጥ የባለሙያዎችን ግብዓት እና ትክክለኛ ውጫዊ መረጃዎችን ይጠቀማል።

አውነታን ማጣራት እና በሃሰት የተቀነባበሩ መረጃዎችን መለየት ለውሳኔ ሰጪ የመንግስት አካላት ተገቢ መረጃዎችን ለማቅረብ ይረዳል። ለእውነታ ማጣሪያ ማረጋገጫ የቀረበው መረጃ በአግባቡ ተጣርቶ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ማረጋገጥ። ማጣራት የማይቻሉ መረጃዎች ከሆኑ እንደ የሰው አስተያየቶች፣ ቃል መግባት እና ግምቶች ብቻ ሲሆኑ እነዚህን በተመለከተ ራሱን የቻለ የመረጃ ማጣሪያ ስልት ስራ ላይ ይውላል።



**የመረጃዎች እውነተኛ ማጣሪያ ሂደቶች**

- የቀረቡትን ጥያቄዎች መለየት፦ በተለምዶው የደብሊውኤች ጥያቄዎች (ማን፣ መቼ፣ የት፣ ለምን፣ እንዴት ወዘተ...) የሚሉትን በመጠቀም የማጣራት ስራዎችን መስራት።
- ጽንሰ ሀሳቦችን እና ሃረጋትን በአግባቡ መተርጎም ወይም መግለጽ
- የመረጃ ምንጭ ማግኘት፦ የማረጋገጫ ማስረጃዎችን እና ማረጋገጫ ስልቶችን መለየት፤
- ባለሙያዎችን መጠቀም፦ በማብራራት ረገድ እንዲረዱ
- መረጃዎችን ማረጋገጥ፦ የመጨረሻ የቅርብ መረጃዎችን እና አስተማማኝ የሆኑ መረጃዎችን ለይተው መጠቀም፤
- የቀረቡ ጥያቄዎችን ማመሳከር፦ ሌሎች ምንጮችንም በመለየት ማነጻጸር ስራዎች ናቸው።

ግለሰቦች ከግጭት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚችሉ የሚከተለው እንደ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፦ በቅርቡ በአንድ ክልል ለተከሰቱ ግጭቶች መንስኤው አንድ ብሄርነው የሚል የማህበራዊ ሚዲያ ፖስት እንዳያችሁ አስቡ። የሚከተሉት መረጃው እውነተኛ መሆኑን ማጣራት የምንችልባቸው መንገዶች ናቸው፦

- **የመረጃ ምንጮች፦** አስተማማኝ የዜና ድርጅት፣ከታማኝ የአይን ምስክሮች ወይም የመረጃ ምንጮች መግለጫ ከአስተማማኝ ድርጅት የተገኘ ምንጭ ነው?
- **ከበርካታ ምንጮች ማመሳከር፦** ከሌሎች የመረጃ ወይም የዜና ምንጮች፣ አለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ወይም ከሌሎች ገለልተኛ ታዛቢዎች፣ እና ሌሎች ምንጮች መረጃዎችን በማሰባሰብ ማመሳከር እና ማጣራት ያስፈልጋል። ከእነዚህ መረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች ታማኝነታቸው ወጥነት ሊኖረው ይገባል።
- **የይዘቱን አውድ እና ዳራዎች፦** ከርእሱ ባሻገር ለግጭቶቹ መንስኤ ወይም ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ታሪካዊ አውዶችን እና ምክንያቶችን ለመረዳት ጽሁፉን ማንበብ።
- **ተጨባጭ በአይን የሚታዩ ማስረጃዎችን መመርመር፦** የቀረበው ጥያቄ ጋር ተያይዞ ምስሎች ወይም ቪዲዮዎች ቀርበው ከሆነ የምስሎቹን በሌላ አንግል ወይም ገጽታ መመርመሪያ መሳሪያ በመጠቀም ታማኝነታቸውን ማመሳከር እና ማረጋገጥ። አሳሳች የሆኑ እይታዎች ወይም የቆዩ ፈለጎች ዘገባውን/ትረካውን ሊያዛቡ ይችላሉ።
- **የባለሙያ ትንተና መፈለግ፦** ከክልሎች ወይም ከየትኛውም ባለስልጣናት እንደ ፖሊስ አካል ያሉ ከጉዳዩ ጋር ቀጥታ አግባብነት ወይም ግንኙነት ካለው ባለሙያ ማሟላት።

የእነሱ ጥልቅ እይታ ሌላ መረጃ ወይም አስተማማኝ አስተያየት ወይም ውጤት ሊሰጠን ይችላል።

- **መድሎ እና አጀንዳ ከግምት ውስጥ ማስገባት፡-** በመረጃ ምንጮቹ ላይ ያዳላሉ ተብለው የታሰቡ ጉዳዮችን መመርመር መገምገም ወይም የጸሀፊውን ትክክለኛነት ወይም ታማኝነት ማረጋገጥ። መረጃዎቹን ያቀረቡት ሆነ ብለው ለትክክለኛ አላማ መሆኑን ወይም የተለየ አጀንዳ ወይም ዘገባ ትረካውን ሊያዛባ ወይም አድሎ ሊያስከትል ይችላል?
- **የማጣራት ስራዎችን ወቅታዊ ማድረግ፡-** ግጭቶች በባህሪያቸው በፍጥነት የሚዛመቱ ክስተቶች ናቸው። በመሆኑም ወቅታዊነቱ የተረጋገጠውን መፈለግ ወይም በየጊዜው የሚደረጉ ሪፖርቶችን መከታተል እና አዳዲስ መረጃዎች ከተገኙ በመጠቀም የክስተቱን መነሻ ላይ ለውጥ የሚያስከትሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ይህ አይነቱን የአካሄድ ቅድም ተከተል ግለሰቦች ከግጭቶች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በጥልቀት መገምገም እና መረዳት እንዲችሉ የሚረዳ በመሆኑ የተሳሳተ መረጃ ስርጭትን ወይም ግጭት ቀስቃሽ መረጃዎችን በማስወገድ በከፍተኛ ደረጃ ስሜት ቀስቃሽ የሆኑ እና ውስብስብ ጉዳዮች ላይ ህዝቡ መረጃ እንዲኖረው እና በጥልቀት እንዲወያይበት ይረዳል።

## 4.4 የተሳሳቱ መረጃዎች ዝርዝር በወቅቱ መለየት

- [ ] ምንጮችን ማረጋገጥ
- [ ] ይዘቱን በሙሉ ማጣራት
- [ ] ጽሐፊውን ማጣራት
- [ ] ምስሎቹን ማጣራት
- [ ] በርእሰ ጉዳዩ ላይ ሌሎች ሪፖርቶችን ማካተት
- [ ] አድሎ ተፈጥሯል የሚለውን መለየት

**ቅድመ ማጋለጥ፡-** በመጀመሪያ ደረጃ ሰዎች ለተሳሳተ መረጃ እንዳይወድቁ ወይም በተሳሳተ መረጃ ስር ከመውደቃቸው በፊት ሰዎች መከላከል የሚችሉበትን መንገዶች እንዴት ለማሰስ የሚረዳ አካሄድ ነው።

ምርምር የሚያካሄዱ ባለሙያዎች የእውነት የማጣራት ሂደት የበሽታ ምልክቶችን እንደማከም እና ሰዎች በዚህ ተጽእኖ ስር እንዳይወድቁ አስቀድሞ ለመከላከል የሚረዳ ክትባት እንደሆነ ይናገራሉ።




**የእውነት ማጣሪያ መሳሪያዎች**

የተለያዩ መረጃዎችን ይዘት ለማመሳከር እና ለማጣራት የሚረዱ በርካታ ግልጽ የሆኑ የመመርመሪያ መሳሪያዎች ይኖራሉ። ከእነዚህ መሰረታዊ የእውነታ ማጣሪያ እና መመርመሪያ መሳሪያዎች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው።

**የምስል ማመሳከሪያ ማረጋገጫ መሳሪያዎች**

- በጎግል ሌንስ ግልባጭ ምስል ፍለጋ
- ቲን-አይ
- ቢንግ
- ያንዴክስ
- ኢንቪድ





**የመገኛ መልካ ምድር ማመላከቻ መሳሪያ**

- የጎግል ማፖች (የጎዳና ምልከታ)
- ጎግል ኧርዝ
- ወርልድ ኢሜጅሪ ዌይ ባክ

**የኤ አይ መለያ መሳሪያዎች**

- www.fakeimagedetector.com
- www.deepware.ai

*የተያያዘ ጥናታዊ ጽሁፍ 3፡-*





**አውድ፡-** በፌስቡኩ ላይ የተለጠፈው እና ለህዝቡ የተለቀቀው ምስል የሚያመለክተው "የኢትዮጵያ በርበራ ወደብ" ን ነው።

**ስራ፡-**


- ይህንን ጥያቄ የእውነታ ማጠናሪያ ቅደም ተከተሎችን/ ሂደቶችን በመጠቀም መመርመር
- ይዘቱን በጥልቀት በመመርመር እና አስተማማኝ ምንጮችን በመጠቀም የመረጃውን ትክክለኛነት ማጣራት
- የማህበራዊ ሚዲያ የመረጃ ማጣሪያ አስመልክቶ ዝርዝር ሪፖርቶችን (የእውነታ ማጣሪያ ስልቶች) ማጠናከር

# 03

# ጥበብ ለሰላም ግንባታ



# አርቲቪዚም ከኢትዮጵያ አውድ አንፃር



## ፁዘት

56 የምዕራፉ ዓላማ
57 መግቢያ እና ትርጓሜዎች
63 ጥበብ ለአንድነት እና ለብዝሃነት አከባበር
68 ጥበብ እንደ የማህበራዊ ለውጥ ቀስቃሽነት
74 ይህንን እንስራ

## የምዕራፉ አላማ

*በዚህ ምዕራፍ ጥበብ በሰላም ግንባታ ውስጥ ያለውን አስተዋጽኦ አቅም የምንመለከት ሲሆን በተለይ ደግሞ ከኢትዮጵያ አውድ አንጻር ጥበብ ለሰላም ግንባታ ያለውን አቅም እና አስተዋጽኦ እንመለከታለን። ለሰላም ግንባታ፣ ለማህበራዊ ለውጥ፣ ለህዝብ አንድነት እና ከድህረ ግጭት በኋላ ሰላም ለማስፈን እንዴት ጥበብን ማሳደግ ወይም አክቲቪዝምን ማጎልበት ይቻላል የሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል። የኢትዮጵያ አርቲስቶች እና በየቀኑ የእነሱ ፈጠራዎች ህዝቡ እንደ መሰረታዊ ውይይት የሚጠቀመውን ለዘላቂ እና እውነተኛ ሰላም እንዴት መጠቀም እንደሚቻል እናስሳለን።*





## 1. መግቢያ እና ትርጓሜዎች



*ኢትዮጵያ በዘርፈ ብዙ ጥበባዊ ቅርሶች ሃብታም ስትሆን ይህም ለበርካታ ክፍለ ዘመናት በስፋት እና በብዛት የሚንጸባረቅ ቱባ ባህሎች እና ብዝሃ ባህሎች ታሪካዊ መግለጫዎች ከብሄራዊ ማህበራዊ እድገት ጥልቀት ጋር ይያያዛል።*

እነዚህ መግለጫዎች ለመዝናኛ ብቻ የተዘጋጁ አይደሉም። በትክክል የህግ የበላይነት እና አተገባበር የሚያመለክቱ ወይም እንደ መመሪያ የሚያግዙ፣ የድል ዜናዎች የሚዘክሩ ከፈጣሪ የተመረጡ መሆናቸውን የሚያመለክቱ ወይም አቅጣጫ የሚያስይዙ ሁኔታዎችን እና ፈጣሪንም ጨምሮ የሚተቹ ስራዎች ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ ጥበባዊ መግለጫዎች ከኢትዮጵያ ህብረ ብሄር ወይም ህብረ-መልካ ምድሮች አንፃር የበለጠ ብሄራዊ ማንነት መግለጫዎች ለመፍጠር እና ብሄራዊ ስሜት ለማዳበር ረድተዋል።

ሃገሪቱ በተለያዩ ብዝሃ ባህሎች የበለጸገች ከመሆኗም አንጻር ከ80 በላይ ብሄር ብሄረሰቦች የሚኖሩባት እያንዳንዳቸውም የየራሳቸው ባህሎች፣ ቋንቋዎች፣ ጥበባዊ አገላለጾች እና ጥበባት ነጸብራቆዎች ያላቸው ናቸው። ብዝሃነት ጥንካሬ በመሆኑ ታሪካዊ እና አሁንም የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን እንደ የብሄር ውጥረቶች፣ በተለያዩ ሃብቶች ወይም የሃብት ምንጮች የሚስተዋሉ እና የፖለቲካ ግጭቶችን ጨምሮ ማህበራዊ ልዩነቶችን በማስወገድ ወይም ከእነዚህ ጋር ተያይዞ የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ የበኩሉ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

በኢትዮጵያ የጥበብ ስሜት ምንጊዜም ተለዋዋጭ ባህሪያት ያሉት ሲሆን አብዮታዊ ስሜቶች የሚቀሰቅሱ ሙዚቃዎችን ጨምሮ የሰላም ግንባታ እና አንድነት የሚያቀነቅኑ የጥበብ አይነቶች ናቸው። ጥበብ በኢትዮጵያ ማህበረሰብ ዘንድ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ያለው ሲሆን በተለይ ታሪኮችን በማስተላለፍ፣ ባህላዊ ጥበቃዎች እና እንክብካቤዎች እንዲሁም ማህበራዊ ግልጋሎቶች አለው። ባህላዊ እና ዘመናዊ የጥበባት ፎርማቶች ከአፈ ታሪክ ወይም በአፍ ከሚነገሩ ግጥሞቸ እና ሙዚቃ ጀምሮ እስከ ቲያትር፣ ድራማዎች እና የዲጂታል ሚዲያ ጥበባት ከምንም በላይ ለምክክር ጉባኤ፣ ለእርቅ ድርድር እና ለሰላም ግንባታ ከፍተኛ ሃይል ያላቸው መሳሪያዎች ናቸው።

በዚህ የመስክ መመሪያ መጽሀፍም በምዕራፉ የተካተተው ተገቢውን የኢትዮጵያ ጥበባዊ ቅርሶች በመጠቀም ግጭቶችን ለማስወገድ እና ማህበራዊ አንድነትን ለማጎልበት መስራት ላይ ያነጣጠረ ነው። ይህ የጥበባዊ መመሪያ አንድነትን፣ ማህበራዊ ለውጥን እና የድህረ ግጭት ማገገሚያ ግንባታ ለማዳበር ይረዳል።

*ሥነ-ጥበቡ በአንተ ላይ እንዲናገር አትፍቀድ- የዐርቲቪዝም ንግግርን መረዳት*

- **ጥበብ፡-** የሰው ልጅ የፈጠራ ክህሎቶች እና የተለያዩ ሚዲያዎች ያላቸው አስተሳሰብ የጥበባት እይታዎች፣ የጥበባት አፈጻጸም እና የስነ ጽሁፍ ጨምሮ ከፍተኛ ጥበባዊ ዋጋ እና እሴት ያላቸውን ስሜት ቀስቃሽ ወይም ታሪኮችን ለማስተላለፍ ይጠቀሙበታል።
- **አርቲቪዝም፡-** አክቲቪዝም ማለት ደግሞ ስሜታዊ በመሆን ማህበራዊ ወይም ፖለቲካል ለውጦችን ለማምጣት የሚወሰድ እርምጃ ወይም የሚደረግ ጠንከር ያለ ዘመቻ ነው።
- **#አርቲቪዝም፡-** ለማህበራዊ ወይም ለፖለቲካ አክቲቪዝም ጥበብን እንደ መሳሪያ ወይም አንዱ ዘዴ መጠቀም ማለት ነው።
- **የተቃውሞ ጥበብ፡-** ጥበብ በአንዳንድ ማህበራዊ ወይም ፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ያጋጠሙትን ችግሮች ወይም አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለመግለጽ ይረዳል።
- **የመልሶ ግንባታ ጥበብ፡-** ጥበብን ለተለያዩ ጉዳዮች የምንጠቀም ግለሰቦች እና ማህበረሰብ ከአካላዊ፣ ከስሜታዊ እና ስነ ልቦናዊ ጉዳቶች እንድናገግም ይረዳናል።

## የውይይት ጥያቄዎች

- ከቀረቡ ትርጓሜዎች/ፍቺዎች የበለጠ በግል አርቲቪዝምን/ጥበባዊነትን እንዴት ትገልጸዋለህ?
  - *አርቲቪዝም/ጥበባዊነት የፈጠራ መግለጫ እንደ ሙዚቃ፣ ስእሎች፣ የሸክላ ጥበባት፣ ጥፈራ ወይም የሰውነት እንቅስቃሴ በመጠቀም የማህበራዊ ኢ-ፍትሃዊ ተግዳሮቶችን በመቅረፍ ለለውጥ የሚያገለግል ነው።*
- በህይወት ማንኛውንም አይነት የጥበብ ምሳሌዎች አጋጥሞህ ያውቃል? አጋጥሞህ የሚያውቅ ከሆነ ምን አይነት ተጽእኖ አሳድሮብሃል?
  - *በደርግ ዘመን የኢትዮጵያ የተቃውሞ መዚቃዎች ወይም በአዲስ አበባ የተቀረጹ ጽሑፎች አንድነትን ያበረታቱ ነበር።*
  - *ከአለም አቀፍ ምሳሌዎች ደግሞ እንደ ባንክሲ የጎዳና ጥበባት ወይም እንደነ "ፈላ ኩቲ" አይነት በሙዚቃ በፖለቲካ የሰፈነውን ሙስና ያጋለጠውን መጥቀስ ይቻላል።*



- አርቲቪዝም/ጥበባዊነት ከልማዳዊ ተቃውሞ ወይም አክቲቪዝም እንዴት ይለያል?
  - *ልማዳዊ አክቲቪዝም አብዛኛውን ጊዜ ቀጥተኛ የሆኑ ስልቶችን እንደነ ህዝባዊ ተቃውሞዎችን፣ አቤቱታዎችን፣ የፖለቲካ ዘመቻዎችን ይጠቀማል። በሌላ በኩል ደግሞ አርቲቪዝም የተለያዩ ተቃውሞዎችን ለመግለጽ የፈጠራ ቅስቀሳዎችን በመጠቀም ስሜታዊ እና በተጨባጭ እይታ የሚገለጹ መልእክቶችን ይጠቀማል።*
  - *ጉርሻ፡- ስለ ዘፈን ወይም ስለ የስእል ጥበባት አስብ፤ ከማንፌስት ማንበብ ወይም በቀጥታ በተቃውሞ ሰልፍ ላይ ከመሳተፍ እንዴት ይለያል?*

ጥበብ በሰው ዘር በሙሉ ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜ ዘርፈ ብዙ ስሜቶችን በአንዴ መቀስቀስ የሚችል ነው። እያንዳንዱ ነገር ከሙዚቃ ጀምሮ እስከ ስእል ጥበባት፣ ቲያትር ጥበብ እና አገላለጽ ባላቸው ለየት ያለ ቀኝት የሰው ስሜት የሚቀሰቅሱ እና በቀጥታ ከሰው ልብ ውስጥ የሚቀረጹ ናቸው።

በእርግጥ ጥቂቶች ጥበብ ለሰላም ከፍተኛ ሃይል ያለው መሆኑን ይቃወማሉ። በርካታ አርቲስቶች በኢትዮጵያ የሰላምን ተምሳሌትነት ወይም አስፈላጊነት በማቀንቀን የማህበረሰቡ አንደነት ግንባታ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። በሃገራችን በድምጻዊ ሙህመድ አህመድ የተቀነቀነው "ሰላም" የሚለው ተወዳጁ ሙዚቃው ዘመናትን ተሻጋሪ የሰላም አስፈላጊነትን በመግለጽከትውልድ ወደ ትውልድ የተሸጋገረ ነው። እንዲሁም የእጅጋየሁ ሺባባው "እስከ መቼ" የሚል ሙዚቃ በሃገራችን ለህዝብ አንድነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው እና ያበረከተ እና ህዝቡ በፍቅር አብሮ እንዲኖር የሚያበረታታ ሌላው ምሳሌ ነው።

# 2. ጥበብ እና ታሪካዊ ዳራው


***የኢትዮጵያ የጥበብ ቅርሶች ቆየት ያሉ እና ስር የሰደዱ የታሪካችን ሃብት ናቸው። እነዚህም ቅርሶች በሃገራችን ለፖለቲካ እና ለሃይማኖት መገለጫዎች እንደ አይነተኛ ሃይል እና ለሃገሪቱ ብሄሮች እንደ መስኮት ራሳቸውን የሚያዩበት ነው።*** የኢትዮጵያ ቅርሶች ከሺ.ህ አመታት በላይ እድሜ ያስቆጠሩ በተለይ ከብሄራዊ ማህበራዊ ልማት እና እድገት ጋር የተያያዙ ናቸው። ይህ የፈጠራ መገለጫ ወይም ማብራሪያ ለተራ ጌጥ ወይም መዝናኛ ብቻ የሚያገለግል ሳይሆን ታሪክን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ እና ሃይማኖታዊ መገለጫዎችን እንዲሁም የሃይል ማጠናከሪያ ሂደቶችን ለማስተላለፍ ከፍተኛ ሃይል ያለው መሳሪያ ነው።

## 2.1 ሃይማኖት እና ጥበብ በኢትዮጵያ

የአክሱም ዘመነ መንግስት (ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ4ኛ መቶ ክፍለ ዘመን - 8ኛው ክፍለ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ) እንደ ዋነኛ መሰረት የሚቆጠር ነው። በዚህ ዘመነ መንግስት የተገነቡ የአክሱም ሃውልቶች የግንባታ ጥበብ እጅግ በጣም አስገራሚ እና ለንጉሳዊ ቤተሰቦች ሃውልት የመቃብር ቦታ ላይ እንደ ምልክት የተገነባ እና የድል መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል። እነዚህ ሃውልቶች እንደ ሁለቱም ጥበብ እና ታሪካዊ ቁርፋቶች የሚያገለግሉ ናቸው።

**የበለጠ ለመማር፡-** የአክሱም ሃውልት ከአንድ ድንጋይ ተፈልፍሎ ቀጥ ብሎ እንዲቆም የተገነባ ሃውልት የተለያዩ የማስታወሻ ጽሁፎች ወይም የእፎይታ ንድፍ የተቀረጸበት እንደ መቃብር ሆኖ የሚያገለግል ጥርብ ድንጋይ ነው።

የክርስትና እና የእስልምና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በ4ኛው ክፍለ ዘመን እና በ7ኛ ክፍለ ዘመን ነበር። የእነዚህ ሃይማኖቶች ወደ ሃገራችን መምጣት ደግሞ በሃገራችን ጥበባዊ እና ታሪካዊ ቁርፋቶች ላይ የራሱ አዲስ ምእራፍ የከፈቱ ከመሆናቸውም በላይ የራሳቸውን ህብረ ቀለማት እንዲሁም ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው ትረካዎች ይዘው ብቅ ብለዋል። ታሪካዊ እና ሃይማኖታዊ ቦታዎች እንደ አክሱም ሃውልት፣ የላልይበላ ውቅር አብያተ-ክርስቲያናት፣ የሀረር ጀጎል ግንብ፣ የአባጁፋር ቤተ-መንግስት እና ሌሎች በርካታ ታሪካዊ እና ሃይማኖታዊ ምንጮች የየራሳቸው ስነ-ጥበባት፣ ስነ-ህንፃ እና ሃይማኖታዊ ስርዓቶችን አበርክተዋል፡ እነዚህ መዋቅሮች የአምልኮ ቦታዎች እና ጥበባዊ ማስረጃዎች በእምነት እና በተለያየ መንገድ የኢትዮጳያ ማህበረሰብን ቀርጸውታል።



ከአንድ አለት የተፈለፈለ የላልይበላ ውቅር አብያተ-ክርስቲያን





የሃረር ጀጎል ግንብ

## 2.2 ንጉሳዊ የመኖሪያ ስፍራዎች እና የጥበባት ማበብ

የኢትዮጵያ የተለያየ አገዛዝ ስርዓቶች መስፋፋት ተከትሎ የስነ ጥበብ መግለጫዎችም ተስፋፍተዋል። የንጉዊሳ ቤተ-መንግስት ወይም ፍርድ ቤት ዘርፈ ብዙ ጥበባት አላቸው። ሙዚቃ እና ስነ ጽሁፍ ተስፋፍተዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንደ ክራር አገልግሎት ላይ በመዋል የአድማጩችን ስሜት ለመግዛት ከመቻልም በላይ በአዝማሪዎች የሚቀነቀኑ ታሪካዊ የሙዚቃ ግጥሞች የህዝቡን ትኩረት መሳብ ችሏል። እነዚህ መገለጫዎች የንጉሳዊያን ቤተሰቦች ወይም ከፍተኛ ደረጃ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍልን ለማዝናናት ብቻ አገልግሎት ላይ የዋሉ አይደሉም። የመሪዎችን ስልጣን ህጋዊ እሳቤ የሚያሰጡ እንዲሁም የእነሱን ድል የሚዘክሩ እና ከእግዚአብሄር የተሰጡ ወይም የተቀቡ መሆናቸውን መልእክት የሚያስተላልፉበት በአጠቃላይ በጥበባት ስልቶች የማህበረሰቡ ድምጽ በመሆን የማህበረሰቡን ስሜት የሚገልጹ የጥበባት ውጤት ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ ጥበባዊ መገለጫዎች የብሄራዊ ማንነት መገለጫዎችን በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለማዳበር ወይም ለማጎልበት አገልግለዋል።

## 2.3 ጥበብ እና የማህበረሰብ ግርግር

ጥበብ ወይም የጥበብ ውጤቶች ለበርካታ ዘመናት የህዝብ ግርግርን ለመግለጽ አገልግሎት ላይ ውሏል። ህዝባዊ ግርግር ወይም ቀውስ በሚከሰትበት ፣ ኢትዮጵያ በተወረረችበት ፣ በተፈጥሮ አደጋዎች በተመታችበት ጊዜ እና መሰል ክስተቶች ባጋጠሙበት ወቅት የጥበብ ስራዎችን ተጠቅሞ ተግዳሮቶችን ለመቋቋም አስፈላጊ ስራዎች ተሰርቶበታል። የሃይማኖታዊ ስእላዊ መግለጫዎች በጥቁር ቀለማት የሚሳሉ ስእሎች ሲሆኑ ጦርነትን እና በችግር ጊዜ የሰዎችን ድፍረት እና እምነት ያሳያሉ። በመካከለኛ ዘመን የነበረው አይነተኛ ግጥም "የሰቆቃው ጴጥሮስ" በሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን የተፃፈው ሲሆን ኢትዮጵያ በጣሊያኖች በተወረረችበት ጊዜ ምን ያህል ለኢትዮጵያዊያን ከባድ ህመም እንደነበር ለማሳየት የተጠቀመበት ከፍተኛ ሃይል ያለው ማሳያ ግጥም ነው።

የ20ኛው ክፍለ ዘመን በሰው ልጅ ታሪክ አዲስ ነገር ይዞ የመጣ ነው። የኢትዮጵያ አርቲስቶች እንደነ ገብረክርስቶስ ደስታ የነበራቸውን የጥበብ ክህሎት ተጠቅመው ከአውሮፓውያን ጥበባት ጋር በማዋህድ ባህላዊ እና ዘመናዊ የጥበባት ንጥረ ነገሮችን በመቀየጥ መጠቀም የጀመሩበት ዘመን ነው። በመሆኑም ዘመኑ ለጥበብ አንድ እርምጃ ወደፊት ማሸጋገር የቻለ እና በፈጠራ ጥበባቸውም የፖለቲካ ስርዓት እና ማህበራዊ ኢ-ፍትሃዊ ተግባራትን በጥልቀት መቃወም የጀመሩበት ዘመን ነበር።

የኢትዮጵያ የጥበባት አሻራ እስከ ዛሬም ድረስ ህያው ሆኖ ይገኛል። ሰዎች ዛሬም ድረስ የተለያዩ ባህላዊ ጥበባትን እንደ  ሸማ ስራ ፣ ሸክላ ና ቅርጻ ቅርጽ  ጥበባት እየተጠቀሙ የሚገኝ ሲሆን ዘመናዊ አርቲስቶች ደግሞ በጥበባት ዘመናዊ ማንነታቸውን በማሰስ እና ከአለም ጋር  በማቆራኘት  የሀገሪቱን ውስብስብ ታሪክ ማሰስ ቀጥለዋል።

## የውይይት ጥያቄዎች

- የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሶችን ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ ያጋጠሙን ዋና ዋና ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸው?
    - *የከተሞች መስፋፋት እና ዘመናዊነት በአንድ በኩል ታሪካዊ ቅርሶችን እና ቦታዎችን ችላ ማለት  ወይም  መጥፋት ያስከትላል።*
    - *ባህላዊ ቱርፋቶችን ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ ምንም አይነት በጀት ወይም ውስን በጀት መኖሩ  የኢትዮጵያ ከአለት የተፈለፈሉ አብያተ-ክርስቲያናት ፣ የእጅ ጽሁፎች እና ጥንታዊ ባህላዊ መሳሪያዎችንለመጠበቅ ፈታኝ ያደርገዋል።*
    - *በአካባቢው ማህበረሰብ ለባህላዊ ቅርሶች የሚሰጠው ዋጋ ዝቅተኛ ወይም የሌለ መሆኑ፤*
- በእለት እለት የኑሮ እንቅስቃሴ ውስጥ የትኛው የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርስ ወይም ጥበብ አጋጥሞህ ያውቃል? መልሱ አዎ ከሆነ ካየህው ቅርስ ምን ተማርክ?
    - *በየቤተክርስቲያኑ ወይም በየቤቱ የሚገኙ ሃይማኖታዊ ስእሎች እንደ  ቅዱሳን ስእሎች ወይም መጽሀፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች ማሳየት፤*
    - *ባህላዊ እደ-ጥበባት እንደነ ቅርጫት፣ የሸክላ ውጤቶች፣ ጨርቃጨርቅ በየቀኑ የምንጠቀምባቸው ናቸው።*
- የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሶችን ለማስጎብኘት ኤግዚብሽን ለማሳየት እንደተዘጋጀ አድርገህ አስብ፤ በዚህ ጊዜ ትኩረት የምታደርግባቸው የጥበብ ቅርሶች የትኞቹ ናቸው ለምን?



# 3. ጥበብ ለአንድነትና ለብዝሃነት አከባበር

*የተለያዩ ባህሎችን፣ ብሄረሰቦችን እና ዳራዎቻቸውን ለማሳተፍ፣ የፈጠራ ድምፃቸውን እንዲሰጡ እና የጋራ ሰብአዊነትን እና ግንዛቤን ለማጠናከር ጥበብ አይነተኛ ሃይል ያለው መሳሪያ ነው።*

ይህ አንድነት በኢትዮጵያ ጥበባት የሚረጋገጥ ሆኖ በተለይ የታሪካዊ ቅርሶች መገለጫ ላይ ትኩረት በማድረግ የሃገሪቱን ብዙሃነት እንደ መልካም ታሪካዊ ነጸብራቅ በመጠቀም በርካታ ባህል እና የተለያዩ ስነ ህዝብ አንድነት ማረጋገጥ ይቻላል።

በኢትዮጵያ ባህላዊ እና ዘመናዊ ጥበባት በተለያዩ ሚዲያዎች እርስ በእርሳቸው አብረው ተደጋግፈው ይገኛሉ። የተለያዩ የፋብሪካ ውጤቶች፣ ውስብስብ ንድፍ ያላቸው ጨርቆች፣ ለልዩ ሥነ ሥርዓቶች እና በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ የሚለበሱ ልብሶች እና  ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች በተሞሉ ድንጋዮች የተቀረጹ አብያተ ክርስቲያናት፣ የመንገድ ጥበብ፣ ፎቶግራፍ እና የአፈጻጸም ጥበብ ካሉ የተለያዩ ባህላዊ እና ዘመናዊ ጥበባት አንድ ላይ የሚያገለግሉ መሆናቸው ማረጋገጫ ነው።

በመሆኑም እነዚህ ኢትዮጵያ ከምትታወቅባቸው እና ከበለጸገችባቸው በርካታ የተለያዩ ጥበባት የተወሰኑት ናቸው።

በኢትዮጵያ ማህበራዊ-ፖለቲካ ፍኖተ ካርታ። በአንድ በኩል ያሉት የሚስማሙበት የብሄር ፌደራሊዝም የተውሰኑትን በሄሮች ገፍቴ የሚውጡ ጥያቄዎቻቸውን መልሶል፣ ከነዚህም ውስጥ እራስን በራስ የማስተዳደር፣ የባህል እና ፖለቲካ ተሳትፎ፣ የስልጣን ክፍፍል እንደ ማሳያ ሊቆጠሩ ይችላሉ። በሌላ መንገድ ደግሞ የብሄር ፌደራሊዝም በጋራ ካሉን አንድነቶች ይልቅ ልዩነቶቻችንን በማጉላት በዘር የተደራጀን ግጭት በአገሪታ አምጥቷል ብለው የሚቀበሉም አሉ።



*ጥበብ መከፋፈልን በመዋጋት የአንድነት ድልድይ ግንባታ ረገድ - ይህ እንዴት ይሆናል?*

- ***የምንጋራቸው ስብአዊነት፦*** *ጥበብ የተለያዩ ታሪኮችን ወይም ሰብአዊ ስሜቶችን የሚጠቀም የአለም አቀፍ ቋንቋ በመሆኑ በብዙሃን መካከል አንድነትን እና መተሳሰብን የሚያቀነቅን እና የሚያጎለብት ነው።*
- ***መሰረታዊ ደረጃዎች፦*** *በጋራ የሚጋሩ እሴቶች እና የታሪክ ትሩፋት ላይ ትኩረት በማድረግ ጥበብ የባለቤትነትን ስሜት የሚፈጥር ማህበረሰባዊ አንድነትን የሚያጎለብት ነው።*
- ***ውይይትን ማነቃቃት፦*** *ተጽእኖ ፈጣሪ ጥበብ በማህበረሰቡ መካከል በጋራ ጉዳያቸው ላይ እንዲወያዩ መነቃቃትን  በመፍጠር፣ ለተከፋፈሉት ድልድይ በመሆን የሚያገናኝ እና የበለጠ የወደፊት አንድነት መንገድ የሚጠርግ ነው።*
- ***ብዝሃነትን ማክበር፦*** *ጥበብ ብዝሃነትን በማክበር አንድነት ከማረጋገጥ አንጻር ከፍተኛ ጥበባዊ ሃይል ያለው እንዲሁም በብዝሃነት ውስጥ የሚታዩመልካም ባህልን በማጠናከር ወይም በማጎልበት አካታችነትን ይገነባል።*
- ***ማህበረሰብ ግንባታ፦*** *የተቀናጀ የጥበብ ፕሮጀክቶች በጋራ የሚጋሩ አላማዎች ላይ ትኩረት በማድረግ እና የመጋራት ስሜት በማጎልበት በህዝቡ መካከል ከአንድነት ይልቅ ልዩነትን የሚያከሩ ግንቦችን በማፍረስ ጠንካራ አንድነት ያለው ማህበረሰብ ግንባታ ላይ ከምህበረሰባዊ ነትን ኛ ሚና አለው።*

*እነዚህ መሰረታዊ እና ማዕከላዊ እሴቶች ለሰላም ግንባታ ከፍተኛ ሃይል ያለው መሳሪያ የሆነውን ጥበብ በመለየት ወይም በማቀፍ አንድነትን ለማጎልበት የሚያገለግሉ ናቸው።*

## 3.1 የጥበብ ቅጾች

**የግድግዳ ስእሎች፦** *የህዝብ ጥበብ በማህበረሰቡ መካከል ውይይቶችን በማነሳሳት እና በሚጋሩአቸው እሴቶች እና ታሪኮች በጋራ ለጋራ ጉዳይ እንዲወያዩ ያነቃቃል።*




*አንድነት ያበራል፦*
*በሳር ቤት አዲስ አበባ ኢትዮጵያ አዲስ ስትሪት አርት በአፍሪካ ህብረት ከአውሮፓ ህብረት መልክተኞች ጋር በትብብር የተሰራ የግድግዳ ስእል፤*

*ፎቶ፦ በይሳቅ ሚደቅሳ*






***መልካሙን እንዝራ፦***
*በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ በአዲስ ጎዳናዎች ላይ የተሳሉ የግድግዳ ስእሎች በናሪሸያን ቤተክርስቲያን አርዳታ እና በኢትዮጵያ ትብብር የተሳሉ የስእል ጥበቦች*



### እርጥብ ሳር መያዝ የሰላም ምልክት ነው፤

*የጋሞ አባቶች በዞኑ የኦሮሞ ንብረት የሆኑ የንግድ ተቋማት ላይ የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ እርጥብ ሳር በእጆቻቸው በመያዝ በተቃዋሚዎች ፊት ተንበርክከው በመለመን ተቃዋሚዎቹን አስቁመዋል። በስፊው የተሰራጩ ምስሎች እና ቪዲዮዎች ይህንን ተምሳሌታዊ የሰላም ተግባራቸውን አሳይተዋል።*

***የጋሞ አባቶች፦*** *በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ የጋሞ አባቶች ምስል፣ በአዲስ ስትሪት አርት በኢትዮጵያ ከብራዚል ኤምባሲ ጋር በትብብር የተሳለ | አሲደምፕሮጀክት።*

*ፎቶ፦ በአዲስ ስትሪት አርት*

### አርቲስቱ ማነው?

**አዲስ ስትሪት አርት** በአዲስ አበባ ዙሪያ አንድነትን፣ ፍቅርን እና ሰላምን የሚያበረታቱ ግዙፍ የግድግዳ ስዕሎችን በመስራት ይታወቃሉ። እያንዳንዱ የግድግዳ ላይ ስእሎች አዲስ አበባ ለወደፊት የማህበራዊ ቅንጂት ያለባት እና ሰላም የሰፈነባት ከተማ ለመሆን እንደምትጥር ለተመልካቹ ያስረዳሉ።

**የአልባሳት ጥበባት፡-** ባህላዊ ልብሶች ሰዎች ከታሪካዊ ቅርሶቻቸው ጋር ተያያዥነት እንዳላቸውና ማህበረሰቡን በተቀናጀ ጥበባት ስራዎች ግንባታ የሚያገናኝ ወይም የሚያስተሳስ ነው።

**አርቲስቱ ማነው?**

**በሽሮ ሜዳ የሚገኙ ሽማ ሰሪዎች፡-** ሽሮ ሜዳ የባህላዊ አልባሳት ማዕከል ብቻ ሳይሆን የበርካታ ኢትዮጵያዊያን ብሄሮች ወይም የኢትዮጵያዊያን ህብረ ብሄርነት ማሳያ ማዕከል ነው። የሃገር ውስጥ እና የውጭ ጎብኚዎች የበርካታ ማህበረሰባችን ባህላዊ አልባሳት ሌሎች መለዋወጫ ዕቃዎቻቸውን ለመግዛት ወደ አካባቢው የሚጎርፉ ሲሆን የእያንዳንዱን ማህበረሰብ ባህል የበለጸገ መሆኑን ያረጋግጣሉ። እድ-ጥበቦቹ በዘር በተዋረድ በመጡ የአካባቢው ባለሙያዎች ወይም ሽማ ሰሪዎች እጅግ በተዋበ እና የሃገሪቱን ህብረ ብሄር ባማከለ መልኩ የተሰሩ እና የተመረቱ ናቸው። በተጨማሪም ባህላቸውን ከመንከባከብ እና ከማቆየት አልፎ ይህ አሰራር ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ሽማ ሰሪዎችን የእርስ በእርስ መከባበር ያዳበረ የእደ-ጥበብ ስራ ሂደት ነው። የስራዎቹን ጥበባት እና ምልክቶቻቸውን በምናይበት ጊዜ እጅግ በጣም ጥበባቸው የሚደነቅ ሆኖ ይገኛል። ይህ ልምድ ደግሞ መንገደኞች ወይም ተጓዦች በኢትዮጵያ ጥበባዊ ቅርሶች እንዲደመሙ አድርጓል።

**ሙዚቃ እና ዳንስ/ውዝዋዜ፡-** ባህላዊ ሙዚቃዎች እና ውዝዋዜዎቻቸው አንድነትን የሚያቀነቅን እና የሚያጎለብት ጥላቻን እና መከፋፈልን የሚያወግዝ አንድነትን ወይም በጋራ የመኖር ስሜት የሚያጎለብት ነው። ባህላዊ ወይም ቅይጥ ውዝዋዜዎች በእነዚህ በተለያዩ ወገኖች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያዳብር የባህላዊ ቅርሶች ማሳያ ማእከል፣ ብዝሃነትን ማክበር እንዲቻል የሚያደርግ እንዲሁም ግንዛቤ የሚያጎለብት ነው። ይህ የፈጠራ መገለጫም ለጌጥ ወይም ለውበት ብቻ ሳይሆን ታሪኮችን በማስተላለፍ፣ ባህላዊ መገላጫዎች እና የሃይል ግንባታ እና ጥንካሬ ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሃይል ያለው መሳሪያ ነው።

**አርቲስቱ ማነው?**

**መላኩ በላይ የፈንድቃ ባህላዊ ጭፈራ ቤት መስራች ዳሬክተር ተወዛዋዥ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ የግሎባል አምባሳደር ነው።** የእስክስታ ጭፈራ አይነተኛ እና ዋነኛው ባለሙያ የሆነ በዚህ ረገድ ያለው ክህሎት "ተንቀሳቃሹ የመሬት መንቀጥቀጥ" እና "የእስክስታው ንጉስ" ስያሜ አሰጥቶታል። መላኩ ጭፈራ የጀመረው በ1980ዎቹ በኢትዮጵያ ጎዳና ሲሆን ሙዚቃ እና ጭፈራ የእለት ተእለት ተግባሩ ሆነ፡ ፡ ከሃይማኖታዊ ክብረ-በዓላት ደግሞ እንደ ጥምቀት ክብረ-በዓል ላይ የሁሉንም ክልሎች



ጭፈራዎች ያሳያል። በዚህ ረገድ ያለው ወይም የሚያሳየው ቁርጠኝነት ቀጣይነት ያለው በመሆኑ መላኩ በኢትዮጵያ ወደ ተለያዩ አካባቢዎች እና ክልሎች በተደጋጋሚ በመጓዝ የሃገሪቱን የ80 ብሄረሰቦች ባህሎችን ወይም ባህላዊ ጭፈራቸውን የተማረ የሁሉንም ብሄሮች ባህላዊ ቅርሶች በዳንስ ያረጋገጠ ደንቅ ባለሞያ ነው።

**ተረት ተረቶች፡-** ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ የሚመጣ የአንድነትን ጠንካራ ገመድን የሚዘረጋ ነው። የሚጋሩ ተረቶች አብዛኛውን ጊዜ በጥሩ እና መጥፎ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች እና ልዩነቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ወይም የተለያዩ ተግዳሮቶች መቋቋም የሚቻልባቸውን መንገዶች በመግለጽ በማህበረሰብ መካከል የሚፈጠሩ መለያያ ግንቦችን የሚያስወግዱ ናቸው።

**አርቲስቱ ማነው?**

**አለቃ ገብረ ሃና፡-** በ19ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የጥበብ ምሁር ተብለው ይጠሩ የነበሩ በቅኔ ወይም በአማርኛ ግጥማቸው እጅግ የመጠቀ እውቀት ያላቸው የሃይማኖት አስተምሮ ስራ ላይ የተሰማሩ ነበሩ። በባህላዊ ቅኔ ከማንም የበለጡ እንዲሁም ገጣሚ እና ለኢትዮጵያ ቤተክርስሪያን አዲስ የክብረ በዓል አቋቋም ያስተዋወቁ የመጀመሪያው ሰው ነበሩ።

## የውይይት ጥያቄዎች

- ከላይ ከቀረበው ሃሳብ በተቃራኒ ጥበብን ጥላቻን ወይም ግጭትን እንዲቀሰቅስ ተድርጎ የቀረበበት ሁኔታ የመታቀው/ቂው አለ?
  - *እንደ ፖለቲካዊ ፕሮፖጋንዳዎች በደርግ ጊዜ ኢትዮጵያ ግዛቷ ከማንም በላይ መሆኑን የሚያቀነቅን ነበር።*
  - *ማህበራዊ ሚዲያ እና ዲጂታል ጥበቦች አንዳንድ ጊዜ ከፋፋይ ዘገባዎች/ትረካዎች ወይም የተሳሳተ መረጃዎች ያሰራጫሉ።*
- የተለያየ ባህሎች ያላቸው ማህበረሰቦች መካከል የተሻለ ግንኙነት እና መረዳዳት ለማረጋገጥ ባህል እንደ ድልድይ ሆኖ ለማገናኘት እንዴት ሚና ሊጫወት ይችላል?
  - *የሙዚቃ እና የውዝዋዜ ቅንጅት እንደ መላኩ በላይ ስራዎች የኢትዮጵያ ብዝሃ ባህላት እና ቅርሶችን በማራኪነት ማሳያ ማዕከል ሆነው ያገለግላሉ።*

*ጠይቅ፡- 10 ደቂቃ ወስዳቸሁ በአካባቢያቸሁ ጥበብ እንደ ማህበረሰብ መገናኛ ድልድል በመሆን እና የባህላት የተሳሳተ ግንዛቤዎችን በመቀነስ ያለው ጥቅም ላይ ሃሳብ ተለዋወጡ።*

- አካታች እና የማህበረሰቡን አንድነት ያረጋገጠ የሰላም ግንባታ ለወደፊት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የጥበብ ውጤቶች ሲባል ወደ አእምሮህ የሚመጡት የትኞቹ ናቸው?
  - *ዲጂታል ጥበባት እና ተጨባጭ ጥበባት ልምዶች የተለያዩ ቅንጅት እና ጥልቀት ያላው ሃይል በመፍጠር በማሃበረሰብ መካከል መተሳሰብን እና መረዳዳትን ይፈጥራሉ።*
  - *የጎዳና ላይ ጥበባት እና ስእሎች በይበልጥ በወጣቱ ትውልድ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ስለሆኑ ለማህበረሰቡ  ለማህበረሰቡ አንድነት እና ማህበራዊ ፍትህ ለማረጋገጥ ስልቶች ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። የማህበረሰብ ግንኙነቶች ወይም ግንባታዎች በጥበባት ወደ ምክክር እና ውይይት በማምጣት አንድነታቸውን በማጠናከር ለሰላም ግንባታ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ።*

# 4. ጥበብ እንደ የማህበራዊ ለውጥ ቀስቃሽነት

***ጥበባት ለቁንጅና ወይም ለጌጥ ብቻ ሳይሆን ለማህበራዊ ለውጥ ከፍተኛ እና ጠንካራ የለውጥ መሳሪያ ናቸው። አርትቪዝም የሚለው ቃል የ"ጥበብ" እና "አክቲቪዝም" የሆኑ ሁለት ቃላት ጥምረት ሲሆን አርቲስቶች ጥበባቸውን ለምክንያታዊነት ጉዳዮች እንዲጠቀሙ ይረዳቸዋል።*** ምንም እንኳን ምስሎቹ አስገዳጅ ምስሎች ወይም ስእሎች፣ ቅርጾች  ተጽእኖ ፈጣሪ ሙዚቃ፣ ውዝዋዜ ተግባራት ቢሆኑም መናገር ለማይችሉ ታሪኮች ወይም ትረካዎች በአግባቡ የሚያስተላልፉ ወይም የሚናገሩ ናቸው። ይዘቶቻቸውም ጠለቅ ያሉ ማህበራዊ ጉዳዮች ትኩረት የሚስቡ እና ማህበራዊ ወይይቶችን የሚቀሰቅሱ ለጋራ ውይይት እና ምክክር የሚያነሳሱ ወይም የሚለኩሱ ሁሉም ለተሻለ አለም እንዲሰሩ የሚያደርግ ሃይል አላቸው።

ሆኖም ግን ጥበባት በሌላ መንገድ ደግሞ ለአሉታዊ ፕሮፖጋንዳዎች ወይም ህዝብን ለመከፋፈል ወይም በብዙሃን ማህበረሰብ ውስጥ ጥቃት ሊቀሰቅሱ እንደሚችሉ መገንዘብ ይኖርብናል።

### አክቲቪዝም እንደ ሃይል ያለው መሳሪያ - ይህ እንዴት ይሆናል

**ግንዛቤዎችን ማዳበር፡-** አርቲስቶች የጥበብ ስራዎቻቸውን ለሌሎቻችን ሌላአዲስ አስተሳሰብ እንድንከተል የሚያደርጉ እና ዋና ዋና እውነታዎችን ከተሸፈኑበት በማጋለጥ በጥልቅ ጉዳዮች ላይ አመለካከታችንን ለመለወጥ የሚያስችሉ ሃሳባዊ እና ስሜታዊ ምላሾቻችንን በማርገብ ወደተሻለ ለውጥ እንድናመራ ወይም እንድናስብ ይሰራሉ። በቅርቡ በሃገራችን ኢትዮጵያ ስለሚስተዋለው ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በተመለከተ በርካታ አርቲስቶች ለሰላም እና ማህበራዊ ደህንነት የጥበብ ክህሎቶቻቸውን ተጠቅመው ህዝቡን አንቀሳቅሰዋል። ይሁን እንጂ በአንዳንድ ሁኔታዎች ጥበብ ጥላቻን ለማሰራጨት እና ብዙሃን ብሄሮችን ለመከፋፈል እንደ ምክንያት ያገለግላሉ።



**የማነቃቂያ እርምጃዎች፡-** ጥበብ በተፈጥሮ ህዝባዊ ውይይቶች እና ምክክሮችን የማነቃቃት እና ህዝቡን የተለየ ነገር ማድረግ እንዲችል መቀስቀስ ይችላሉ።
**ደህና ቦታ፡-** አርቲቪዝም የተፈለገውን ውጤት ማምጣት የሚቻለው ጸጥታው የተከበረ እና በነጻነት ሀሳብን የመግለጽ የሚችልበት የተመቻቸለት ስፍራ ሲቀናጅ ነው።

### የጥበብ ስራዎች

**ጦርነት አቁም፡-** በቅርቡ የወጣው የኤምዩኒክ ፊልም በኢትዮጵያ ለብዙ ሰብአዊ ጥፋት ምክንያት የሆነው ጦርነት ማቆም የሚቻልበትን ነጥቦች አንጸባርቋል። በሁለት አመታት ውስጥ ብቻ በ800 ሚሊየን ህዝብ ላይ ጉዳት ያደረሰውን ጦርነት በተመለከተ ፊልሙ የህዝብን ስቃይ፣ በተለይ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ለጦርነት እና ለግጭቱ ቁጥር አንድ ተጋላጭ የሆኑት ህጻናት ስቃይን አጋልጧል። ጦርነቱ ያስከተለው አስከፊ እልቂት ለማሳየት ከፍተኛ ሃይል ያለው መሳሪያ በመሆን በአስቸኳይ ሰላም መውረድ እንዳለበት የሚያስፈልግ መሆኑን አስታውሷል።

**ማሞ ቂሎ** በኢትዮጵያ ዩቲዩብ የሚተላለፍ ተከታታይ ትረካ ሲሆን በተለይ በአሽሙር እና በቅኔ ማህበራዊ ጉዳዮችን እና እውነተኛ ክህሎት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በተለይ በኢትዮጵያ የእለት ተእለት ኑሮ በተግዳሮቶች የተሞላ እንደሆነ በማሳየት ለእያንዳንዱን ግለሰብ ድምጽ ሆነዋል።

ከአሽሙር አነጋሮች በተጨማሪ ትረካዎችን በተለይ እጅግ በጣም ስሜታዊ ሊያደርጉ የሚችሉ ርእሰ ጉዳዮችን መቋቋም የሚያሰችል እንደ ሙስና፣ ድህነት እና የማህበራዊ አድሎን እና መድሎን ወይም እኩልነት ማጣት ላይ ትኩረት በማድረግ እያዝናና እያዋዘ የሚያስተላልፈው መልእክት እነዚህን ከባድ ርእሰ ጉዳዮች ወይም ስሜት የሚነኩ ርእሰ ጉዳዮችን ለመቀልበስ ይሰራል። ይህ የሚተላለፈው በዩቱብ ሲሆን በርካታ ሰዎች ዘንድ የደረሰ እና በርካቶችን ያሳተፈ ነው። ይህንን የሚከታተሉ እና የሚያዩ የራሳቸውን አስተያየት ስለሚጨምሩበት በጉዳዩ ላይ በተለይ በአጭር ድራማ የተነሱት ርእሰ ጉዳዮች ህዝባዊ ምክክር እና ውይይት ሊያነሳሳ ወይም ሊያቀጣጥል ይችላል።

**የበለጠ ለመረዳት፡-** *የአሽሙር ንግግር ስሜትን የሚኮረኩሩ ዘይቤዎችን በመጠቀም፣ በማጋነን ወይም በመሳለቅ በፖለቲካ አንጻራዊ ሁኔታዎች እና ሌሎች ርእሰ ጉዳዮች ላይ የሰዎችን ደካማ አመለካከት እና አስተሳሰብ በመተቸት መልእክቶችን ያስተላልፋል።*

**የርሃብ ሰለባዎች፡-** ቀዳማዊ ሃ/ስላሴ ከስልጣን ከመገርሰሳቸው በፊት የጥበባት ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ከንጉሱ አገዛዝ ስርዓት ጋር ተቃውሟቸውን ሲያሰሙ ከነበሩ ስራዎቻቸው "የርሃብ ሰለባዎች" በእሸቱ ጥሩነህ የተደረሰ አጭር መጣጥፍ ሲሆን በህዝብ ላይ በርሃብ ምክንያት የደረሰውን ሰቆቃ ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር።

ሶሻሊስት የደርግ መንግስት ስልጣን ከተቆጣጠረ በኋላ ጥበብ ዋነኛው የፖለቲካ ፕሮፖጋንዳ አይነተኛ መሳሪያ ሆነ። አርቲስቶች በሶቤት ሶሻሊስት በሰለጠኑና በተማሩት መሰረት ውስብስብ ጉዳዮችን ቀለል አድርጎ በማቅረብ ግዛቱን በከፍተኛ ደረጃ ከፍ ከፍ ያደርጉ ነበር። በዚህ ጊዜም ጥልቅ ትችቶች ሲሰሙ የነበ ሲሆን ከእነዚህም በግዛቱ ላይ የተጣሉ ማዕቀፎች፣ መልእክት አዘል ነበሩ።



*እሸቱ ጥሩነህ፦ የረሃብ አደጋ ሰለባዎች በ1974፣ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ሙዚየም አዲስ አበባ፤*



*ጌታቸው ዮሴፍ "አብዮታዊ እናት ሃገር ወይም ሞት"፣ 1979/1980 በኢትዮጵያ ብሄራዊ ሙዚየም አዲስ አበባ፤ ከኬት ኮውቸር*

## የውይይት ጥያቄዎች

- አርቲቪዝም/ጥበባዊነት ለብዙ ተመልካቾች ተደራሽነቱን ለማረጋገጥ እና በማህበራዊ ለውጥ ላይ ያለውን ተጽእኖ ለማሳደግ ምን ማድረግ ይችላል?
  - *ጠይቅ፦ ተሳታፊዎች በማህበረሰብ ተደራሽነት እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ እንዲያንጸባርቁ በተለይ የኢንተርኔት ተደራሽነት ወይም የገንዘብ ድጋፍ እጥረት፣ እና የሃሳብ ማሻሻያ መፍትሄዎች ዙሪያ እንዲናገሩ ጠይቃቸው።*
  - *አርቲቪዝምን ከትምህርት እንዲሁም ከማህበራዊ ሚዲያ ማሰራጫ ዘዴዎች በስፋት ለማቆራኘት እና ለማጎልበት እንዲቻል ከትምህርት ቤቶች እና ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በመቀናጀት መስራት እና ማህበረሰብን ማዕከል ያደረጉ እግዚብሽናችን፣ ዝግጅቶችን እና ወርክሾፖችን በአካባቢው ቋንቋ ማስተላለፍ እና አቀናጅቶ መስራት።*
- በአርቲቪዝም ምክንያት የሚመጣ ማህበራዊ ለውጥ ዘላቂ ሊሆን ይችላል? አዎ ከሆነ፣ ይህንን ለማረጋገጥ ምን ምን አይነት ስልቶችን መጠቀም እንችላለን?
  - *ሰነድ እና ማህደር የአርቲቪዝም ፕሮጀክቶች የወደፊት ትውልዶችን ለማነሳሳት፣ የማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን መዝገብ ለመጠበቅ እና ጥበባዊ ተነሳሽነቶችን ከትምህርታዊ ዘመቻዎች ጋር ለማጣመር ዘላቂ ግንዛቤን መፍጠር ነው።*



- ፈጣሪዎች ስራቸውን በማህበራዊ ለውጥ ሲተገበሩ ግምት ውስጥ ማስገባት ያለባቸውን ማንኛውንም የስነምግባር አመለካከት ማሰብ ይችላሉ?
  - *በሥነ ጥበብ ውስጥ የተገለጹትን የግለሰቦችን ወይም የማህበረሰብን ክብር እና ግላዊነት ማክበር፣ ሚስጥራዊነት ያላቸውን ጉዳዮች ለግል ጥቅም ወይም እውቅና ብቻ መበዝበዝን ማስወገድ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን በመግለጽ ከስሜታዊነት መቆጠብ፣ ባህላዊ ስሜቶችን በማስታወስ እና አመለካከቶችን ማስወገድ።*
- ማህበራዊ ለውጥን ለማምጣት ለአርቲቪዝም ውጤታማነት ታዳሚው ተጠያቂ ነው?

  *ጠይቅ፦ ተሳታፊዎች 5 ደቂቃ ወስደው ያላቸው ልምድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ፤*
  - *ከዚህ በፊት ከጥበብ ይዘት ጋር የተያያዘ ተነሳስተው ያውቃሉ?*
  - *ተመልካቾች አርቲስቶችን እና መንስኤዎቻቸውን የበለጠ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመደገፍ ምን ማድረግ ይችላሉ?*

# 5. ጥበብ ለድህረ-ግጭት ፈውስ

***ከግጭት በኋላ በግጭት ምክንያት የተፈጠሩ ቁስሎች በአካላዊም ሆነ በስነ ልቦና የሚያስከትለው ውጤት የግጭቱን ቁስል ያመረቅዛል። በመሆኑም ጥበብ ራሱን በቻለ የጥበብ ቋንቋ አዲስ ስነ-ልቦናዊ እና አካላዊ ፈውስ በተለይ በጦርነት ወይም በጥቃት ለተጎዳ ማህበረሰብ የጦርነት ወይም የግጭት ጠባሳን ለመግለጽ አይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል።***

የጦርነት ወይም የግጭቶች ሰለባ የነበሩ በመገምገም ያላቸውን ስሜት በጥበብ በመፈወስ የተለየ ማንነት በመገንባት በጥበብ ሃይል  በመጠቀም ወደ ተሻለ ምቹ ስሜት ማሸጋገር ይቻላል።

## 5.1 ጥበብ ጠባሳን ይፈውሳል - በዚህ መልኩ

- **ያልታዩትን መግለጽ፦** በጥበብ ግለሰቦች ያጋጠማቸውን ጉዳት ወይም እክል ቃልን ሳይጠቀሙ ለመግለጽ ተገቢ ቦታ ይፈጥርላቸዋል።
- **የመቋቋሚያ ስልቶች፦** የጥበብ ፈጠራዎች የጭንቀት እና ጥላቻ ወይም ድባቴ ፈውስ በመሆን አእምሯዊ ጤንነትን ይገነባል።

- **በራስ መተማመን መገንባት፡-** የጥበብ ፈጠራ ሂደቶች የተግባራት አፈጻጸም እና የራስ መተማመን እድሎችን ይፈጥራሉ።
- **መፈወስ እና ማስታረቅ፡-** የአርት ፕሮጀክቶች ማህበረሰብን በማሰባሰብ መቀራረባቸውን የሚያዳብር እና የሚያጠናክር ነው።
- **የማህበረሰብ ዳግም ግንባታ፡-** የተቀናጀ የጥበብ ስራ ማህበረሰቡ የሚጋራው አላማዎች በተመለከተ ይህንኑ ስሜት የሚያጎለብትበት የወደፊት ተስፋ የሚያለመልምበት ነው።

እርምጃ እንውሰድ

- **የትረካ ንግግሮች ሃይልን መጠቀም፡-** ኢትዮጵያ በተለያዩ ትረካዎች እና አባባሎች የበለጸገች በመሆኗ እነዚህን በተጨባጭ በጥበባት በሚታዩ ቅርጾች መጠቀም ይቻላል። በግጭት ውስጥ ያለፉትን ማህበረሰብ ወይም ግለሰቦችን ለመርዳት ያጋጠማቸውን በስእሎች፣ በተለያዩ ምስሎች ቅርጻቅርጾች፣ የግድግዳ ላይ ስእሎች በመጠቀም ግጭቱ ያስከተለባቸውን ስሜት እንዲያስወግዱ ማድረግ ይቻላል።
- **የሙዚቃ እና ውዝዋዜ ህክምና፡-** ሙዚቃ እና ውዝዋዜ የኢትዮጵያ ባህል አካል ናቸው። በሙዚቃ ዝግጅት ስሜቱ ለተጎዳ ማህበረሰብ የሚደረገው ህክምና ህብረተሰቡ በሙዚቃው ራሱን ወይም ስሜቱን ለመግለጽ ደህና ቦታ ማግኘት የሚችል በመሆኑ ባህላዊ ውዝዋዜዎች ለአካላዊ እና ስነ-ልቦና ህክምና አገልግሎት ሆነው ሊረዱ ይችላሉ።
- **ጉዳት እንዳያደርስ ለመከላከል የሚችሉ ባለሙያ መፈለግ፡-** ከግጭት በኋላ ላለው የስነልቦና ጠባሳ ህክምና ፈውስ ሂደት ጥበብን መጠቀም የባለሙያዎችን እርዳታ ወይም ልዩ ስልጠና ሊፈልግ ይችላል ምክንያቱም እንደዚህ ያሉ ሂደቶች በጣም ስሜታዊ ሊሆኑ እና አንዳንድ ጊዜ በተጠቂዎች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ።
- **ተንቀሳቃሽ የጥበብ ህክምና ቡድን፡-** ወደ ተለያዩ ራቅ ያሉ መንደሮች ድረስ በመጓዝ አገልግሎቱን በቀጥታ ለሚፈልጉት አካላት ወይም ማህበረሰብ ክፍል በአግባቡ መስጠት የሚችሉ ተንቀሳቃሽ ቡድን  አስፈላጊውን ያሟሉ ቡድን ማዘጋጀት እና ማሰማራት። ኢትዮጵያ እንደ ሌሎች ቦታዎች ሁሉ በተለይ በድረ-ግጭት ለግጭት ሰለባ ለሆኑ ማህበረሰብ ክፍል አስተሳሰብ እና ፈውስ ለመስጠት እና ለማገገም የሚያስችሉ የጥበብ ህክምና ያስፈልጋታል።



### አስታውስ፡-

**ለባህላዊ ስሜት ቀስቃሽ ነገሮች ጥንቃቄ ማድረግ፡-** ምንጊዜም ለባህላዊ ስሜት ቀስቃሽ ጉዳዮች እና ነገሮች በጥበብ ህክምና አገልግሎት መስጫ ወቅት ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። የአካባቢ ባህል፣ እምነት እና ሌሎችን ማክበር እና ከማህበረሰቡ ጋር የጥበብ ጥቅም ማስተጋባት ይገባል።

**ዘላቂነት፡-** ከአካባቢው ባለቤት ጋር ለዘላቂ መርሃ ግብር ትኩረት ማድረግ ይገባል። የአካባቢውን አርቲስቶች ማሰልጠን እና ከአስፈላጊ ምንጮች እና ግብአቶች ጋር ማህበረሰቡን ማስታጠቅ ወይም አሟልተው እንዲይዙ ማድረግ እና የጥበብ ህክምና አገልግሎት ለፈውስ እና ለመልካም አኗኗር መጠቀም ይገባል።

### የውይይት ጥያቄዎች፡-

- በጥበብም ሆነ በሌሎች የፈጠራ አገልግሎቶች በሚጠቀሙበት ጊዜ ያገጠመዎት ስሜታዊ ተግዳሮቶች ማስታወስ ይችላሉ?

  *መጠየቅ፡- 5 ደቂቃ ወስደው ባለፉት አመታት የነበሩትን ያስታውሱ። የትኛው ጊዜ ወይም ክስተት ከባድ ነበር? እንዴትስ አለፋት?*
- በድረ-ግጭት አካባቢዎች የጥበብ አርት ሚናዎችን ለመጠቀም ሲሞክሩ ያጋጠመዎት አስቸጋሪ ሁኔታዎች እና ያገኙት ግብረ መልስ ምን ሊሆን ይችላል?
  - *ተግዳሮት፡- በእርግጥ ቋንቋ እና ባህላዊ እንቅፋቶች በመጀመሪያ አካባቢ ለማገናኘት ውስብስብ ሁኔታ ፈጥሮ ነበር።*
  - *ተግዳሮት፡- ከድረ-ግጭት አካባቢዎች ውስን ግብዓቶች እና ለግብዓት የሚያገለግሉ የሎጂስቲክ ተግዳሮቶችን አስከትለዋል።*
  - *ተግዳሮት፡- በግጭት ምክንያት አንዳንድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ያጋጠማቸው ሰዎች ጋር መስራት አስቸጋሪ ሊሆን የሚችል እና በትግስት መስራት ያስፈልጋል።*
  - *አዎንታዊ ግብረ መልስ፡- ግለሰቦችን እና ማህበረሰብን ለመፈወስ የሚደረገው ድጋፍ እጅግ ከፍተኛ ልምድ የሚያሟላ ሊሆን ይችላል።*
  - *አዎንታዊ ግብረ መልስ፡- በጥበብ የአንዱን ሰነ-ልቦና ወይም ስሜት ማሻሻል ወይም በተጨባጭ ፈውስ ለማግኘት ከፍተኛ የጥበብ ልምድ ያስፈልጋል።*
- አስቸጋሪ ሁኔታዎች ያስከተሉ ክስተቶች ካሉበት የጥበብ ህክምና ዝግጅት ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ነዎት?
  - *ውይይት፡- ልምዱ ምን መሆን እንዳበት ተሳታፊዎች እንዴት ይገምታሉ?*

## ይህንን እንስራ

**ለሰላም እና ለፈጠራ መንፈስ መልካም ስሜት አለዎት?**

እሱን ወደ ተጨባጭ ተግባር እንለውጥ! በማህበረሰባችሁ ውስጥ የሰላም ግንባታ ለማጎልበት እነዚህ እንዴት ጥበብን ለሰላም በፈጠራ መጠቀም የሚያሳዩ ተግባራት ወይም ስራዎች ናቸው።

**1ኛ እርምጃ፡-** ቁልፍ ጉዳዮችን መለየት፡- በመጀመሪያ ደረጃ ለመቅረፍ የሚሞክሩትን ምንድን ነው? ማንን በመጀመሪያ ማነሳሳት ትፈልጋለህ? የምትሰብከው የሰላም መልእክት ምንድን ነው? የዘመቻዎ ግብ ምንድነው? እነዚህን ጥያቄዎች ካዘጋጀህ በኋላ ባሉ ግብዓቶች (እንደ ባጀት ጊዜ እና ክህሎት) በመጠቀም የራስን ማዕቀፍ ወይም ሽፋን ምረጥ፤
**ያስታውሱ፡-** ከጥበብ ስራዎች ጋር የሚጣመሩ እንደ ባህል፣ ሃይማኖት ወይም የፖለቲካ ሁኔታዎችን መገምገም።

**2ኛ እርምጃ፡-** የፈጠራ ሰው ሁን፡- የኦላይን ተግዳሮቶችን፣ የአካባቢው ጥበባት ፕሮጀክቶችን የጥበብ አፈጻጸም እና ተግባራት ወይም ሌሎች ተያያዥ የፈጠራ ተግባራትን መጠቀም ያበረታታል። ማቀድ እና ማደራጀት ማለት ተገቢውን የጊዜ ገደብ ማዘጋጀት እና እነዚህን በአግባቡ የሚከናወኑበት አካባቢ እና ማቴሪያሎችን በመለየት በጎ ፈቃደኞችን መዘርዘር እና የሚሰሩትን እና የት አካባቢ ተግባራዊ መደረግ እንዳለባቸው በማህበራዊ ሚዲያ፣ በአካበቢ ሚዲያ እና በበራሪ ወረቀቶች የማስተዋወቅ ስራዎችን መስራት።

**3ኛ እርምጃ፡-** ለምንሰራቸው ስራዎች ተገቢውን ዘዴ ይፍጠሩ፡- እንደ የማሰራጫ መረጃ መረቦችን፣ የማህበራዊ ሚዲያ ቦታዎች ወይም ተቀባይነት ያላቸው አሰራሮችን በተለይ የጥበብ ማሳያ የግል ቦታዎችን ማዘጋጀት። ሌሎች ወደዚህ የሚያመሩ እና የሚያነሳሱትን መጠቀም ወይም ማግኘት። እነሱም ባላቸው ጥበብ እና ስለ ሰላም ያላቸው ታሪኮችን ተቀላቅለው እንዲጋሩ ጠይቃቸው። ጥበብ የተሞላበት ንግግሮች፣ ወርክሾፖች፣ ውይይቶች እና የመረጃ ልውውጥ በማቀድ ለትልቅ ምክክር እና ውይይት ቅድመ ሁኔታዎችን እንዲያዘጋጁ አድርግ። እያንዳንዱ የበኩሉን ተሳትፎ እንዲያደርግ እና ለተለያዩ ድምጾች የበኩላቸውን እንዲያከብሩ ማድረግ።

**4ኛ እርምጃ፡-** በመቀጠል፣ በእውነት ትርጉም ያለው ለውጥ ያድርጉ፡- ጀብዱዎን በስዕሎች፣ ቪዲዮዎች እና የግል ታሪኮች ይያዙ። ስኬቶቻችሁን እና በአካባቢዎ ማህበረሰብ ላይ ያሳደሩትን ተጽእኖ ያካፍሉ። ስለ ቀጣይ ጉዳዮች ደግሞ ማሰብ እና በየአይነታቸው ማደራጀት ወይም ነገሮች በአግባቡ መሄዳቸውን መለየት እና ማወቅ፤

**5ኛ እርምጃ፡-** ሌሎች ውስጥ መነሳሳትን እንፍጠር፡- ጥበብ ተጠቅመው የሚያካሄዱትን የሰላም ጉዞ ከሌሎች ጋር መጋራት እና ፈጠራ እንዴት ሰላምን ማምጣት እንደሚችል ለሌሎች ማሳየት!



### የውይይት ጥያቄዎች፡-

- የእናንተን ማህበረሰብ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከሰላም ግንባታ ስራዎች ከማንም በላይ ተጠቃሚ የሚሆነው ማነው?
- በተለየ ሁኔታ ትኩረት አድርገህ የምትሰራበትን የተለ ስነ ህዝብ ወይም የተለየ የእድሜ ክልል አለህ?
- ያለህን ጊዜ እና የበጀት ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከምንም በላይ ለማደራጀት የምትፈልገው የጥበብ ፕሮጀክት የትኛው ነው?

# ለአመቻች የተዘጋጁ ማስታወሻዎች

## ዩዘት


76 | ስልጠና ማመቻቸት
76 | የክፍለ ጊዜዎን እቅድ ማውጣት
80 | መሰረታዊ ስልጠናዎች
81 | ክፍለ-ጊዜውን ማመቻቸት
84 | በራስ ከስልጠናው ያገኙትን ማብራራት


## 1. ስልጠና ማመቻቸት

በበቂ ዝግጅት እና የሰዎችን ትምህርት እና እድገት ለመደገፍ ባለው ቁርጠኝነት ላይ የተመሰረተ  አውደ ጥናቶችን በተሳካ ሁኔታ ማቅረብ።

ይህ መመሪያ እርስዎን ለመርዳት ቴክኒኮችን፣ ጠቃሚ ምክሮችን እና እንቅስቃሴዎችን ያካትታል።

## 2. የክፍለ ጊዜዎን እቅድ ማውጣት

**ትኩረት የሚሹትን መምረጥ**

እንደ አሰልጣኝ/አስተባባሪ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያስቡበት፡-

- የስልጠናው ዋና ትኩረት ምን እንደሚሆን ይወስኑ።
  - *ተሳታፊዎች እንዲማሩት የሚፈልጉት ነገር ምንድን ነው? ትኩረትዎ የተወሰነ መሆን አለበት። የስልጠናውን ዓላማ በአንድ ዓረፍተ ነገር በግልፅ እና በቀላሉ መግለጽ ሲችሉ ግብዎን ግልጽ አድርገዋል። ይህንን አንድ ዓረፍተ ነገር ይፃፉ፣ ስለዚህ በዒላማው ላይ ለመቆየት ስልጠናዎን ሲያቅዱ ሊያመለክቱት ይችላሉ።*

- ግቡን ከጻፍክ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስነብባቸው፡-
  - *ስልጠናው ግቡን እንዲመታ ምን ማድረግ ይችላሉ?*
  - *ምን ችግሮች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ መገመት እና አስቀድመው ለመፍታት ይሞክሩ?*
  - *ስለ የትኞቹ ጉዳዮች ለመነጋገር መዘጋጀት አለቦት?*
  - *ነገሮች ከፕሮግራም ውጭ እንዳይሆኑ ምን አይነት ህጎች አስቀድመው ማዘጋጀት ያስፈልግዎታል?*



**ማስታወሻዎችን በመላክ ላይ**

- ከስልጠናው አምስት ቀናት ቀደም ብሎ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ አጀንዳ ለተሳታፊዎች ይላኩ፡-
  - *ስልጠናው  የሚካሄድበት  ቦታ አቅጣጫ፤*
  - *ስልጠናው የሚጀመርበት እና  የሚጠናቀቅበት ትክክለኛ ሰአት፤*
  - *በስልጠናው ወቅት  የሚካተቱ ርዕስ እና ቁሳቁስ*

- ለተሳትፎ መስፈርቶች፣ ለምሳሌ የእንግሊዝኛ መሰረታዊ ግንዛቤ ወይም የተወሰነ የኮምፒዩተር እውቀት ደረጃ ካሉ ለተሳታፊዎችን ማሳወቅ።
- ከአውደ ጥናቱ ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ስለ ስልጠናው ለተሳታፊዎች ማሳወቅ።

**ይዘቱን በማዘጋጀት ላይ**

ስልጠናው ስኬታማ እንዲሆን፣ እርስዎ ከሚያስተምሩት ይዘት ጋር በደንብ ማወቅ አለብዎት። **የምናውቀውን ብቻ ነው ማስተማር የምንችለው።**

ለማስተማር ዝግጁ ለመሆን እነዚህን ምክሮች ይከተሉ፡-

- ከላይ እንደተብራራው የክፍሉን ዋና ግብ ገምግም። ከዚያም ይህንን ትኩረት በመጠቀም ለስልጠናው የትምህርት እቅድ ይፍጠሩ። በስልጠናው ወቅት **ምን** እንደሚሸፈኑ እና **መቼ** እንደሚሸፍኑት ይግለጹ።
- ሁሉንም ቁሳቁሶች ማንበብዎን እና በደንብ መረዳትዎን ያረጋግጡ።
- ተሳታፊዎች ምን ጥያቄዎች ሊኖራቸው እንደሚችል አስቡ እና እነዚህን ጥያቄዎች እንዴት እንደሚመልሱ አስቡ።
- ተሳታፊዎች ምን ግራ ሊያጋቡ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ ያስገቡ እና እሱን ለማስረዳት ሶስት መንገዶችን ያዘጋጁ።
- አስተምህሮዎትን ከፍላጎታቸው እና ከችሎታዎቻቸው ጋር ማስተካከል እንዲችሉ የተሳታፊዎችን የእውቀት እና የክህሎት ደረጃ ይወስኑ።
- ማንኛውንም ቪዲዮ ወይም ኦዲዮ ይዘት እና እንዴት መጫወት እንደሚችሉ በደንብ ማወቅዎን ያረጋግጡ።
- ከስልጠናው በፊት ርዕሶችን እና ሀሳቦችን ለጓደኞች እና ለቤተሰብ ማስረዳት እንደ መለማመድ ይረዳል። አንድን ነገር ለማብራራት ብዙ ጊዜ በሰራህ ቁጥር ቀላል ይሆናል። ስለዚህ ከስልጠናው በፊት በሌሎች ላይ ይለማመዱ እና በስልጠናው ቀን የበለጠ ዝግጁነት ይሰማዎታል እና ጠቃሚ መረጃ ለጓደኞችዎ እና ለቤተሰብዎ አባላት ያሰራጩ።

**የሚስፈልጉ ማቴሪያሎች**

- ለውይይት ክፍለ ጊዜው ማቴሪያል ወይም ግብዓት ያስፈልገዎታል? የሚያስፈልጉትን ማቴሪያሎች ወይም ግብዓቶች እንደ የመስክ መመሪያ ወይም ሌሎች ማቴሪያሎች በስልጠና ወቅት የሚጠቀምባቸውን አሁኑኑ ይሰብስቡ።
- ተሳታፊዎች ምን አይነት ማቴሪያሎች ይፈልጋሉ? ወረቀት? እስክርቢቶ ነው? ማንኛውም የታተመ ነገር?

**የክፍለ ጊዜው ሎጂስቲኮች**

- የክፍለ ጊዜውን እቅድ በሚያወጡበት ጊዜ የተዘረዘሩት ግቦችን በአእምሮ የያዙ። ተሳታፊዎች ስለ አንድ ነገር መማር ወይም መውሰድ የሚገባቸው ከሆነ ብቻ ምን ይደረጋል?
- ምን ያህል ጊዜ አለዎት ወይም ያስፈልገዎታል? ለመልመጃ ወይም መለማመጃ ክፍለ ጊዜ ከሚጠበቀው ጊዜ በላይ በመውሰድ በቂ ጊዜ ይኖረዎታል።
- በአሁኑ ጊዜ ያለዎት መሳሪያ ወይም ቦታ ምን አይነት ነው?
- ስንት ተሳታፊዎች ይገኛሉ? ከተጠበቁ ተሳታፊዎች በላይ ወይም ከተጠበቀ ተሳታፊዎች በታች የሚገኙ ከሆነ የስልጠናውን ጊዜ እቅድ በዚያህ መልኩ አስበው ያዘጋጁ።
- ተሳታፊዎቹ የምትፈልጉትን ቁልፍ ነጥቦች መገንዘባቸውን ለመረዳት አስበው ያረጋግጡ። የስልጠናው ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ በስልጠናው የተጠበቁትን ወይም ማቴሪያሎች ከ5 ደቂቃ በታች በሆነ ጊዜ በአጭሩ በማጠቃለል እንዲሁም ተሳታፊዎች ያገኙትን ክህሎት ጠቅለል አድርገው እንዲያብራሩ ያድርጉ።

ለስልጠና የተጠቀሙትን ርእሰ ጉዳዮች እና ለአድማጮች የሚመቹ እጅግ በጣም ማራኪ የማስተማሪያ ስልት ወይም ዘዴ ምንድን ናቸው? ? የተለያዩ በርካታ የሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ወይም ስልቶችን ተጠቀሙ።

የሚከተሉት በስልጠናው ክፍለ ጊዜ መጠቀም የሚችሏቸውን አንዳንድ የማስተማሪያ ስልቶች ወይም ፎርማቶች ናቸው፡-

- [ ] **ማስተማር** በቅድሚያ ሃሳባዊ የሆነ እርስ ጉዳይ ማስተዋወቅ ወይም ማብራራት ነው። ይህንን ክፍለ ጊዜ በ30 ደቂቃ ወይም ባነሰ ጊዜ ማጠናቀቅ እና ተያያዥ ወይም ተዛማጅ ነገሮችን በማስከተል ማብራራት። በሚያስተምሩበት ጊዜ በመነሻው እና በመጨረሻው የርእሱን አንኳር ነጥቦች ጠቅለል አድርገው ማቅረብ።

- [ ] ከማስተማሪያ ክፍለ ጊዜ በኋላ **ውይይቶች** ጠቃሚ ናቸው። ውይይቱን የሚያዳብሩ ያልተገደቡ ጥያቄዎን ማዘጋጀት ውይይቱን ለማጎልበት ይረዳሉ። በዚህ መልኩ የሚቀርቡ ያልተገደቡ ጥያቄዎች አዎን ወይም አይደለም የሚል አጭር መልስ የላቸውም። ነገር ግን ለማንሰላሰል የሚረዱ ናቸው። ያልተገደቡ ጥያቄዎች ምሳሌዎች፡-



- የተማርከውን በማህበረሰቡ ዘንድ ተግባራዊ እንዴት ያደርጋሉ?
- ስለ ውይይቱ ርዕሰ ጉዳይ በአግባቡ ለመረዳት እጅግ አስቸጋሪ የሆኑ ገጽታዎች የትኛቹ ናቸው?
- ሰዎች በኦላይን ላይ ያላቸውን ግንኙነቶች እንዴት መለወጥ ይቻላል ብለው ያስባሉ?

የውይይት ክፍለ ጊዜ ከተጠበቀው በላይ ረዥም ሰዓት ሊፈጅ ይችላል። በመሆኑም የጊዜ አጠቃቀመዎን ገደብ አስቀድመው በማመቻቸት ለተሳታፊዎች ግልጽ ያድርጉ። በዚህ ረገድም በቀላሉ ማለት የሚቻለው፤ “አሁን ለ10 ደቂቃ በርእስ ጉዳዩ ላይ ውይይት እናደርጋለን በመቀጠልም ወደ አስፋላጊ ጉዳይ እንሸጋገራለን።”

- [ ] **ማሳያዎች** በምትሰሩበት ጊዜ ስለእዚህ ጉዳይ የሚያጠናክሩ በአግባቡ ማሳየት የሚችሉ መንገድ ማዘጋጀት። አብዛኛውን ጊዜ በተሰበሰበው የቡድን አባላት ፊት አስፈላጊውን የማሳያ ቅደም ተከተሎች ለማቅረብ ጥሩ ሀሳብ የሚሆነው እያንዳንዱ ተሳታፊ ወይም ተማሪ በራሱ የፈለገውን እንዲያደርግ መምራት ነው። በዚህ አካሄድ ተሳታፊዎች ወዲያው ለማሳየት የፈለጉትን ነገር የሚያንጸባርቁ ወይም በማንሰላሰል የሚያቀርቡ ለመገንዘብ የሚያስፈልጋቸውን ነጥቦች ወይም ቦታዎች ይኖራቸዋል።

- [ ] **የኦላይን ትምህርት መከታተል፡-** ሰልጣኞች ስለተወሰነ ክህሎት ወይም እውቀት መማር በሚፈልጉበት ጊዜ የሚሰጣቸው ወይም የሚረዳቸው የኦላይን ትምህርት ሲሆን እንዲሁም በዚህ ጊዜ የሚያስፈልጋቸው የቪዲዮ ወይም ኦዲዮ ማቴሪያሎች መጠቀም የበለጠ ትምህርቱን ያግዛል።

- [ ] **ሚና መጫወት፡-** አዲስ ክህሎትን መስራት እና ከሌሎች ተሳታፊዎች አስተያየት መማርን ያካትታል።

- [ ] **የቡድን ስራ፡-** ብዙ ተሳታፊዎች ካሉ የቡድን ስራ ጥሩ ሀሳብ ነው። ትልቁን ቡድን ወደ ትናንሽ ቡድኖች መከፋፈል ትችላላችሁ፣ ይህም የበለጠ መስተጋብር እንዲፈጥሩ እና ለመወያየት እና ጥያቄዎችን ለመጠየቅ በቂ ጊዜ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። የቡድን ስራን በሚሰጥበት ጊዜ ሁሉ ለተሳታፊዎች ተግባራቶቹን ለመጨረስ ምን ያህል ጊዜ እንዳላቸው ይንገሩ እና ጊዜው ሊያልቅ ሲቃረብ የሶስት ደቂቃ ማስጠንቀቂያ ይስጡ።

- [ ] **ተያያዥ በጉዳዩ ላይ የተካሄደ ጥናት፡-** የጉዳይ ጥናቶች ተማሪዎች አዲስ መረጃን ወደ አውድ ውስጥ እንዲያስገቡ ይረዳቸዋል። መረጃውን ሲያካሂዱ እና ከተገቢው ሁኔታ ጋር ሲያገናኙ፣ መረጃውን በኋላ እንዲያስታውሱ የሚያግዙ የአዕምሮ ግንኙነቶችን ይፈጥራሉ።

## 3. መሰረታዊ ስልጠናዎች

- [ ] **በስልጠና ወቅት እንደ አንድ አመቻች የሚኖሩትን ሚና መገንዘብ፤**
በመግር ማስተማር ሂደት አመቻች መሰረታዊ ሚናዎች ይጫወታል። በስልጠና ወቅት አንድ አመቻች ከሚኖራቸው ዘርፈ ብዙ ሚናዎች እጅግ መሰረታዊ ነገር ለተሳታፊዎች ምቹ እና ደህንነቱ የተረጋገጠ አካባቢዎችን መፍጠር መቻል ነው። ተሳታፊዎች በስልጠና ወቅት ወይም ትምህርት በሚሰጣቸው ጊዜ በማንኛውም ጊዜ ጥያቄ ሲጠይቁ መልካም ስሜት ሊኖራቸው ይገባል። እንዲሁም ስለፈለጉት እና ስለሚያውቁት ስለ መልሱ እርግጠኛ ባይሆኑም መናገር መቻል ያስፈልጋቸዋል።

- [ ] **ቃናውን ማመቻቸት**
ሰዎች ውጤታማ ትምህርት ማግኘት የሚችሉት ድጋፍ ሰጪ እና ደህንነቱ የተረጋገጠ አካባቢ ሲመቻች ነው። ማንኛውም ከአስተሳሰብ እስከ ቃላት አመራረጥ ድረስ፣ በአካላዊ ምልቶች መግለጽ እና የአነጋገር ለዛ በስልጠናው ላይ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል። ስልጠናው በሚሰጥበት ጊዜ መልካም ገጽታን ማንጸባረቅና ድጋፍ መስጠት ላይ ያተኩሩ።

- [ ] **ተሳታፊዎችን ማሳተፍ**
በእያንዳንዱ የስልጠና ሂደት ተሳታፊዎን በንቃት ማሳተፍ አስፈላጊ ነው። ሰዎች በስልጠና ወቅት በአግባቡ ሲካፈሉ የበለጠ እንዲረዱ ያስችላቸዋል። አንዱ የተሳታፊዎችን ተሳትፎ የማነቃቃት ዘዴ በስልጠናው ሂደት በርካታ ጥያቄዎችን በማቅረብ ተሳታፊዎች በሙሉ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ ነው።

- [ ] **የስልጠናው አያያዝ**
እንደ አንድ ጉዳይ አመቻች እርስዎ የስልጠናው ክፍለ ጊዜ ስራ አስኪያጅ በመሆንዎስልጠናው በተቀመጠለት መርሃ ግብር ስለመከናወኑ ቁጥጥር ማድረግ የእርስዎ ሃላፊነት ነው። በስልጠና ወቅት የሚያጋጥሙ ከባድ እና ውስብስብ ወይም ያልተጠበቁ ሁኔታዎችን ውጤታማ በሆነ መልኩ መቀረፍ ይጠበቅበዎታል። በአጠቃላይ በስልጠና ወቅት የሙያጋጥሙ ችግሮችን ምንም ቢሆን ከቁጥጥር ውጪ እንዳይሆን የመቆጣጠር እና በአግባቡ የመያዝ ሃላፊነት ይኖረዎታል።

- [ ] **የጊዜ አጠቃቀም**
በስልጠና ወቅት ተሳታፊዎች የሚያስደስታቸው የቡድን ውይይትና ያላቸውን ልምድ ከሌሎች ጋር መጋራት ነው። ከዚህም የተነሳ ውይይት ሰፋ ያለ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። እንዲሁም የተጀመረውን ውይይት ምኑ ጋር መቋጨት እንዳለበት ማወቅ እና ወደ ተከታዩ ውይይት መሸጋገር ለስልጠናው አስፈላጊ ነው። በቀላሉ ስልጠናው በተያዘለት መርሃ ግብር መሰረት መካሄድ እንደሚያስፈልግ በመግለጽ ተሳታፊዎች ስልጠና ከተጠናቀቀ በኋላ መወያየት እንዲችሉ ማድረግ ይቻላል። ለተሳታፊዎች



ለመልመጃዎች ያላችውንግሳወቅ ጠቃሚ ነው። በመሆኑም ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት አንድ ሰው ለምን ያህል ደቂቃ እንደሚናገር ያሳውቁ። ከቡድን ስራ ወይም የተግባር ትምህርት ምን ያህል ጊዜ እንዳላቸው አሳውቃቸው። ይህ አሰራርን ተግባራዊ በሆነ ቁጥር የበለጠ ባዘጋጁት መርሃ ግብር መሰረት ስልጠናውን ማከናውን እና ስልጠናው በተያዘለት መርሃ ግብር በአግባቡ ማካሄድ ይችላል።

**እባክዎን ያስተውሉ፡-**

- የ#defyhatenow አሰልጣኞች እና አቅራቢዎች ወቅታዊውን ግጭት በተመለከተ የፖለቲካ አስተያየቶችን መጋራት የለባቸውም።
- ተሳታፊዎች የፖለቲካ ክርክር ውስጥ መግባት ወይም መሳደብ የለባቸውም። የአሰልጣኝ ሚናዎ ወደ ፖለቲካው ከተመለሱ ውይይቶችን ማቆም ነው።
- ከዋናው ርእሰ ጉዳይ የሚለይ ማንኛውንም ሰው የማስቆም መብት አለህ።

## 4. ክፍለ-ጊዜውን ማመቻቸት

- [ ] የሰዓት መቆጣጠሪያ ወረቀት
- [ ] የትራንስፖርት ማበረታቻ ወረቀት (የሚመለከተው ከሆነ)
- [ ] የግብረመልስ ዳሰሳ ቅፅ
- [ ] የእንቅስቃሴ ዘገባ አብነት
- [ ] ፎቶዎች/ቪዲዮዎች (ሰነድ/ፎቶግራፍ አንሺ፣ የድምጽ መቅጃ)
- [ ] ፕሮጀክተር (የሚመለከተው ከሆነ)
- [ ] ገበታዎች እና እስክሪብቶች
- [ ] ተርጓሚዎች (የሚመለከተው ከሆነ)
- [ ] ማስታወሻ ያዥ

መርሃ ግብር (የመጀመሪያ ቀን) [እንደ ምሳሌ ብቻ የሚያገለግል]

| ሰዓት | ርእስ |
|---|---|
| 08:30 - 09:00 | የስልጠናው መግቢያ እና ግቦች (መግር) |
| 9:00 - 10:00 | የፕሮፖጋንዳ እና ሃሰት ወሬዎች መግቢያ (ትምህርት እና በየቡድን ውይይቶች ማድረግ) |
| 10:00 - 11:00 | በማህበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግር ለመቀነስ ውይይት (የቡድን ስራ) |
| 11:00 - 11:30 | የሻይ ሰዓት |
| 11:30 - 13:00 | የማህበራዊ ሚዲያ ዘዴዎች/ፕላትፎርሞች፦ ቱዊተር፣ ኤፍቢ፣ እንስታግራም፣ ዩቱብ (ማሳያዎች የቡድን ስራ) |
| 13:00 - 14:00 | የምሳ ሰዓት |
| 14:00 - 14:30 | የኦላይን ዘመቻ እንዴት እንደሚዘጋጅ (ትምህርት) |
| 14:30 - 15:30 | ጠንካራ የማህበራዊ ሚዲያ ግንባታ ተግዳሮቶች (የውይይት ክፍለ ጊዜ) |
| 15:30 - 15:45 | የእረፍት ሰዓት |
| 15:45 - 17:00 | በኦላይን የምታቀርባቸውን (ትምህርት፣ ማሳያ፣ የቡድን ስራ) አያያዝ እና ቁጥጥር መሳሪያዎች |
| 17:00 - 17:30 | ግብረ መልስ እና ማስተላለፍ |



## ክፍለ ጊዜ ማስተዋወቅ

- [ ] **ከአድማጮች ጋር የማረጋገጥ ስራ ማድረግ፤**
  አንዴ ሁሉም ነገር ከተመቻቸ የእንኳን ደህና መጡ መልእክት ካስተላለፉ በኋላ የስልጠናውን **አላማ** እና **ግቦች** ማስተዋወቅ ነው። በዚህ ጊዜ ምን ማድረግ እንዳሰብክ እና የፈለከውን ሁኔታዎች በማዘጋጀት ተጠቀም። ስልጠናው የተረጋጋ እንዲሆን ትፈልጋለህ? ወይስ ሃይል የተሞላበት? ወይስ የተረጋጋ እና ግልጽ ስሜት የተሞላበት? የስብሰባውን ስሜት ለመቆጣጠር ሁሉም ነገር በእጅዎ ነው። ሁሉም የሰዓት መቆጣጠሪያ ቀጽ ላይ መፈረሙን አረጋገጡ።

- [ ] **ሎጂስቲክስ**
  በወርክሾፖ መነሻ አንዳንድ ደንቦችን ለማስቀመጥ ጊዜ ውሰድ፣ ለምሳሌ ሌሎች ሃሳባቸውን በሚገልጹበት ጊዜ ማክበር ያለብን ወይም ስለ ፖለቲካ መወያየት የሌለብን መሆኑን ተናገር። አስፈላጊ የሆኑትን እንደ መታጠቢያ ክፍል ሎጂስቲክስ የሚገኙበትን ለተሳታፊዎች መናገርም አስፈላጊ ነው።

- [ ] **ወደ አጀንዳው ይግቡ**
  ከተሳታፊዎቹ ጋር በቀጥታ ወደ ስብሰባው አጀንዳ በቀጥታ መግባት ተገቢ ይሆናል። **በድጋሚ የወርክሾፑን አላማ እና ግቦች** ማስታወስ እና ለተሳታፊዎች ማጋራትን ያስታውሱ። ተሳታፊዎች ስለሚማሩት ርዕሱ ጉዳይ በተሻለ መልኩ ከተረዱ በኋላ በተሻለ መልኩ መሳተፍ ይችላሉ። የስልጠናውን ዋና ዋና ርዕስ ጉዳዮች ወይም ነጥቦች ለሁሉም ተሳታፊዎች ጽፈው ማሳየት ይችላሉ። "ዛሬ የምንማረው ስለ ኤክስ ይሆናል" ብሎ መናገሩ ቀላል ነው።

## በክፍለ ጊዜው

- አዲስ እርስ ጉዳይ በሚያስተዋውቁበት ጊዜ ከቀላል ነጥቦች ጀምሮ ወደ ውስብስብ ይሄዱ። ከአንዱ ርዕስ ጉዳይ ወደ ሌላ ርዕስ ጉዳይ ከመሸጋገረዎት በፊት ውይይት ስለተካሄደበት ጉዳይ በአግባቡ እያንዳንዱ ተሳታፊ መረዳቱን ማረጋገጥ እና ያልገባቸው ወይም ያልተረዱት ካለ ጥያቄ እንዲጠይቁ ማበረታታት ወይም ጊዜ መስጠት አይዘንጉም።
- ጥያቄ የሚያቀርቡበትን ሰዓት ይስጡ ነገር ግን ጥያቄዎችን እና ውይይቶችን ከመርሃ ግብሩ ውጪ አይደረግ። በእቅድዎ መሰረት ሁሉም ነገር ይከናወን።
- ከእያንዳንዱ የውይይት አጀንዳ ሰዓት ወይም ጊዜ በኋላ ዋና ዋና እጅግ አስፈላጊ ነጥቦች ሃሳብ ጠቅላል አድርገው ያቅርቡ።
- በተቻለ መጠን ሁሉም በቀላሉ መረዳት የሚችለውን ቀላል ቋንቋ ይጠቀሙ። በመማር ማስተማር ወቅት ግልጽ ሀሳቦችን እና ግልጽ ቋንቋዎችን መጠቀም በጣም አስፈላጊ ናቸው።

**የመልመጃ ስራዎች**

- ለቡድን ስራዎች እና ለሌሎች የመልመጃ ስራዎች የራሳቸውን ሰዓት ጨምሮ ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ ይሰጣቸው።
- መልመጃዎቹን የምታሰራቸው ለምን እንደሆነ በግልጽ አብራራላቸው፤ እንዲሁም ከመልመጃዎቹ ምን ማግኘት እንደሚችሉ የምጠብቀውን አብራራላቸው።
- ከመልመጃዎቹ ጋር ተያይዞ ግብረ መልስ እና የተለያዩ ሃሳቦች መጋራት ካስፈለገ፣ የፈለከውን እና ቡድኑ እንዴት ማጋራት እንዳለበት ግልጽ አድርግላቸው። ለምሳሌ፦ በውይይቱ መጨረሻ የቡድኑ አባል የቡድኑ ሶስት ዋና ዋና የተማሩትን ነጥቦች ለሌሎች ማጋራት ይኖርበታል። ለማጋራት ግፋ ቢል 1 ደቂቃ ይሰጣችኋል።

### 3-2-1 የግብረ መልስ ክፍለ ጊዜ

በየስልጠናው ቀን መጨረሻ ተገቢ የእለቱ ስልጠና ማጠቃለያ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ የሚሰጡ ግብረ መልስ ክፍለ ጊዜ ያካትቱ ይኖራል። ለእያንዳንዱ ተሳታፊ የተጠየቁትን የሚጸፉበት ወረቀት ይሰጣቸው።

- ከተማሩት ሶስት ነገሮች
- በስራቸው ወይም በህይወታቸው የሚጠቀሙት ሁለት ነገሮች
- እስከ አሁን ያላቸው አንድ ጥያቄ

እነዚህን ግብረ መልሶች በማሰባሰብ አንብበው በቀጣይ ቀን ግልጽ መደረግ የሚገባቸው ጥያቄዎችን በጥልቀት በመከለስ ማዘጋጀት ይችላሉ። የአንድ ቀን ክፍለ ጊዜ ከሆነ ስልጠናውን የበለጠ ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ ከስልጠናው በኋላ በአግባቡ የተከናወኑ እና መለወጥ የሚገባቸው ለመለየት በግብረ መልሱ ይጠቀሙ።

**የመዝጊያ ፕሮግራም**

- እያንዳንዱ ተምሯል ብለው ተስፋ ያደረጉባቸውን ነጥቦች በተለይ ያገኙትን ክህሎቶች አስመልክቶ እንዴት በእለት ተእለት የህይወት እንቅስቃሴ ተግባራዊ በማድረግ እንሚጠቀሙበት ጠቅለል ባለ አገላለጽ ማብራራት።
- ስልጠናውን ገና ሲጀምሩ የዘረዘሩትን ወይም የፃፉትን ያጣቅሱ፦ “ዛሬ የምማረው ስለ x ይሆናል።” ይህ አባባል “ዛሬ የተማርነው ስለ x ነው” ወደሚለው አአባል ከተቀየረ ተሳታፊዎችን ጠይቃቸው።
- ቡድኑ እጅግ ጠቃሚ የሆኑትን ያገኙትን እንዲያብራሩ ወይም እንዲጋሩ ጠይቃቸው።
- ሁሉንም በመምጣታቸው አመስግናቸው። አግባብነት ያለው መስሎ ከታየህ ቀጣይ ስላለው ማንኛውም ሂደት አብራራላቸው።

## 5. በራስ ከስልጠናው ያገኙትን ማብራራት

ከስልጠናው በኋላ አስተያየቶቹን እና ስልጠናው እንዴት እንደሄደ ሀሳብዎን ይከልሱ። መጀመሪያ ላይ ያቀዱትን ግብ አሳክተዋል? አዎ ከሆነ፣ እንዲሳካልህ እንደረዳህ የተሰማህን ጻፍ። አንድ የተወሰነ ክፍለ ጊዜ



ነበር? የሆነ ነገር እንዴት እንደሚቀርብ ቅርጸት ነበር? ቁልፍ ጊዜ ነበር?

ግቡን ካላሳኩ ስልጠናውን ይከልሱ እና ምን እንደተፈጠረ ይወስኑ። ግቡ ከእውነታው የራቀ ነበር? ስልጠናው በበቂ ሁኔታ ታቅዶ አልነበረም? አንዳንድ ቁሳቁሶች ጎድሎዎት ነበር? በጣም ብዙ ትምህርቶችን ተጠቅመዋል? የበለጠ ስኬታማ ለመሆን በሚቀጥለው ጊዜ ምን መለወጥ ይችላሉ?

**የማረጋገጫ ዝርዝር**

ስልጠናው ሲጠናቀቅ የሚከተሉትን ሰብስበው ከቡድኑ ጋር ይጋሩ ያካፍሉ፦

- [ ] የክትትል (አቴንዳንስ) ወረቀት ከነፊርማዎች ተሟልተዋል
- [ ] የተሟላ የትራንስፖርት ክፍያ ወይም ደረሰኝ ቅጽ (የሚመለከታቸው ከሆኑ)
- [ ] የተሟሉ የግብረ መልስ ጥናት ቅጾች
- [ ] የተሟላ የመልመጃ ሪፖርቲንግ ቅጽ
- [ ] ፎቶዎች/ቪዲዮዎች
- [ ] ማንኛቸውም በወረቀት (ፍሊፕ ቻርትና ፖስት ኢት) ያሉ ማስታወሻዎች (ፎቶ ተነስተዋል/ተገልብጠዋል)
- [ ] የቡድን ውይይት ማስታወሻዎች ተሰብስበዋል
- [ ] ከተሳታፊዎች የድምፅ አስተያየት

# ማስታወሻ

# ምስጋና

በዚህ የጥላቻ ንግግር መቃወም ወይም መግታት ስልጠና ላይ ተሳትፋችሁ የራሳችሁን ሀሳብ ጊዜ እና አዋንታዊ ምላሾች አስተዋጽ ያበረከታችሁ እንዲሁም ላደረጋችሁት አይነተኛ ትብብር በተለይ በኢትዮጵያ፣ ካሜሮን፣ ደቡብ ሱዳን ዩጋንዳ እና ኬንያ ሌሎች በኦላይን በተለያዩ የአለም አቀፍ ክፍሎች ለሚገኙ የሰላም ግንባታ ሂደት ላበረከታችሁ ምስጋናችን የላቀ ነው።

#defyhatenow ይህን የመስክ ስራ ማንዋል ወይም መመሪያ ለመላው ኢትዮጳያ ዜጎች በተለይ ለህብረተሰቡ የተሻለ ሰላም ለመፍጠር ተቀናጅተው ለሚሰሩ በሙሉ ያቀርባል።

**የኢትዮጵያ ቡድን**
ብሩክ ተገኝ
ሜሮን አንተነህ
ቻላቸው ወርቁ
አህለም ቦጋለ
ናኦል ጌታቸው
አብርሃም ሰለሞን
ሃበን ገ/እግዚአብሄር

**የበርሊን ቡድን**
ስቲፈን ኮቫትስ
ሱዛን በሊንግሃውሰን
ካሎራይን ፓትሪክ
ሴዳ ሱዚንግ
ቫለንቲን ዋስሊው
ብሌን ገ/ህይወት ደስታ

**የናይሮቢ ቡድን**
ኬንዲ ጂኩንዳ
ዳንኤል ኪንግ ኦሪ
ኒጆኪ ካሪኡኪ

#defyhatenow
https://defyhatenow.org
https://defyhatenow.org/ethiopia/
https://www.facebook.com/defyhatenowethiopia/
https://www.instagram.com/defyhatenow_ethiopia/
https://www.facebook.com/defyhatenow
https://twitter.com/defyhatenow

ልዩ ምስጋና በኢትዮጵያ የፕሮጀክቱ ይፋዊ አስተዳደር አጋር ለሆነው ፖዘቲቭ ፒስ ኢትዮጵያ።

*የ#defyhatenow በኢትዮጵያ የኦንላይን ጥላቻ ንግግሮችን እና ብጥብጦችን ለመመከት የሲቪክ እና የዲጂታል እርምጃዎችን የመውሰድ እንቅስቃሴ የr0g_ኤጀንሲ ፎር ኦፐን ከልቸር ኤንድ ክሪቲካል ትራንስፎርሜሽን gGmbH በርሊን ሲሆን፣ በአውሮፓ ህብረት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ነው።*

agency for open culture & critical transformation
POSITIVE PEACE | ETHIOPIA
Funded by the European Union

